# ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በራያ አላማጣ ወረዳ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድሕረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር መርሐ ግብር ለኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አለማየሁ ሃፍተ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማካሪ፣ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ጥር 2004

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ክፍል

የኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር ድሕረ ምረቃ ኘሮግራም

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በራያ አላማጣ ወረዳ

ከአለማየሁ ሃፍተ


ጥቅምት 2004

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |

# Administrative Region and Woreda Map of Tigray




ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ማውጫ

ይዘት | ገጽ


አጠቃሎ

1. መግቢያ ........................................................................................................1

1.የራያ አላማጣ ሕዝብና አካባቢ ማስተዋወቂያ ......................................................1

1.1.1 ራያ አላማጣ ወረዳ የሚገኝበት ክልል ............................................................1

1.1.2የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ታሪክ (አፈ-ታሪክ እና ጡፍ ታሪክ)፣ ከጎረቤት ብሔረሰብ/ብሔረሰቦች ጋር ያለው ዝምድናና ግንኙነት። ..........................................2

1.1.3. የህዝቡ ዓይነትና ብዛት፣ የሚነገረው /የሚነገሩት ቋንቋ/ቋንቋዎች እና የቋንቋው /የቋንቋዎቹ ቤተሰብ/ ቤተሰቦች (language family /families). ..................5

1.1.4የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ አደረጃጀት (Social organization) ..........................6

1.1.5 የሃይማኖት ጉዳይ በራያ አላማጣ ወረዳ ..........................................................7

1.2. የጥናቱ ምንነት ........................................................................................8

1.2.1. ጥናቱን ለማኪያሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች ....................................................8

1.2.2. የጥናቱ ዓላማዎች (Objectives of the study) ............................................... 8

1.2.2.1. አጠቃላይ ዓላማ ..................................................................................8

1.2.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች..................................................................................8

1.2.3. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች...........................................................................9

1.2.4. መረጃው የተሰበሰበት ምንጭ ......................................................................10

1.2.5. መረጃው የቀረበበት መንገድ ........................................................................10

1.2.6. መረጃው የተተነተነበት መንገድ ....................................................................10

1.2.7 ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ቀደምት ጥናቶች ..........................................10

2. የራያ አላማጣ ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታበት/የሚፈታባቸው መዋቅር/መዋቅሮች (Structures)..............................................................................14

2.1 የግጭት ምንነት በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ........................................ 14

2.2 የግጭት መንስኤዎች በራያ አላማጣ ማህበረsብ................................................15

2.3. አንድ ጠብ (ግጭት) ሲፈጠር የሚኬድባቸው ቦታዎች ....................... ............ 15

2.3.1. ትልቅ ሰው ወደአለበት ቤት መሄድ ......19

2.3.2. በገዛ ፈቃድ ለአቦገረብ እጅ መስጠት ......19

2.3.3. ራት ብሎ ወደ ሚገኘው ቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ መሄድ ......20

2.4 በሽምግልናው ስርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት አካላት ......20

2.5. የአቦገረብ ምንነት ......21

2.6. የድባርተ ምንነት ......23

2.7. አቦገረብ የሚመረጡበት መስፈርት ......23

2.8.አቦገረብ የሚቀዩበት ጊዜ ......24

2.9 የመዋቅሩ ሁኔታ በአሁኑ ሰዓት ......25

3. የራያ አላማጣ ብሔረሰብ ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸው ሂደቶች (Procedures) ....28

3.1 ግጭት እንደ ተከሰተ መጀመርያ የሚሰማው አካል ......29

3.2 ግጭቱን የመመርመር ሁኔታ ......29

3.3 ሽማግሌዎቹ ወደ ውሳኔ የሚያመሩበት መንገድ ......30

3.4 የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ......30

3.5 አቦገረብ እና ድባርተ ወይም የአገር ሽማግሌዎች የወሰኑትን ተሟጋቾች እንዲቀበሉና በተግባር እንዲተረጉሙ የሚያደርጉበት መንገድ ......35

3.5.1 በታቦት እንዲምሉ ማድረግ ......35

3.5.2 ስነ-ቃል የአገር ሽማግሌዎች ወይም አቦገረብ እንዲከበሩ በማድረግ ያለው ፋይዳ፤ ..36

3.5.3 በጋብቻ ወይም በክርስትና እንዲተሳሰሩ በማድረግ ......36

3.5.4 በአቦገረብ ወይም በአካባቢው ህዝብ እንዲናቁ በማድረግ ......37

4. በራያ አላማጣ ማህበረሰብ የግጭት መፍቻ ስርዓት ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች እና የተሰጡ የውሳኔ ዓይነቶች ......38

4.1. ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች ......38

4.2. ከሴት (ውሽማ) ጋር የተያያዘ ግጭት ......38

4.3. በመጠጥ (በስካር) ምክንያት የሚከሰት ግጭት ......39

4.4. ከመሬት (የሚታረስ መሬት፣ ግጦሽ መሬት፣ ድንበር) የተያያዙ ግጭቶች ......39

4.5. ለከብቶች በተከለከለ መሬት ("ሕዛእቲ") የሚነሳ ግጭት ......40

4.6. የቤተሰብ ጠብ ......41

4.7. ወንጀል ......42

4.8. ተራ ወንጀሎች ......43

4.9. የቡድን ጠብ ......45

5. በመደበኛ ፍርድ ቤት፣ በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች መሀከል ያለ ግንኙነት ........ 48
5.1 አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓቶች በአሁኑ ጊዜ ........ 48
5.1.1 ለመስዋዕት የሚሆን እንስሳ ዕርድ ........ 49
5.2. በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ዘንድ አቦገረብ ከመደበኛው ፍርድ ቤት የሚመረጡበት ምክንያት ........ 51
5.3. በራያ አላማጣ ማህበረሰብ መደበኛ ፍርድ ቤት ከባህላዊው ይበልጥ ጠቃሚና ፍትሐዊ የመሆን ሁኔታ፤ ........ 51
5.4. በራያ አላማጣ ወረዳ አቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ከመደበኛ ፍርድ ቤት ጋር ያላቸው ዝምድና ........ 52
6. ትንተና እና ቁዘማ (Analysis and reflection) ........ 55
6.1. በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ያሏቸው ማህበራዊ እሴቶች፣ እምነቶችና መርሖች ........ 55
6.1.1. ድባርተ የሚጸልዩበት ወይም የሚለምኑበት ቦታ ........ 55
6.2. በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ላይ የሚታዩ ብርታቶች እና ድክመቶች፤ ........ 56
6.3. ጠበኞች አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቶች ተቀብለው ጉዳያቸውን ወደዚያ እንዲወስዱ የሚያደርጓቸው መሰረታዊ ምክንያቶች ........ 58
6.4. አቦገረብና ድባርተ ማህበራዊውን ሰላም የማስጠበቅና የማረጋጋት ፋይዳ ........ 59
6.5. የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ አቦገረብ ባህላዊ ስርዓት ከመደበኛው ፍርድ ቤት የሚመርጥበት ምክንያት ........ 61
6.6. በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ሂደት ውስጥ የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ያለው ሚና ........ 62
6.7. አቦገረብና ድባርተ ለተለያዩ ማሕበረሰብ ክፍሎች መብት የሚያስተናግዱበት ሁኔታ.... 63
6.8. በመደበኛው የፍትሕ ስርዓት ውስጥ ቢካተቱ የሚጠቅሙ የአቦገረብ እና ድባርተ መልካም ባህሪያት ........ 63
7. ማጠቃለያ (Ronclusion) ........ 65
8. ይሁንታ(Recomendations) ........ 67
ዋቢ መሕሀፍት(Bibliography)
የአውራ መረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በራያ አላማጣ ወረዳ የሚያተኩር ሲሆን፣የአካባቢው ማህበረሰብ በግጭት ወቅት ለዕርቅ የሚገለገልባቸውን አቦገረብ እና ድባርተ የተባሉ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች የሚከተሉት መዋቅር፣ሂደት እና ሌሎች ፎክሎራዊ ገጽታዎችን የሚዳስስ ነው። አቦገረብ የወንዶች ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ሲሆን፣ድባርተ የሴቶች ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ነው። የ"ራያ አላማጣ" ወረዳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ሚና አጉልቶ ማሳየት፤ እንዲሁም የግጭት አፈታት ዘዴዎቹ፣ ስነ-ስርዓቶች፣ ክንዋኔዎችና ፎክሎራዊ ገፅታዎች ማብራራት ደግሞ የጥናቱ ዓላማዎች ናቸው።

ይህ ጥናት በስምንት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ምዕራፍ ሁለት የራያ ማህበረሰብ ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅሮች(Structures)፣ምዕራፍ ሶስት የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸው ሂደቶች፣ ምዕራፍ አራት በራያ አላማጣ ወረዳ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች እና የተሰጡ ዓይነተኛ ውሳኔዎች፣ምዕራፍ አምስት በመደበኛ ፍርድ ቤት፣በአቦ ገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች መሀከል ያለ ግንኙነት፣ምዕራፍ ስድስት ትንተናና ቁዘማ፣ምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ እንዲሁም ምዕራፍ ስምንት ይሁንታ ናቸው።

የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ከዘመናዊው የህግ ስርዓት ይልቅ ባህላዊውን ይመርጣልስ። ስርቆት በአካባቢው ማሕበረሰብ ከባድ ወንጀል ከመሆኑ የተነሳ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶቹ ኣይካተትም ። በድባርተ በኩል በዕርቅ ወቅት የሚተባበሩ ቢሆኑም በአቦገረብ ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ብዙ ጊዜ እንደማይሳተፉ፣ በራያ አላማጣ ወረዳ ማሕበረሰብ ዋናዋና የግጭት መንስኤዎች ስካር፣ ሴት(ውሽማ) እና ግጦሽ መሬት እንደሆኑ፣አቦገረብ እና ድባርተ ለመሆን የሚጠቀሙባቸው መስፈርቶች ባላባት(የአካባቢው ተወላጅ) መሆን፣ የነገር ልክ የሚያውቅ፣የዕድሜ ባለጸጎች(በብዛት) ጨዋ ባህርይና ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው እንደሆኑ የጥናቱ ግኝቶች ናቸው። አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ዘላቂ መፍትሔ በማስገኘት ረገድ የላቀ ጠቀሜታ ስላላቸው የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትኩረት እንዲሰጡበት፣አቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ለማህበረሰቡ ባህል፣እምነት እና ልማድ የጀርባ አጥንት በመሆናቸው እነዚህ እሴቶች ቀጣይነታቸው እንዲረጋገጥ በማህበረሰቡም ሆነ በመንግስት አካላት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው የሚሉ ደግሞ የጥናቱ ይሁንታዎች ናቸው።

# 1 መግቢያ

## 1.1የራያ አላማጣ ሕዝብና አካባቢ ማስተዋወቂያ

### 1.1.1 ራያ አላማጣ ወረዳ የሚገኝበት ክልል

ራያ አላማጣ ወረዳ ከአዲስ አበባ በ584 ኪ.ሜ ርቀት በስተሰሜን አቅጣጫ፣ የትግራይ ክልል ዋና ከተማ ከሆነው መቀሌ ደግሞ በ170 ኪ.ሜ ርቀት በስተደቡብ አቅጣጫ ይገኛል። የራያ አላማጣ ወረዳ በሰሜንና በምስራቅ የራያ ዓዘቦ ወረዳ፣ በምዕራብ የኦፍላ ወረዳ፣ በደቡብ ደግሞ የአማራ ክልል ያካልሉታል።



ስእል 1 የራያ አላማጣ መልክአ ምድር በከፊል

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በራያ አላማጣ ወረዳ የሚያተኩር ሲሆን፣የአካባቢው ማህበረሰብ በግጭት ወቅት ለዕርቅ የሚገለገልባቸውን አቦገረብ እና ድባርተ የተባሉ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች የሚከተሉት መዋቅር፣ሂደት እና ሌሎች ፎክሎራዊ ገጽታዎችን የሚዳስስ ነው፡፡ አቦገረብ የወንዶች ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ሲሆን፣ድባርተ የሴቶች ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ነው፡፡ የ"ራያ አላማጣ" ወረዳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ሚና አጉልቶ ማሳየት፤ እንዲሁም የግጭት አፈታት ዘዴዎቹ፣ ስነ-ስርዓቶች፣ ክንዋኔዎችና ፎክሎራዊ ገፅታዎች ማብራራት ደግሞ የጥናቱ ዓላማዎች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት በስምንት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ምዕራፍ ሁለት የራያ ማህበረሰብ ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅሮች(Structures)፣ምዕራፍ ሶስት የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸው ሂደቶች፣ ምዕራፍ አራት በራያ አላማጣ ወረዳ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች እና የተሰጡ ዓይነተኛ ውሳኔዎች፣ምዕራፍ አምስት በመደበኛ ፍርድ ቤት፣በአቦ ገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች መሀከል ያለ ግንኙነት፣ምዕራፍ ስድስት ትንተናና ቁዘማ፣ምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ እንዲሁም ምዕራፍ ስምንት ይሁንታ ናቸው፡፡

የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ከዘመናዊው የህግ ስርዓት ይልቅ ባህላዊውን ይመርጣልስ፡፡ ስርቆት በአካባቢው ማሕበረሰብ ከባድ ወንጀል ከመሆኑ የተነሳ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶቹ ኣይካተትም ፡፡ በድባርተ በኩል በዕርቅ ወቅት የሚተባበሩ ቢሆኑም በአቦገረብ ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ብዙ ጊዜ እንደማይሳተፉ፣ በራያ አላማጣ ወረዳ ማሕበረሰብ ዋናዋና የግጭት መንስኤዎች ስካር፣ ሴት(ውሽማ) እና ግጦሽ መሬት እንደሆኑ፣አቦገረብ እና ድባርተ ለመሆን የሚጠቀሙባቸው መስፈርቶች ባባባት(የአካባቢው ተወላጅ) መሆን፣ የነገር ልክ የሚያውቅ፣የዕድሜ ባለጸጎች(በብዛት) ጨዋ ባህርይና ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው እንደሆኑ የጥናቱ ግኝቶች ናቸው፡፡ አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ዘላቂ መፍትሔ በማስገኘት ረገድ የላቀ ጠቀሜታ ስላላቸው የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትኩረት እንዲሰጡበት፣አቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ለማህበረሰቡ ባህል፣እምነት እና ልማድ የጀርባ አጥንት በመሆናቸው እነዚህ እሴቶች ቀጣይነታቸው እንዲረጋገጥ በማህበረሰቡም ሆነ በመንግስት አካላት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው የሚሉ ደግሞ የጥናቱ ይሁንታዎች ናቸው፡፡

### 1.1.3 የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ታሪክ (አፈ-ታሪክ እና ጡፍ ታሪክ)፣ ከጎረቤት ብሔረሰብ/ብሔረሰቦች ጋር ያለው ዝምድናና ግንኙነት።

የራያ ህዝብ አመጣጥ ወይም ታሪክ ስንቃኝ፣ ራያዎች ከዚህ አካባቢ መጡ ወይም የዚህ ህዝብ ዘር ናቸው ለማለት በሚያስቸግር መልኩ በርከት ያሉ አፈታሪኮች እና የተወሰኑ ጡፍ ታሪኮችን እናገኛለን።

ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ "የግራኝ አሕመድ ወረራ" በሚለው መፅሐፋቸው ራያ የሚለውን ስም እንደሚከተለው ይገልጹታል። "ይህ አገር በዚህ ስፍራ በዚህ ስም እስከ ዛሬ መኖሩን ወይም በእነ አፄ በዕደ ማርያም ዘመን ዶብኣ[1] ወይም ዶባ ይባል የነበረው [ከኦሮሞ] ወረራ ወዲህ በዋጅራትና በራያ ስያሜ መለወጡን በትክክል አላረጋግጥም" (1966፣81)።

እንደ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ አገላለፅ ራያ የሚለው ስያሜ ኦሮሞዎች አካባቢውን "ከወረሩ" በኂላ የመምጣቱ ሁኔታ አሻሚ ነው።

ከአፈ-ታሪኩ እንደሚሰማው ራያ የኦሮሞኛ ቃል ነው። አርሴ ማርየ እንደነገሩኝ ራያ ማለት በኦሮምኛ ቋንቋ ሰራዊት ወይም ወታደር ማለት ነው ይላሉ። በመስክ ላይ መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ አውራ መረጃ አቀባዮቼ ከሆኑት አንዱ አርሴ ማርየ እንደነገሩኝ

"ራያ ማለት እ... የእኛ ቋንቋ አይደለም፤ በኦሮምኛ ቋንቋ ግን ሰራዊት ማለት ነው" (ሚያዚያ 07፣2003፣ ስክርብ ገፅ 21) ።

ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ “የግራኝ አሕመድ ወረራ” በሚለው መፅሐፋቸው ስለ ራያ ስያሜ አመጣጥ የገለፁት ሐሳብና አርሴ ማርየ የነገሩኝ ሐሳብ፣ በከፊል የሚመሳሰል ሲሆን፣ በከፊል ደግሞ ይለያያል። ከኦሮሞ “ወረራ” በኂላ የመጣ ስያሜ መሆኑን ሁለቱም ሲገልፁ፣ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ዶብአ የነበረው ከኦሮሞ “ወረራ” ወዲህ በራያ ስያሜ መለወጡን ማረጋገጫ እንደሌላቸው ሲያብራሩ፣ አርሴ ማርየ ግን ራያ የሚለው ስያሜ ከኦሮሞ “ወረራ” በኂላ የመጣ የመሆኑ ማረጋገጫ የሚከተለውን ሐሣብ አቅርበዋል።

---

[1] ዶብኣ ወይም ዶብ የሚለው የገሮን አሞራና የገሮን ቀንጣፋ ወታደሮች ወግተው ያሸነፏቸው በጠቅላላው ግዕዙ “ሰብአ ዶባ” ይላቸዋል በማለት ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ይገልጹታል(1966ዓ.ም) ። ከዚህ ጋር አያይዘው አቶ ግደና መስፍን የተባሉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፊሎሎጂ መርሐ ግብር አስተባባሪ እንዲህ ይላሉ ። “ከአምባላጀ ተራራ (ደቡባዊ ትግራይ) በስተምዕራብ ካለው የተራራ ሰንሰለት አንዱ ተራራ አሁንም ድረስ “ጃንአሞራ” መባሉ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ከሚሉት የሚስማማ ይመስለኛል። ምክንያቱም ይህ አካባቢ የራያ መልክአ ምድር ሰሜናዊ ዳርቻ ነውና።“

"እነዚህ ጨርጨር፣ ገርጃለ፣ እ... ጋራርሳ፣ በየ፣ የሚባሉት የራያ አካባቢዎች ስማቸው የኦሮምኛ ነው። ስለዚህ ራያ ማለት ወታደር፣ ሰራዊት ማለት ነው" (ሚያዚያ 07፣2003 ስክርብ ገፅ 21) ።

አርሴ ማርየ ካሉት መገንዘብ የሚቻለው፣ ከላይ የተጠቀሱት አካባቢዎች የኦሮምኛ ቃላት ናቸው። ስለዚህ ራያም ከእነዚህ ስሞች አብሮ የመጣ ስለሆነ፣ ከ"ወረራው" በኋላ የመጣ ስያሜ መሆኑን እንደማስረጃ ሊቀርብ ይችላል። ምክንያቱም በአካባቢው የትግርኛ ቋንቋ ራያ የሚል ቃል ትርጉም የለውም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአላማጣ ወረዳ ታሪካዊ አመጣጥን ስንቃኝ በአፈ-ታሪክና በተለያዩ አካላት የተለያየ ስያሜ ሲሰጡት ይታያል።

"ሃርሞ ራያ" በሚለው መፅሔት የሚከተሉት የአላማጣ ወረዳ ስያሜዎች ተጠቁመዋል።

> አንድ ንጉስ ራቅ ካለ አካባቢ ይመጣና የአሁኑ አላማጣ አካባቢ ከደረሰ በኋላ ይመሸዋል፤ እሱም ከነሰራዊቱ እዛው ያድራል፤ የንጉሱ ሰራዊት ለዕራቱ የሚሆን በሬ አርዶ ስጋ ለመጥበስ እሳት ሲያቀጣጥል ንጉሱ ይቆጣሉ፤ እሳቱ ከታየ ጠላት ያየናል በማለትም እንዲጠፋ ያዝዛል። ሰራዊቱ ሁኔታውን ከተረዳ በኋላ ታድያ እንዴት አድርገን እንጥበሰው ብሎ ንጉሱን ሲጠይቀው፣ ንጉሱም የአማራ ሰው ስለነበረ "አላምጣ" ብሎ ስለተናገረ አላማጣ ተባለ ይባላል /ሰኔ 2002፣ 19/።

"አላምጣ" የሚለው ቃል ከዚህ አፈ ታሪክ እንደምንረዳው ንጉሱ፣ ለሰራዊታቸው የሚሆን የሚበላ ነገር እንደሌላቸውና ማምጣትም እንደማይችሉ ነው።

አላማጣ[2] ለሚለው ስያሜ ሌላው አፈ-ታሪክ "ሃርሞ ራያ" በሚለው መፅሔት እንዲህ በማለት ይገልፀዋል።

> በአንድ ወቅት በአላማጣ አካባቢ ድርቅ ይከሰትና፣ ከከተማው ራቅ ባለ ቦታ "ኦዳ"[3] ላይ ሆነው እናቶች ይለምናሉ። በዚህ ጊዜ ልመናቸው ሰምቶ

---

[2] "አላማጣ" የሚለውን ስያሜ "አላህ መጣ" ከሚለው መምጣቱ በስነ-ልሳን ጥናት ውህደተ ድምፅን (Merger) ያሳያል። ምክንያቱም በውህደተ ድምፅ (ሀ, ለ >ለ ወይም ሀ, ለ>ሀ) ይገልፃል። (Camp bell 2006;20).

ሀ, ለ የተለያዩ ሁለት ድምጾችን ይወክላሉ።

[3] "ኦዳ" ማለት ትልቅ ዋርካ ሲሆን፣ በራያ አካባቢ ድርቅና ሌሎች ችግሮች ሲከሰቱ እናቶች ለልመና ወይም ለምክክር ሚጠቀሙበት ቦታ ነው። "ኦዳ" የኦሮምኛ ቃል ነው፡(፡ምንጭ ከራሴ)

> ኃይለኛ የሆነ ዝናብ ይዘንብላቸዋል። የአካባቢው ሴቶች ወይም የሚለምኑ አዛውንት እናቶች እጅግ በጣም ተደስተው ይሄው ... "አላህ መጣ" ሲሉ አላማጣ የሚለው ስም ተሰጣት ይባላል / 2002፣ 19/።

እዚህ መነሳት ያለበት በተለያዩ ሰዎች የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የማይመሳሰሉ ናቸው። አላማጣ ለሚለው ስያሜ ሁለቱም ቀረቤታ ያላቸው ቢሆኑም፣ ታሪካዊ አመጣጣቸው ግን በእጅጉ ይለያያሉ። ስለዚህ ስያሜው አፈ-ታሪክ ስለሆነ ከሁለቱም አንዱን ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ሁለቱም ጭራሽ ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ። ከሁለተኛው ጥቅስ ጋር በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰል የአላማጣ ስያሜ አፈ-ታሪክ አቶ አርሴ ማርየ እንደነገሩኝ:-

> ግብረ ድንግል[4] ከላስታ ሲሸሹ እዚህ አካባቢ ጥሩ የምንጭ ውሃ ስላለ ከነሰራዊታቸውና ሰራተኞቻቸው አርፈው ነበር፤ እዚህ አካባቢ ንጉስ ከነሰራዊታቸው አሉ ሲባል የአገር ሽማግሌዎች ንጉሱን ለማየት ይመጣሉ፤ ንጉሱ ግን አልተገኙም፣ የአካባቢው ሽማግሌዎች ህዝቡን ሲጠይቁት ሌላ ንጉስ እየመጣ መሆኑን ስለሰሙ ሸሽተዋል ይሏቸዋል። ሽማግሌዎቹም ከንጉስ የሚበልጥ አላህ መጣ እንዴ? ስላሉ፣ ከዚያች ቀን ጀምሮ አላማጣ ተብላ ትጠራለች /ሚያዚያ 07፣2003፣ ስክርብ ገፅ 22/ ።

ከአፈ ታሪኩ መረዳት የሚቻለው"አላህ መጣ እንዴ?"የሚል አነጋገር ከጊዜ በኋላ የቃሉ ፍደላት እየተቀየሩና እየጠፉ" አላማጣ" ወደሚለው ቃል የተቀየረ ይመስላል።

የታሪኩ አመጣጥ የሁሉም አፈ-ታሪክ የተለያየ ቢሆንም፣ አላማጣ ለሚለው ስያሜ "አላህ መጣ" የሚቀራረበው ይመስላል። ምክንያቱም ከሶስቱም አፈ-ታሪኮች የሁለቱም የመጨረሻ ቃል "አላህ መጣ" የሚል ነው።ይሁንና የአካባቢ ስያሜ ከየትመጣነት ተረኮች በባሕርይ በእርግጠኝነት ለመወሰን አዳጋች መሆኑ ልብ ይሏል።

ራያ አላማጣ ወረዳ አጎራባች ብሔረሰብ ከሆኑት አፋር ክልልና አማራ ክልል የመተሳሰብ፣ የመተባበር ፣ የመጋጨት ወዘተ.. ሁኔታዎች ይታዩበታል።

> የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ከአማራ ክልል ጋር የጎላ ጠብ ባይኖራቸውም፣ ከአፋር ክልል ግን ይጋጫሉ። በሚጋጩበት ጊዜ ከመንግስታዊ የዕርቅ ስርዓት ይልቅ በአገር ሽማግሌዎች ይታረቃሉ።

---

[4] አቶ አርሴ ማርየ "ግብረ ድንግል" ያሉትን ከታሪክ ኢትዮጵያ የወጣ ወይም ተአማኒነት የጎደለው ይመስላል። ምናልባት "ግብረ ድንግል" የሚለውን [ልብነ ድንግል] የሚለውን ስም ለመጥቀስ የተጠቀመበት ይመስላል።

> የአፋር ክልል የጎሳ ባላባቶች[5] ከአቦገሬብ ጋር በመሆን ወይም በመመካከር የሚያደርጉት ዕርቅ ነው/ሚያዚያ 11፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 42/::

በማለት አንድ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ አባት ገልፀውልኛል።

### 1.1.4. የህዝቡ ብዛት፣ የሚነገረው ቋንቋ እና የቋንቋው ቤተሰብ (language family).

ሃረሞ ራያ የተባለው መጽሔት የራያ አላማጣ ወረዳ የህዝብ ብዛት እንደሚከተለው ገልጾታል(2002፣4)::

በ2001 ዓ/ም የህዝብና የቤት ቆጠራ መሰረት የራያ አላማጣ ወረዳ ህዝብ ብዛት 84,484 መሆኑ ይገመታል። ህዝቡ በአብዛኛው በገጠር አካባቢ የሚኖር ሲሆን፣ አንድ የከተማ ቀበሌን ጨምሮ አስራ አምስት ቀበሌዎች እና ሃምሳ ሶስት ጎጦች ይገኙበታል።

አሁንም "ሃርሞ ራያ" በተባለው መጽሔት የኣካባቢው ቋንቋ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል(2002፣5)::

ራያ አላማጣ ወረዳ በትግራይ ክልል ስር የሚተዳደር ቢሆንም፤ ህዝቡ የትግርኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች ተናጋሪ ነው። ይህም ልሳነ-ክልኤ ያደርገዋል።

እነዚህ ሁለት ቋንቋዎች በኢትዮ-ሰሜቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ስር እንደሚመደቡ ቤንደር እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

"….. Four of these are Ethio-Semtic languages. Amharic, Tigrinya, Tigre and Chaha" (1976: 64).

እንደ ቤንደር አከፋፈል ኢትዮ-ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦች አራት ሲሆኑ፤ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ትግረ እና ቸሀኛ ናቸው።

---

[55] "የጎሳ ባላባቶች"የአፋር ክልል ባህላዊ የዕርቅ አባቶች ናቸው። የአፋር ክልል ብሔረሰብ ከተለያዩ ጎረቤት ብሔረሰቦች ቢጋጩ (በድንበር ግጭት ጊዜ) ሲገጥማቸው ለማስታረቅ የሚቀርቡ አባቶች ናቸው (በአላማጣ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት አቶ መንገሻ ካሳ(ግንቦት 2፣ 2003 ዓ/ም፣ ስክርብ ገፅ 49)::

### 1.1.5 የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ አደረጃጀት (Social organization)

በራያ አላማጣ ወረዳ ከ "አቦገረብ" እና "ድባርተ" ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ውጪ ሌሎች የአገር ሽማግሌዎች አሉ፡፡ እነዚህ የአገር ሽማግሌዎች በግጦሽ መሬት ክፍፍል ጊዜ፣ በለቅሶ ጊዜ፣ በአንድ አንድ ሃይማኖታዊ እና መንግስታዊ ክብረ በዓላት በአስተባባሪነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

በግጦሽ መሬት አከፋፈል እና አስተዳደር የራያ አላማጣ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ስርዓት አለው፡፡ ጠብ ሲከሰት አንድ አንድ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደነገሩኝ እና ከማህበረሰቡ ጋር አብሬ ሳድግ እንደታዘብኩት፣ ችግሮች ሲከሰቱ በአካባቢው ሽማግሌዎች አማካኝነት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ከብቶች ሲሞቱበት፣ ሐዘን ሲያጋጥመው፣ የአካባቢው ህዝብ ገንዘብ ወይም እህል እንዲያዋጣ በማድረግ በመተባበር ይረዳዳሉ፡፡ ሌላው በራያ አላማጣ ወረዳ እና አካባቢው ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር የሚችለው "ኦፈራ" የሚባል የስራ ዘርፍ አለ፡፡ የ"ኦፈራ"ጠቀሜታ አውራ መረጃ አቀባዮቼ ከሆኑት አንዱ መንገሻ ካሳ እንዲህ በማለት ገልጾልኛል፡፡

> ኦፈራ[6] ማለት እንግዲህ .... በጋራ የሚሰራ ስራ ነው፡፡ ለምሳሌ ዛሬ እኔጋ ሆነህ ከሰራህ፣ ነገ ደግሞ አንተጋ እሰራለሁ ማለት ነው፡፡ ይህ ዋና ዓላማው በግብርናው መስክ ስራ ለማቃለል ተብሎ የተፈጠረ ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ አብረህ እየተጫወትክና እየተሳሳቅህ ስለምትውል ጠብህን ትረሳዋለህ፡፡ እነዚህ ማህበረሰቡ የፈጠራቸው Co-operation ወይም Co-ordination ሲሆኑ፣ እግረ መንገዳቸው ፍቅርና ሰላም የሚያነግሱ ናቸው (ግንቦት 2፣ 2003 ዓ/ም፣ ስክርብ ገፅ 49)፡፡

"ኦፈራ" አንድን ስራ ለማቃለለ ሲባል፣ በርከት ያሉ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ተሰባስበው የአንድ ሰው የስራ ጫና የሚያቃልሉበት የህብረት ስራ ነው፡፡ "ኦፈራ" በውቂያ፣ አጨዳ፣ ወይም በአረም ጊዜ ሊከወን ይችላል፡፡

የ "ኦፈራ" ዋና ዓላማ ተባብሮ መስራት ሲሆን፣ በተጨማሪም በአንድ አካባቢ ያሉትን ሰዎች በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ፣ በመካከላቸው የመቻቻልና የመተሳሰብ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ እነዚህን

---

[6] ኦፈራ የትግርኛ ቃል ሲሆን፣ ደቦ የሚለውን የአማርኛ ቃልን ይተካል፡፡(ምንጭ ከራሴ)

በመሳሰሉ ማህበራዊ አደረጃጀቶች (Social organizations) በመጠቀም በጋራ የሚኖርበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

### 1.1.7 የሃይማኖት ጉዳይ በራያ አላማጣ ወረዳ

ሃርሞ ራያ በተባለው መጽሔት የአካባቢው የሃይማኖት ጉዳይ እንደሚከተለው ይገልጸዋል (2002፣6)፡፡

በራያ አላማጣ ወረዳ ህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት መሰረት በወረዳው የሚገኝ ሕዝብ በብዛት የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን፣ ክርስትና 65% እስልምና 30%፣ እንዲሁም የሌላ ሃይማኖት ተከታይ 5% ይገኝበታል፡፡

በወረዳው የሃይማኖት መስተጋብርን ስንቃኝ፣ እስልምናና ክርስትና በእምነት ቢለያዩም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ማለትም በጋራ በመስራት እና ግጭቶችን በጋራ በመፍታት ረገድ ከፍተኛ የትብብር ልምድ አላቸው፡፡ የየራሳቸው የሆኑት ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ቢኖሯቸውም በመካከላቸው ጠብ ሲፈጠር ግን የሁለቱም አስታራቂ ሽማግሌዎች በመመካከር ችግሩን ለመፍታት ይተጋገዛሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ መንገሻ ካሳ እንደሚከተለው ነግሮኛል፡፡

> .... እዚህ ላይ በጣም የሚደንቅህ ነገር እ... በተለይም እስልምናና ክርስትና አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ፡፡ ሙስሊሞች እዚህ አካባቢ መስፈር ከጀመሩ ከአስራ ሶስተኛ ወይም አስራ አምስተኛ ክፍለ ዘመን ይመስለኛል... እ... የታሪክ መፃህፍት እና ትላልቅ አባቶች እንደሚናገሩት ማለት ነው፡፡ ሙስሊሞቹ ደግሞ ኦሮሞዎች ናቸው፡፡ ከአስራ ሶስተኛ ክፍለ ዘመን ሙስሊሞች ግዛት ማስፋፋት[7] ጀመሩ፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ሰሜን ወሎ እና ራያ ሜዳማ ስለሆነ ለግጦሽ መሬት ተስማሚ ነው፡፡ ስለዚህ ምን ልልህ ፈልጌ ነው እ... በክርስትና ሃይማኖት በብዛት "አቦገረብ" የዕርቅ ስርዓት ናቸው የሚከተሉት፤ ሙስሊሞቹ ደግሞ " ቃሊቾች" ናቸው፡፡ አልፎአልፎ ቃሊቾቹ "ዓሊ"[8] ይሏቸዋል፡፡ ወይም ደግሞ "ተፍሲር"[9] ይሏቸዋል (ግንቦት 2፣2003 ዓ/ም፣ ስክርብ ገፅ 52)፡

---

[7] የሙስሊሞች መስፋፋት (Muslim Expansion) መረጃ አቀባዩ መንገሻ ካሳ አስራ ሶስተኛ ወይም አስራ አምስተኛው አጋማሽ የሚለውን ግምታዊ ታሪክ፣ ከ1520ዎቹ ወዲህ ስለሆነ ሙስሊሞች ግዛት ማስፋፋት የጀመሩት፣ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን በሚለው ቢታረም ይመረጣል፡፡

[8]"ዓሊ" የዓረብኛ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም የናጠጠ እውቀት ያላቸው አባቶች ማለት ነው በማለት በፎሎሎጂ መርሐ ግብር የአረብኛ ፊሎሎጂ መምህር የሆኑት አቶ ከማል ኢብራሂም ገልጸውልኛል፡፡፡

## 1.2. የጥናቱ ምንነት

### 1.2.1. ጥናቱን ለማኪያሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች

የራያ ማህበረሰብ ተወልጄ ያደኩበት ነው፡፡ በተለይም ከተወለድኩበት አካባቢ የ96 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በሚገኘው ራያ አላማጣ ወረዳ በሚባለው አካባቢ ብዙ የግጭት ዓይነቶች እና ባሕላዊ የዕርቅ ስርዓቶች እንዳሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች እታዘብ ነበር፡፡ ከአፋሮች ጋር የድንበር ግጭት፣ በግጦሽ መሬት፣ በሴት (ውሽማ) በስካር እና በመሳሰሉ ነገሮች ግጭት ይነሳ ነበር፡፡

ሌላው ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት የሆነኝ በኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም የተማርኩት ትምህርት ከርዕሰ ጉዳዩ የሚያያዝ ሆኖ ስላገኘሁት የነበረኝን ፍላጎት ይበልጥ በመቀስቀስ እንዳጠናው አድርጎኛል፡፡

### 1.2.2. የጥናቱ ዓላማዎች (Objectives of the study)

ይህ ጥናት በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን የራያ አላማጣ ወረዳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ያተኮረ ሲሆን፡- አጠቃላይና ዝርዝር በሆኑ ዓላማዎች ተመስርቶ የሚቀርብ ነው፡፡

#### 1.2.2.1. አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ የ"ራያ አላማጣ" ወረዳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ለማህበረሰቡ ያላቸው ሚና በጥልቀት መተንተን፤ እንዲሁም የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ ስነ-ስርዓቶች፣ ክንዋኔዎችና ፎክሎራዊ ገፅታዎች ማብራራት ነው፡፡

#### 1.2.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ላይ ጥልቅ የሆነ ትንተና በማድረግ በማህበረሰቡ ላይ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ፤

---

[9] "ተፍሲር" ማለት የዓረብኛ ቃል ሆኖ፣ መተርጎም፣ መፍታት፣ መዳኘት እና ማገናዘብ ማለት ነው በማለት በፊሎሎጂ መርሐ ግብር የአረብኛ ፊሎሎጂ መምህር የሆኑት አቶ ከማል ኢብራሂም ገልጸውልኛል፡፡

(Natural Setting) ስላላጋጠመው ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት (Induced Natural setting) በማዘጋጀት የዕርቁ ስርዓት ሊያዘጋጅ ችሏል፡፡

### 1.2.4. መረጃው የተሰበሰበበት ምንጭ

የራያ አላማጣ ወረዳ የግጭት አፈታት ስርዓትን ለማጥናት መረጃ የተሰበሰበው የወረዳውን የባሕላዊ ዕርቅ ስርዓት ከሚያውቁት የአገር ሽማግሌዎች እና ከወረዳው አስተዳደሮች ነው፡፡

አቦገረብና ድባርተ ከሆኑት የተወሰኑትን በመምረጥ፣ እንዲሁም ከገበሬዎችና የአቦገረብ አባል እና መምህር ከሆነው አንድ ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ የአካባቢው እና የሕዝቡ ማስተዋወቂያ ከወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት፣ ከወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት፣ እንዲሁም በራያ አላማጣ አስተዳደር ከሚያዘጋጁት መጽሔቶች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

### 1.2.5. መረጃው የቀረበበት መንገድ

መረጃው የቀረበበት መንገድ በአብዛኛው በገለጻ (Description) ሲሆን፣ አውራ መረጃ አቀባዮች የተናገሩት በመጠቀም ብቻ ነው፡፡

### 1.2.6. መረጃው የተተነተነበት መንገድ

የማሕበረሰቡ የግጭት አፈታት ስርዓት የሚያሳትፋቸው መዋቅሮች፣ ሂደቶችና የአፈጻጸም ስነ-ስርዓት እንዲሁም የሚከተሏቸው ትእምርቶች ተተንትነዋል፡፡ የአተናተኑ መንገድም የዕርቅ ስርዓቶቹ ግጭትን የሚፈቱበት ዘዴ ቃልበቃል በሚባልበት ደረጃ ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ጋር የሚዛመድ በመሆኑ በማስተያየት እና ከማህበረሰቡ ልምድ ጋር በማዋሀድ ነው፡፡

### 1.2.7 ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ቀደምት ጥናቶች

በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ በትግርኛ የተሰሩ በርከት ያሉ ጥናቶች ቢኖሩም፣ ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ግን፣ በራያ ዙሪያ የተሰሩ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ናቸው፡፡ እስከ አሁን ድረስ በራያ ዙሪያ በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

ላይ ተጠንተው ያገኘኋቸው ሶስት ሲሆኑ፣ እነሱም የሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያ ፅሑፎች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች በራያ ያሉትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች አፈታት የተሰሩ ይሁኑ እንጂ፣ ባጠኗቸው የግጭት መፍቻ ዓይነቶች እና የአከዋወን ስርዓታቸው ከእኔ ጥናት የተለዩ ናቸው። ሶስቱም ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር በምን እንደሚመሳሰሉና እንደሚለዩ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

"Change and continuity in the traditional institutions and Mechanisms of local governance and conflict resolution among the Wajerat: An Ethno historical study" by Tarkegn Gebreyesus, 2005, (social Anthropology).

በዚህ ጥናት ላይ የተካተቱት ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች 'ዕስራ ዓዲ" "ገረብ" እና "ደመር" ናቸው። እነዚህ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች ምን ምን ፋይዳ እንደላቸው፣ ማህበረሰቡ ለባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች ያለው አመኔታ፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ለማህበረሰቡ ፍትህና አንድነት ያላቸው አስተዋፅኦ ዳስሷል።

"ዕስራ ዓዲ" "ደመር" እና "ገረብ" የሚባሉት ባሕላዊ ስርዓቶች የባህላዊ አስተዳደርና የግጭት መፍቻ ስርዓት ቢሆኑም፣ አጥኚው ከግጭት ጋር ያያዘው "ገረብ" ወይም "አቦገረብ" ብቻ ነው። በዚህ ጥናት "አቦገረብ" የድንበር ግጭት ሲከሰት የሚያደርጉት የዕርቅ ስርዓት ሂደትና አከዋወን ብቻ የሚዳስስ ነው። የእኔ ጥናት ግን ከዚህ ይለያል። ምክንያቱም "አቦገረብ" ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት በራያ አላማጣ ከድንበር ግጭት ውጪ ያሉትን ግጭቶች በተጨማሪ ይመለከታል። ስለዚህ አቦገረብ በእኔ ጥናት ሁለመናዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ነው።

ሌላው ከእኔ የጥናት ርእስ ጋር የሚዛመደው (Andargachew Tilahun, 2009) ሲሆን በሰሜናዊ ምስራቅ ትግራይ የሚገኙት የደስዓ ጎሳዎች ነው።

ደስአዎች ከአፋርና ከራያ በድንበር ስለሚገናኙ በባህላዊ ዕርቅ ስርዓታቸውም ከራያ ይመሳሰላሉ። "ደመርና" "አቦገረብ" የሚባሉት ስርዓቶች በከፊል የሚጠቀሙ ቢሆኑም፣በባህላዊ የዕርቅ ስርዓታቱ ህግ መሰረት ሴቶች በመሬት ርስት እና በሌሎች ባህላዊ ስርዓቶች ውሳኔ ላይ የመሳተፍ መብት የላቸውም።

"Women were not allowed to have possession right over the land and some traditional institution decisions (2009:55).

በደስአዎች ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎች በግጦሽ መሬት /ሕዛእቲ/፣ በደንና ተመሳሳይ ሃብቶች፣ በውሀ አጠቃቀም፣ በጠለፋ፣ ከመሬት ጋር የተያያዙ ግጭቶች፣ የድንበር ግጭቶች፣ ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ግጭቶች፣ ሀይማኖታዊ ግጭቶች  እና ከመሬት አከፋፈል ጋር የተያያዙ ግጭቶች ተጠቃሽ ናቸው፡

ደስአዎች ግጭቶችን የሚፈቱባቸው ሂደቶች አሉ፡፡ አንድ ግጭት ሲከሰት በተለይ ከግድያና ድንበር ግጭቶች ውጪ ከሆነ በቅድሚያ የቤተዘመድ ጉባኤ /ናይ ዓለተ-ዘመድ ጉባኤ/ ያየዋል፡፡

"Family or close relative elders council is made up of the same family linked in blood customarily, members of the immediate or extended family try to intervene and settle disputes (2009:102).

በድንበር ግጭት ወይም በ"ጋዝ"[10] ጊዜ ጦርነቱን የሚመሩ፣ የዕርቅ ስርዓት ሲፈፀምም በመሪነት (በሰብሳቢነት) የሚያገለግሉ አቦጋዝ ("Father of a raid") እና አቦገረብ ("Father of the river") በመባል ይታወቃሉ ሲል አጥኚው ያስገነዝባል፡፡ ከባህላዊው የአስተዳደር ስርዓታቱ ጎንለጎን የሚሰሩ ሃይማኖታዊ አስተዳደሮች /አባት፣ ገበዝ፣ አቃቢት፣) ይገኙበታል፡፡ በመሬት አስተዳደርም እንዲሁ (ርስቲ፣ ግራ ምሳሕ፣ ግራ ቤተክርስቲያን) በመባል የሚታወቁት ስርዓቶች አሉ፡፡

እያንዳንዱ የባህላዊ አስተዳደር ሹም (አቦገረብ፣ ደመር፣ ጭቃሹም፣ ዳኛ አቦ ሻራ፣ ከሳሲ ወይ ዓጋቲ) ምን አይነት ስራ እንዳላቸው አጥኚው ቢገልፅም፣ የባህላዊ አስተዳደር ሹሞች (ሽማግሌዎች)በምን እንደሚመረጡ ግን አልገለፀም፡፡

በግጭት ጊዜ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት፣ የሃይማኖት አባቶች እና የመሬት አስተዳደሮች የየራሳቸው የሆነ የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ አጥኚው እነዚህ ነገሮችን ማንሳቱ እንደ አወንታ ቢታይም በግጭት ጊዜ የአስተዳደር ስርዓቱ አንዱ በሌላው ጣልቃ የመግባት መብት ያለው መሆኑን እና አለመሆኑን ግን አልተመለከተውም፡፡ ምክንያቱም

---

[10] ጋዝ በግጦሽ መሬት እና በ ሌሎች ምክንያቶች ግጭቶች ሲከሰቱ በራያ እና በአፋር ህዝቦች የሚታይ አለመግባባት ወይም አለመስማማት ነው በማለት በግብርና ስራ የሚተዳደረው በእምባ አላጀ ወረዳ የሚኖር ሓዲስ ካልአይ ይገልጻል፡፡

በባህላዊ ስርዓቶች መካከል በስራ መደጋገፍ ሊኖር ይችላል፣ ባይኖርም እንኳ ለምን እንደማይደጋገፉ መመርመሩ ጠቃሚ ነው።

በዚህ ጥናት ውስጥ ሌላው ባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት "ድባርተ" ነው። አጥኚው እንዳለው "ድባርተ" የሴቶች ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ሲሆን፣ በድንበር ጦርነት ጊዜ እና በጋዝ ጊዜ ምህላና ጸሎት በማድረግ እናቶች እግዚአብሔርን የሚለምኑበት ስርዓት ነው። የእኔ ጥናት የሚያተኩረው የራያ አላማጣ ወረዳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ግን፣ በተወሰነ መልኩ ከዚህ የሚለይ ይመስለኛል። "ድባርተ" የሴቶች ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ቢሆንም፣ በድንበር ጦርነት እና በጋዝ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ግጭት ሲከሰት ነው። ምህላና ጸሎቱን ብቻቸው በመሆን ቢከውኑትም ወንዶች /አቦገረብ/ ጎን ለጎን ዕርቁን ወይም ስርዓቱን የሚያራምዱበት መንገድ አለ።

በዕርቁ ስርዓት የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

"Zäwäld" an Indigenous conflict Transformation in situation in Raya: Challenges and prospects." By Sisay Mengiste, 2010.

ይህ ጥናት በራያ ማህበረሰብ በተለይም በቆቦ ወረዳ የሚያተኩር ሲሆን፣ በዋናነት ያነሳቸው ነጥቦች፣ ዋና ዋና የዘወልድ ስርዓት ህጋዊ ተስተላልፎ ምን እንደሚመስል፣ የዛወልድ ስርዓት ሊቀየር እና ሊዳከም የሚያደርጉት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑና የመሳሰሉትን አንስቷል። በዚህ ጥናት በመጠኑ የተዳሰሱ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች "ቱፍታ"፣ "ወዳጃ"፣ "ድባርተ"፣"አባገረብ"፣ "ቆላ"፣ "ዘወልድ"፣ "መዛሪድ"፣ "ፍስኒ ሰገድ"፣ "የድደ ደንብ"፣ እና "ክፍሌ" ሲሆኑ፣ በእስልምና ሃይማኖት ግጭትን ለማብረድ የሚያስችሉ ደግሞ "ሼህ" (አበጋር) የሚባሉ እንዳሉ ይገልፃል። አጥኚው ከእነዚህ የዕርቅ ስርዓቶች መካከል በቆቦ ወረዳ በበዛት የሚሰራበትን "ዘወልድ" በመምረጥ አጥንቷል።

አጥኚው "ዘወልድ" ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ከትንሺ የባልና ሚስት ግጭት እስከ ትልቁ የግድያ እና የድንበር ግጭቶች ያሉትን የሚዳስስ መሆኑን ገልጿል። ስለዚህ አጥኚው "አቦገረብ" እና "ድባርተ" የሚባሉት ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በራያ እንዳሉ ጠቀሳቸው እንጂ ምንነታቸውን እና የአከዋወን ሂደታቸውን አልገለፀም።

የእኔ ጥናት ግን በራያ አላማጣ ወረዳ ይበልጥ የሚታወቁትን "አቦገረብ" እና "ድባርተ" የተባሉትን  ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በጥልቀት የሚዳስስ ነው፡፡

## 2. የራያ አላማጣ ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታበት/የሚፈታባቸው መዋቅር/መዋቅሮች (Structures)

### 2.1. በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ የግጭት ምንነት

ግጭት በተለያየ ስፍራ፣ በተለያየ ጊዜ፣ እንዲሁም በተያዩ ማህበረሰቦች የተለያየ ፍች ሊኖረው ይችላል፡፡ የተለያዩ ፍቾች የመኖራቸው ምክንያት በተለያዩ ሰዎች ባለው የእውቀት ወይም የአስተሳሰብ አድማስ፣ ከአኗኗራቸው እና ከተለያዩ ማህበራዊ እሴቶቻቸው የሚመነጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ግጭት ወይም ጠብ በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ምን ማለት እደንደሆነ አቶ እምባየ ደስታ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡፡ "ግጭት ማለትማ እ...7 እርስ በርስ አለመስማማት፣ ፍቅርና ሰላም ማጣት፣ ወይም ደግሞ የሰው ገንዘብ መመኘት እኮነው" (ሚያዚያ 22፣2003 ስክርብ ገፅ 23)፡፡

ስለዚህ ግጭት በራያ አላማጣ ማህበረሰብ የእርስ በርስ አለመስማማት፣ አንዱ በአንዱ ላይ መበቀል የሚል ፍች አለው፡፡ በአንድ አካባቢ ያሉት ማህበረሰቦች ተፋቅረውና ተስማምተው መኖር እያለባቸው፣አንዱ የአንዱን ንብረት በመፈለግ፣በአንዱ ፀጋ ላይ ሌላው ቅናት በማሳደር እና በመሳሰሉት ምክንያቶች በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ይታያል፡፡

በOSSREA ሁለተኛ ሃገራዊ አውደ ጥናት ላይ አሰፋ አበበ Goveን ጠቅሶ ግጭትን እንዲህ ይገልጸዋል፡፡ "The word <conflict> can be defined as "Clash, competition, or mutual interfrence of opposing or incompatible forces or qualities (as ideas, interests, wills)" (OSSREA 2005, 52).

እንደ አሰፋ አባባል፡- ግጭት አንድ ጥቅም ለማግኘት በሚፎካከሩ ሁለት ተቃራኒ ኃይሎች መሀከል የሚከሰት አለመስማማት ወይም ትንንቅ ሲሆን፣ ይህም ካላቸው ሐሳብ፣ ፍላጎት እና ምኞት የሚመነጭ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ የጠብንና አለመግባባትን ብያኔ መስጠት ሲሞክር እንዲህ ይላል፡- "In most cases, conflict

and dispute are used interchangeably and the term "dispute" can be defined as "Verbal controversy, strict by opposing argument or expression of opposing views or claims, controversial discussion" (OSSREA 2005, 52).

የግጭት ሌላው ገፅ አለመግባባት ሲሆን፣ የቃላት ክርክር፣ ሐሳብን ወይም አገላለፅን፣ ወይም ደግሞ በአንዱ አመለካከት ወይም ተቃውሞ መከራከርን የሚያሳይ ነው። የዚህ ሐሳብ ከራያ አላማጣ ማህበረሰብ ለግጭት ያለው አመለካከት ሲተያይ የአገላለፅ ልዩነት ቢኖረውም፣ በግጭት ላይ ያላቸው ፍች ግን ተመሳሳይ ነው።

## 2.2 የግጭት መንስኤዎች

- ግጭት በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። በሰዎች መካከል ተፋቅሮ መኖር እንዳለ ሁሉ፣ መጣላት ወይም መጋጨትም አለ። ሰዎች ተግባብተውና ተዋደው እንዳይኖሩ፣ የሚያደናቅፉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። Yosef G.M.and Tesfaye W.M.የግጭት መነስኤዎች እንዲህ ይገልፁታል።

> "The causes are as diverse as the conflicts, and tge pattern to them.In enter-personal conflicts include desertion, adultery,violence in the home and the like.At the higher level involving grups threats over territory often involve property disputes or controversy over resourses us age by different groups"(2008:7).

> የግጭቶች መንስኤ ቁጥር በግጭቶቹ መጠንና ዓይነት የሚለያይ ነው። በግለሰዎች ደረጃ የሚከሰቱ ግጭቶች በሽርሙጥና፣ ድብድብ፣ ወልዶ መጣልና የመሳሰሉ ምክንያቶች የሚከሰቱ ሲሆኑ፣እንዲሁም በተደራጁ ቡድኖች መሐል የሚከሰቱና ድንበር ዘለልም ሲሆኑ ይችላሉ።እነዚህ ግጭቶች በምጣኔ ሐሳብ አጠቃቀም ሳቢያ የሚከሰቱ ናቸው።

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ሰዎች እንዲጋጩ የሚያደርጉ ምክንያቶች ወይም የጠብ መንስኤዎች ስካር፣ ውሽማ መያዝ፣ በግጦሽ መሬት፣ በድንበር እና የመሳሰሉት ናቸው።

(ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 25) በማለት አቶ እምባየ ደስታ ነግረውኛል።

እንደ አቶ እምባየ ደስታ አባባል፣ ግጭት ሲከሰት መጀመሪያ የት ይኬዳል? ለሚለው የድሮና የአሁኑ የተለያዩ መሆናቸውን እንገነዘባለን። በድሮ ጊዜ ጥፋት የፈፀመው አካል ትልቅ ሰው ወዳለበት ቤት በመሄድ፣ ሌላ ደም መፋሰስ እንዳይከሰት ይደረግ ነበር። ገዳዩ ተደብቆ እያለ፣ ያስደበቀው ሰው እና ሌሎች ሽማግሌዎች ጨምሮ ወደ ሟች ዘመድ በመሄድ፣ ገዳዩ እጃቸው ላይ እንዳለ በመናገር መፀፀቱንና ጥፋተኝነት የተሰማው መሆኑን ይነግሯቸዋል። ገዳዩ ጥፋተኛ መሆኑን እንደተረዳና እንደተፀፀተ እምባየ ደስታ ሲገልፁ "ሁሉም ነገር ለእኛ ተውሉን፣ እኛጋር እያለቀሰ፣ በሰራው ሰይጣናዊ ስራ እየተፀፀተ ነው፤ እህል አይበላ ውሃ አይጠጣ፤ ከሟቹ ይልቅ እሱ ከፍቶታል፤ ብለን" እንነግራቸዋለን" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 25) ይላሉ።



ስእል 2 አውራ መረጃ አቀባዮቼ ከሆኑት አንዱ አቶ እምባየ ደስታ

በዚህ ጊዜ የሟች ወይም የተበዳይ ወገኖች በተወሰነ መልኩ ይረጋጋሉ። ምክንያቱም ገዳዩን ያስደበቀው ሰው ሄዶ ካስታወቀ ከባድ ኃላፊነት እንደተሸከመ የሟች ወገኖች ያውቃሉ። የሟች ወገኖች ተቆጥተው ገዳዩን ለመጉዳት ወይም ለመበቀል አይሯሯጡም። ገዳዩ ሽማግሌዎቹ እጅ ላይ ከገባ ከቁጥጥራቸው ስር እንደሆነ ያምናሉ።

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ዋና የግጭት መንስኤዎች ምንምን እንደሆኑ አቶ ተላ ቓሺ እንዲህ ብለዋል፡፡

"… ስለዚህ መጠጥ ቤት ችግር ነው፡፡ በሴት የሚጣሉም አሉ፡፡ እ…. በመሬት፣ እ… ለከብቶች ተብሎ በተከለከለ ቦታ፣ ከብቶችህ ከገቡ ጠብ ሊነሳ ይችላል፤ ጋሪ ስንቱ፡፡ በብዙ ምክንያት ትጣላለህ" (ግንቦት 02፣2003፣ስክርብ ገፅ 58) ፡፡

## 2.3. አንድ ጠብ (ግጭት) ሲፈጠር የሚኬድባቸው ደረጃዎች

የራያ አላማጣ ማህበረሰብ አንድ ግጭት ሲከሰት ወደ ተለያዩ አካላት በመሄድ የተከሰተው ጠብ ይፈታል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ሰዎች ተጋጭተው፣ በቂም በቀል መቀጠል ወይም ውሎ ማደር ነውር ነው፡፡ ጠቡ እንደከሰተ እንደየ ግጭቱ ዓይነት የአገር ሽማግሌዎች አይተው እንዲዳኟቸው ይደረጋል፡፡

የአካባቢው ዋና የግጭት ማብረጃዎች ተቋማት አቦገረብና ድባርተ ቢሆኑም፣ ቀላል ግጭቶች ከሆኑ፣በአቦገረብ አባልነት የሌሉ ታላላቅ አባቶች እና የተጣሉት ሰዎች የቅርብ ጓደኞች የሆኑት ጠቡን የማብረድ ድርሻ አላቸው፡፡

### 2.3.1. ትልቅ ሰው ወደአለበት ቤት መሄድ

በአሁኑ ጊዜ እየተዳከመ ቢሄድም፣ ባለፉት ጊዜያት ገዳይ ወይም ማንኛውም ጥፋት የፈፀመ ሰው መጀመሪያ ትልቅ ሰው ወዳለበት ቤት ነበር የሚሄደው፡፡

> ድሮ በእኛ ጊዜ አንድ ሰው ቢገድል ትልቅ ሰው ወደ አለበት ቤት ይሄድ ነበር፡፡ የትልቅ ሰው ቤት ስለሆነም ማንም አይደፍረውም፤ በወሬ ወሬ ገዳዩ እከሌ ቤት ገብቷል፣ ከተባለ ማንም አይነካውም፤ ትልቅ ሰው መድፊር እግዚአብሔርን እንደ መድፊር ይቆጠር ነበር፡፡ ዘንድሮማ እየገደለ ሰዎች ካዩት እጅ ከፍንጅ ይይዙታል፤ ሰው ካልነበረ ደግሞ ወደ ጫካው ይገባል፡፡ ግን ተፈልጎ ለሽማግሌዎች እጁን እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ አንድ አንድ ጊዜ ፖሊሶች ሲመጡ እንኳ እኛው ራሳችን ይዘንላችሁ እንመጣለን ብለን ቃል እንገባላቸዋለን

ይህ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔርን ከመፍራትና ለአካባቢው አባቶች ካላቸው አክብሮትና እምነት ነው፡፡ የሚች ወገኖች በአካባቢያቸው ያሉትን ሽማግሌዎች ምን ያህል እንደሚያምኗቸው ሲገልፁ፡-

"... ይሄ ምንድነው ካልከኝ ሰውን መፍራት፣ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ እኛም አናሳፋራቸውም፡፡ ኃላፊነት ተሰምቶን ለህይወታችን ጥሩ ነገር ሰርተን ማለፍ ነው የምንፈልገው፡፡ ሰው ለምን ይጣላል? ለምን ቂም በቀል ይስፋፋል? እግዚአብሔርንስ ለምን እናስቀይመዋለን?" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 25)፡፡

የተበዳይ ወገኖች ከሚፈሯቸው ግንባር ቀደም ነገሮች፣ የአካባቢው ሽማግሌዎችንና እግዚአብሔርን ነው፡፡ የአካባቢው ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ እምነት የተጣለባቸው ናቸው፡፡ የተበዳይ ወገኖች የሽማግሌዎቹን ምክርና ተግሳፅ የሻሩ እንደሆነ በአካባቢው በማህበረሰብ ይናቃሉ፤ ህዝቡ "ሽማግሌዎችን የማያከብሩ" በማለት ይሳለቅባቸዋል፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ በአካባቢው እምነት መሰረት ዕርቅ ከእግዚአብሔር ጋር ይያያዛል፡፡ አብሮህ ከሚኖር ሰው አለመታረቅ እግዚአብሐርን እንደማስቀየም ይቆጠራል፡፡ ከዚህም የተነሳ ህዝቡ ይቅር ባይና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

ጥፋተኛ የሆነው ግለሰብ በአካባቢው ካለው ትልቅ ሰው ቤት ይደበቃል፡፡ እሱ ብቻ ስለተደበቀ ግን ብቀላው አይቀርም፡፡ የጥፋተኛው የቅርብ ዘመድ የሆኑት ከተበዳይ ወገኖች ዓይን ራቅ ማለት አለባቸው፡፡ ግጭቱ እንደተከሰተ የገዳይ ቅርብ ዘመዶች የት መሄድ እንዳለባቸው አቶ እምባየ ደስታ እንዲህ በማለት ገልፀውልኛል፡፡

> "ከዛ በኋላ ከገዳይ ወገኖች በተለይ ወጣት የሆኑትን ለጊዜው ራቅ ብለው እንዲሸሽጉ እናደርጋለን፡፡ እ... ምክንያቱም የገዳይ ወገኖች ከሚች ወገኖች ዓይን ሲደበቁ ጥሩ ነው፡፡ ሰይጣንን ለማሸነፍ ብለን ነው እንደዚህ የምናደርገው፡፡ የገዳይ ወገኖች ለጊዜው ውርዴት መስሏቸው ወይም ትዕቢታቸውን ለማሳየት አንሸሽግም ሊሉ ይችላሉ፡፡ እኛ ግን በምክር እናሳምናቸዋለን" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 25)፡፡

ጥፋተኛው በህይወቱ ላይ ከሰጋና የመኖሩ ጉዳይ ካጠራጠረው ደግሞ በአካባቢው ካሉት ሽማግሌዎች ቤት ከመደበቅ ይልቅ ራቅ ወዳለው አካባቢ ሊሸሽ ይችላል፡፡

ጥፋተኛው መሸሹ ሲሰማ፣ የአካባቢው ሽማግሌዎች ከአቦገረብ በመመካከር የፖሊስ አካላትና የተወሰኑት አቦገረብ እንዲያፈላልጉት ይደረጋል፡፡ ጥፋተኛው እንደተገኘ፣ ምናልባት አልያዝምና እምቢ የማለት አዝማሚያ ካላሳየ በስተቀር በቀጥታ የአካባቢው አቦገረብ ወደ ሆኑት ይሄዳል፡፡ እንደየ ሁኔታው ወደ ፖሊስ ጣብያ ከተወሰደ በኋላ በአቦገረብ እንዲታረቅ ጠይቀው ይወስዱታል፡፡ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ(1) አባት ግድያን የፈጸመ የአንድ ሰው ታሪክ አንስተው ሲናገሩ እንደሚከተለው ብለውኛል፡፡

> ...ሰውየውን እንደተገደለ በነጋታው አፋር ገባ፤ ከእዛ በኋላ አቦገረብ የተወሰኑትን ወጣቶች በየአቅጣጫው አሰማርተው፤ እ... ሶስት ፖሊሶችም ከመንግስት እንዲሰጣቸው አቦገረብ ያዝዛሉ፤ ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው ገዳዩን የተገኘው፡፡ ጠጅ ቤት እያለ ነው የያዙት፤ ወዲያው ይዘውት መጡ፤ እ... ፖሊስ ጣብያ እንዲታሰር ተደረገ፡፡ ከእዛ በኋላ አቦገረብ ወዲያ ወዲህ እያሉ የዕርቁ ስነ-ስርዓት እንዲካሄድ አደረጉ (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 42) ፡፡

አውራ መረጃ አቀባዮቹ በብዛት እንደሚሉት ጥፋተኛው ራቅ ወዳለ አካባቢ ሄዶ የሚደበቅበት ምክንያት ለወደፊቱም ለመሰወር አይደለም፡፡ ለተበዳይ ወገኖች ካለው አክብሮትና እንዳይበቀሉት ካለው ፍራቻ የተነሳ ነው፡፡ ጥፋት ፈፅሞ በተበዳይ ወገኖች አቅራቢያ ከታየ በጥፋት ላይ ጥፋት መጨመር ነው፡፡ አይደለም የተበዳይን ወገኖች የአካባቢውን ህዝብም እንደ ናቀ ይቆጠራል፡፡ የተበዳይ ወገኖችም ምን ያህል ቢንቀን ነው ከዓይናችን የማይደበቀው በማለት ይበቀሉታል፡፡ የተበዳይ ወገኖችም በራሱ ላይ ወይም በቅርብ ዘመዶቹ ላይ ጥፋት ያደርሳሉ፡፡

### 2.3.2. በገዛ ፈቃድ አቦገረብ ወዳሉበት በመሄድ እጅ መስጠት

አንድ አንድ ሰዎች በአቦገረብ ላይ ካላቸው ከፍተኛ አመኔታ የተነሳ አቦገረብ እጅ ላይ ከሆንን ሁሉም ነገር ይስተካከላል በማለት ነገሩ እስኪረጋጋ አቦገረብ ወዳሉበት ይሮጣሉ፡፡

> "... እንዳቀራረብህ ነው፡፡ ለምሳሌ ገዳዩ መጀመሪያ አቦገረብ ወደ አሉበት ሄዶ እንዲህ ዓይነት ችግር ገጥሞኛል፤ ምን ላድርግ ብሎ አቦገረብን ያማክራል፡፡ አቦገረብም ዝም አይሉም፡፡ ለጊዜው መደበቅ ካለበት ይመክሩታል፡፡ አይዞህ እኛ ጋር መቆየት አለብህ ካሉትም እነሱ ጋር ይቆያል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አቦገረብ ጥሎ አይጥልም (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 44) ፡፡

በማለት ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ አባት ይናገራሉ፡፡

### 2.3.3. ራቅ ብሎ ወደ ሚገኘው ቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ መሄድ

ገዳዩ ለአቦገረብ እጁን መስጠትና በአካባቢው መደበቅ የሚጠራጠር ከሆነ ከገደለ በኋላ ወድያውኑ ከአካባቢው በመሰወር የቅርብ ዘመዶቹ ወይም ጓደኞቹ ወደ አሉበት በቀንም ሆነ በሌሊት ይጓዛል፡፡ ነገሩ ከበረደና አቦገረብ የዕርቁን ሁኔታ እያፋጠኑት መሆኑን ከሰማ በኋላ አቦገረብ ወይም ሌሎች የአገር ሽማግሌዎች እንዲወስዱት ያስልካል፡፡ ወይም ደግሞ አቦገረብ የት እንዳለ በመጠየቅ ሄደው ያመጡታል፡፡ ከዚህ በኋላ እንደየ ዕርቁ ደረጃ ከሟች ወገኖች ጋር ይታረቃሉ፡፡

ጥፋተኛው ወይም ገዳዩ ከተያዘ በኋላ ሽማግሌዎችና አቦገረቦች በጋራ በመሆን ወደ ሟች ዘመድ በመሄድ እንዲታረቁ ይለምኗቸዋል፡፡

ጥፋተኛው ወይም ገዳዩ ከአቦገረብ ጋር ከተገናኘ በኋላ አቦገረብ የዕርቅ ስርዓት የማፋጠን ስራ ይሰራሉ፡፡ የሟች እና የገዳይ ወገኖች በተመረጠ ስፍራ ለዕርቅ ያገናኟቸዋል፡፡ ከዛ በኋላ ሳይቀራረቡ ለየብቻ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል፡፡ የዕርቁ ፍፃሜ በሚካሄድበት ወቅት በብዛት በሜዳ ወይም ተራራ ላይ ቢሆንም፣ ከከተማ ወጣ ያለ ጠላ ወይም ጠጅ ቤት ድረስ በመሄድም እርቃቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

"በቂ ጊዜ ከሌላቸው ከመሐል ከተማው ገለል ብሎ በሚገኘው ጠላ ቤት ወይም ጠጅ ቤት ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ (ሚያዚያ 28፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 33) በማለት ወይዘሮ በለጠች መሐሪ ገልጸዋል፡፡

ይህ የመሆኑ ሁኔታ፣ ወይም አንድ አንድ ጊዜ ጠላ ቤት ወይም ጠጅ ቤት ላይ የመደረጉ ሁኔታ ከድሮ ጀምሮ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም ጊዜ ማጣት ነው፡፡

## 2.4 በሽምግልናው ስርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት አካላት

በሽምግልናው ስርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት አካላት እንደየ ግጭቱ ዓይነት ይለያያሉ፡፡ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉት ግጭቶች በተለያዩ አካላት ይታያሉ፡፡ ጠቡ ቀላል ከሆነ የተጣሉትን ሰዎች የቅርብ ጓደኞች፣ የሰፈር ወይም የመንደር የዕድሜ ባለፀጎች የሆኑት አባቶች ሊፈቱት ይችላሉ፡፡ በግጦሽ መሬትና፣ የደን ልማት በመሳሰሉ ነገሮች የተጋጩ እንደሆነ ደግሞ "ሀገር" ይዳኛቸዋል፡፡ የድንበር ግጭት፣ የግድያ፣ የከፋ

የቤተሰብ ጠብ እና ሌሎች ከባድ የሚባሉት ግጭቶች ከሆነ ደግሞ "አቦገረብ" እና "ድባርተ" በጋራ በመሆን ጠቡን ይፈቱታል፡፡

### 2.5. የአቦገረብ ምንነት

አቦገረብ ምን ማለት እንደሆነ በአጠቃላይ አውራ መረጃ አቀባዮቼ ተመሳሳይ ሐሳብ ቢሰጡኝም፣ በተወሰነ መልኩ ለየት የሚሉበትም አለ፡፡ አቶ እምባየ ደስታ አቦገረብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡፡

> አቦገረብ አሁን የወጣ ስም አይደለም፡፡ ለምሳሌ እኔ በእድሜኮ ከዘጠና በላይ አድርጌአለሁ፤ ይህን ስም ማን እንዳወጣው ግን አላውቅም፣ ምን ማለት ነው ካልከኝ ግን ግልፅ ነው፡፡ እ.... አቦገረብ የወንዝ አባት ማለት ነው፡፡ ወንዝ ማለት እንግዲህ አካባቢ እንደ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የወንዜ ልጅ ከተባለ፣ አብሮ አደጌ፣ ምንነቴን፣ ምንነቱን የምንተዋወቅ ማለት ነው፡፡ ወይ ደግሞ የምንዋደድ፣ የምንፋቀር ማለት ነው፡፡ አየህ... እና እንደዚህ ዓይነት ትርጉም ነው ያለው፡፡ እ... ሽማግሌዎቹ አቦገረብ ያሉበት ምክንያትም የአንድ አካባቢ የሆኑትን፣ አብረው ያደጉትን ሰዎች፣ አባቶች ማለት ነው፡፡ እንደ አባት ሆነው የተጣሉትን ያስታርቃሉ፤ እንደ አባት ሆነው እ... የተራቡትን ይረዳሉ፤ የታመመውን ያያሉ፡፡ ብቻ ሁሉም ነገር ያደርጋሉ ማለት ነው (ሚያዚያ 22፣2003፣ ስክርብ ገፅ 28)፡፡

ከአውራ መረጃ አቀባዮቼ አንዱ የሆነው መንገሻ ካሳም ስለ አቦገረብ ምንነት ሲናገር እንዲህ ይላል፡፡

> አቦገረብ ሲባል እንግዲህ ወደ አማርኛ ስታመጣው የወንዝ አባት ነው፡፡ የወንዝ አባት ማለት ደግሞ የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ማስተዳደር፣ ማስታረቅና ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ማለት ነው፡፡ የወንዜ ልጅ እንደሚባለው ዘፌን ዓይነት ነው፡፡ ብዙ ሳይራራቁ፣ ዕትብታቸው በአንድ አካባቢ የተቀበረ ሰዎች መቀያየም የለባቸውም ብለው የተነሱ አባቶች ናቸው፡፡ አቦገረብ እንግዲህ የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ የበላይ ሹም ናቸው፡፡ ሁለት ሰዎች ወይም ከዚያ በላይ ወንድማማቾችም ባዳዎችም ሊሆኑ ይችላሉ፣ እነዚህ አቦገረብ የምንላቸው አባትነት ተሰምቷቸው ለማስታረቅ የቆሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ አቦገረብ የአገር ሽማግሌዎች ናቸው (ግንቦት 2፣2003፣ ስክርብ ገፅ 48)፡፡

ከዚህ ብዙም ባልተለየ መልኩ አቶ ተላ ቓሺ አቦገረብ ምን ማለት እንደሆነ እንዲህ በማለት ነግረውኛል፡፡

"አቦገረብ ማለትማ እ… የአካባቢው ሰዎች ሲጋጩ ይቅር ለእግዚአብሔር የሚያባብሉ ማለት ናቸው። አቦገረብ የድሮ ስርዓት ነው። አባቶቻችን ሲጠቀሙት የነበረው ነው። እነሱ ደግሞ ለትውልዳቸው መተዳደሪያ ይሆናል፣ የተጣሉትን ያስታርቃል ብለው ያስተላለፉት ነው (ግንቦት 2፣2003፣ስክርብ ገፅ 55) ።

ወንዝ አዋሳኝ ሊሆን ይችላል፤ በአንድ ወንዝ አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ዘመዳሞችና በደም የተሳሰሩ መሆናቸውን ያምናሉ። እንደ አካባቢው ማህበረሰብ አመለካከት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች መጣላት የለባቸውም። ተደጋግፈው እና ተሳስበው መኖር አለባቸው።



ስእል 3 አቦገረብ በውይይት ወቅት(ሚያዚያ 22 በራያ አላማጣ ወረዳ )

## 2.6.. የድባርተ ምንነት

ድባርተ ከአቦገሬብ ተነጥሎ የሚታይ የዕርቅ ስርዓት አይደለም፡፡ በተለይም እንደ ግድያ፣ አካል የመጉዳት እና የድንበር በመሳሰሉት ከባድ የግጭት ዓይነቶች ድባርተ ከአቦገሬብ ጎን ለጎን በመሆን በተለያዩ ዘዴዎች ዕርቁን እንዲሳካ ያደርጋል፡፡

ድባርተ በግጭት ጊዜ ብቻ የሚደረግ ስርዓት አይደለም፡፡ ድርቅ ሲሆን፣ ያልታሰበ የወረርሽኝ በሽታ በአካባቢው ሲከሰት፣ በክረምት ወራት ዝናብ ሲያቋርጥ ወይም ደግሞ የጦርነትት ቅስቀሳ ሲኖር ድባርተ ተሰባስበው አምላካቸውን ይለምናሉ፡፡ ወይዘሮ በለጠች መሐሪ ድባርተን እንዲህ ይገልፁታል፡፡

"ድባርተ ማለት እ... ግጭት ሲፈጠር፣ በአካባቢያችን ያልታሰበ መከራ ሲወርድብን፣ እግዚአብሔር መዓቱን እንዲያነሳልን የምንለምንበት ነው፡፡ ራያ እንደ ድሮ አይደለም፡፡ አንድ አንድ ጊዜ ዝናብ እያጣን ነው፡፡ እኛ ደግሞ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን፣ እንደ በደላችን ሳይሆን በምህረቱ እንዲረዳን እንለምናለን" (ሚያዚያ 28፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 31) ፡፡

እምባየ ደስታ የድባርተ ምንነት ሲገልፁ፣

"ድባርተ ማለት እ... ምናለ መሰለህ ..እ... ልመና ማለት ይመስለኛል፡፡ ለድባርተ ወጡ ሲባል ተሰባሰቡ፣ ተራራ ላይ ወጡ ወይም ቤተክርስቲያን ሄዱ ነው፡፡ ስለዚህ ሴቶቹ የሚሰባሰቡት ለልመና ነው (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ 29)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ድባርተ ማለት ምን ማለት እንደሆነና በየትኛው ወቅት ምልጃና ልመና እንደሚያደርግ እምባየ ደስታ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

"ዝናብ ሲያቋርጥ፣ ድርቅ ሲሆን ጊዜ፣ ያልታሰበ በሽታ ሲመጣ፣ እ... የሰው ብቻ ሳይሆን የእንስሳት በሽታም ሲመጣ፣ አዲስ ሃይማኖት ሲመጣ፣ ችግር በገጠመን ጊዜ ድባርተ ይወጣሉ" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 27)፡፡

## 2.7. አቦገሬብ የሚመረጡበት መስፈርት

አቦገሬብ በምን መስፈርት እንደሚመረጡ አውራ መረጃ አቀባዮቹ የሆኑት አርሴ ማርየ፣ እምባየ ደስታ እና መንገሻ ካሳ በተከታታይ እንደሚከተለው ይላሉ፡፡

"ከየጎጡ እየተውጣጡ ይመረጣሉ፣ እና እንዴት ነው መሰለህ... ቀደም ብሎ የዕድሜ ባለጠጎች፣ ተወላጅ፣ ማለቴ... ጨዋ፣ እ... የፍርድ ልክ የሚያውቁ፣ የማያዳሉ

ይመረጡ ነበር። አሁን አሁን ግን ወጣቶችም እየመረጥን ነው" (ሚያዚያ 07፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 15) ።

"እ... እዚህ አካባቢ ያላደገ ከሆነ አይመረጥም... ሁሉም ሰውኮ አይሆንም።ማለቴ አሁን ከሌላ አገር የመጣ፣ በማህበረሰቡ ተቀባይነት የሌለው ሰው አይመረጥም። ህዝቡ የመረቀው መሆን አለበት፣ አሁን ምናለ መሰለህ እ... በዕድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ይመረጣሉ፤ በድባርተም አቦገረብም ማለቴ ነው። (ሚያዚያ 22፣2003፣ ስክርብ ገፅ 29) ።

"... የሚመረጡት ባላባት መሆን አንድ ነገር ነው። ለምን ባላባትነት ተመረጠ ካልከኝ እ... እንደኛ ከወገን አንፃር፣ ሁለተኛ ደግሞ ከማህበረሰቡ እምነትና ተቀባይነት፣ እ.... ከተደማጭነት አንፃርም ነው የሚታየው" (ግንቦት 02፣2003፣ ስክርብ ገፅ 46) ።

ጠቅለል ባለው መንገድ ሶስቱም አውራ መረጃ አቀባዮቹ እንደተናገሩት አቦገረብ ለመሆን መመዘኛ ወይም መስፈርት ያስፈልጋል። ከመስፈርቶቹ መካከል ባላባት (ተወላጅ) መሆን፣ የዕድሜ ባለጠጋ መሆን፣ ጨዋ እና የፍርድ ልክ ማወቅ፣ አለማዳላት እና በአካባቢው ህዝብ መመረቅ (ተቀባይነት ማግኘት) በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው።

## 2.8.አቦገረብ የሚቆዩበት ጊዜ

አቦገረብ የሚቆዩበት ዘመን ገደብ የለውም። የዕድሜ ባለ ጸጎች እስኪደክማቸው እና መስራት እስኪያቅታቸው ማገልገል ይችላሉ። በመሀል ማህበረሰቡ የማይወደው ስራ ወይም ሚዛናዊነት የጎደለው ፍርድ የሚሰጡ ከሆነ ግን በህዝብ ፊት ተወቅሰው ይወርዳሉ።

በአካባቢው ማህበረሰብ ለዳኝነት አይበቁም ተብለው በመስፈርትነት የሚቀሩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ጨዋ[11] እና ባላባት[12] ያልሆኑት ናቸው። ባላባት ወይ የአካባቢው ተወላጅ ካልሆነ ያዳላል፤ ወይም ፍርድ ያጎድላል ተብሎ አይመረጥም። የአካባቢው ተወላጅ ከሆነ ግን አብሮት ያደገ ህዝብ ስለሆነ፣ ለሁሉም የማህበረሰቡ ክፍሎች በእኩልነት ያገለግላል የሚል እምነት አላቸው (ስክርብ ገፅ 16፣49)።

---

[11] ጨዋ በሁለት መንገድ ሊፈታ ይችላል። ጨዋ በአንድ በኩል የነገር ልክ የሚያውቅ ወይ አስተዋይ አእምሮ ያለው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት በዘሩ የማይታማ ማለት ነው።(በአላማጣ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት አቶ መንገሻ ካሳ ስክርብ ገፅ 51)

[12] ባላባት ማለት በአከባቢው እምነት ተወላጅና ዘመደ ብዙ የሆነ ሰው ይገልፃል፡፡ (ምንጭ ከራሴ)

ማዕቀብ የሚደረግባቸው ምክንያት "ጨዋ መሆን"የሚሉት ግልፅ ባይሆንም ባላባት መሆን የሚመረጥበትን ምክንያት ግን መንገሻ ካሳ እንደሚከተለው ገልጾልኛል፡፡

> አንድ ሰው ምሁር ስለሆነ ብቻ አያምኑትም፤ ወይም ሊያስተዳድረን ይችላል ብለው አያምኑም፡፡ ከአንድ ምሁር ይልቅ የአካባቢ ተወላጅ የሚመርጡበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምን ቢባል እ... የማህበረሰቡ ባህል፣ ቋንቋ እና እምነት እንዲሁም እነዚህ ማህበራዊ እሴቶች የምንላቸው፣ የማህበረሰቡ አኗኗር ሳይቀር የሚያውቀው መሆን አለበት፡፡ ሌላ ባላባትነት የሚመረጥበት ምክንያት፣ ባላባት ከሆነ ማህበረሰቡ በብዛት ዘመዶቹ ይሆናሉ፡፡ በፍርድ ጊዜ ወይም በዳኝነት ጊዜ ማዳላት አይኖርም፡፡ ጥሩ ነገር ሰርቶ ስላለፈ እ... ወይ ሚዛናዊነት የጎደለው ፍርድ ከሰጠ ተወቃሽነትን ያተርፋል፡፡ እስከ ሰባት ትውልድ ሊያሰድብ ይችላል፡፡ እስከ ሰባት ትውልዱ አሰደበ ማለት ደግሞ በተዘዋዋሪ እሱም ተወላጅ ወይ ባላባት ስለሆነ ይደርሰዋል (ግንቦት 02፣2003፣ ስክርብ ገፅ 49)፡፡

መንገሻ እንደተናገረው በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ባላባት መሆን ተመራጭነት አለው፡፡ ለዳኝነት የታጨው ወይም የተመረጠው ሰው የአካባቢው ተወላጅ ከሆነ፣ የአካባቢው ህዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዝምድና ስለሚደርሰው የማዳላት ስራ አይሰራም፡፡

የአካባቢውን አኗኗር፣ ቋንቋ፣ ባህልና እምነት፣ እንዲሁም የማህበረሰቡን ባህርይ ማወቅ ረገድ ደግሞ ባላባትነትን ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

## 2.9 የመዋቅሩ ሁኔታ በአሁኑ ሰዓት

በራያ አላማጣ ወረዳ የባህላዊ ዕርቅ ስርዓት መዋቅር በተወሰነ መልኩ የመቅረት አዝማሚያ ቢያሳይም ፣ በአብዛኛው ግን እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በመዋቅሩ ላይ ድሮ የነበሩት አሁን ግን ቀሩ የሚባሉት ክፍሎች አውራ መረጃ አቀባዮቼ የሚከተሉትን ተናግረዋል፡፡

በገፅ 19 እንደተጠቀሰው አቶ አርሴ ማርየ አንድ ግጭት ተከስቶ ጉዳዩ መጀመሪያ የት ይሄዳል? የሚለውን ጥያቄ ሲመልሱ እንዲህ ይላሉ፡፡

> ድሮ በእኛ ጊዜ አንድ ሰው ቢገደል ትልቅ ሰው ወዳለበት ቤት ነበር ሮጦ የሚሸሸገው፡፡ ምክንያቱም ትልቅ ሰው ያለበት ቤት ከሆነ ማንም አይደፍረውም፤ በወሬ ወሬ ገዳዩ እከሌ ቤት ገብቷል ከተባለ ማንም አይነካውም፣ ትልቅ ሰው መድፈር እግዚአብሔርን እንደ መድፈር ይቆጠር

ነበር፡፡ ዘንድሮማ እየገደለ ሰዎች ካዩት እጅ ከፍንጅ ይይዙታል፡፡ ሰው ካልነበረ ደግሞ ወደ ጫካው ይገባል (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 2)፡፡

አቶ አርሴ ማርየ እንደሚሉት የድሮና የአሁኑ የዕርቁ መዋቅሮች ይለያያሉ፡፡ በተወሰነ መልኩ ተለውጧል፡፡ ነገር ግን ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቱ የበለጠ እየተጠናከረ መሆኑን አብዛኞቹ አውራ መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ፡፡

በዕርቅ ስርዓት መዋቅር ላይ ሌላው እየተዳከመ ነው የሚባለው ዕርድ ነው፡፡ የተወሰኑት አውራ መረጃ አቀባዮች የዕርድ ስርዓት እየቀረ ነው ቢሉም በብዛት እንደሚሉት ግን የዕርድ ስነ-ስርዓትም እየቀጠለ መሆኑን ነው፡፡ የዚህም ምክንያት በኑሮ ውድነት ነው፡፡ ከኑሮ ውድነት የተያያዘ በሬ ማረድ እየተዳከመ ቢሆንም፣ በግና ፍየል ማረድ ግን እየቀጠለ ነው፡፡ አርሴ ማርየ የዕርድ ጉዳይ ሲናገሩ÷

"በተለይም አሁን አሁንማ ቀርቷል ማለት ይቻላል፡፡ የሚች ወገኖች ከሚከሱት ገንዘብ በተጨማሪ ሌላ እያወጡ ስለሆነ የለም" (ሚያዚያ 07፣2003፣ ስክርብ ገፅ 20)፡፡


÷

ስእል 4 አጥኚው አውራ መረጃ አቀባዮቹ ከሆኑት ሲወያይ:: ከግራ ወደ ቀኝ አለማየሁ ፣ሃፍቱ፣ አቶ አርሴ ማርዬ እና መንገሻ ካሳ::

በተመሳሳይ መልኩ እምባየ ደስታ በአሁኑ ሰዓት በዕርቅ ስነ-ስርዓት ላይ የሚታረድ መሆኑንና አለመሆኑን እንዲህ በማለት ይናገራሉ።

"ዘንድሮ እንደ ድሮ አይደለም። ድሮ የከብት ዋጋ እንዳሁኑ አይደለም። ድሮ ሁሉም ነገር ርካሽ ነበር። እና እስከ አምስት በሬ ለዕርቅ ይታረድ ነበር። ዘንድሮ ግን እንደሚታወቀው ነው። አይደለም በሬ፣ ፍየልና በግም ከመጠን በላይ ተወዷል። እንደየሁኔታው ሁለት ፍየል ወይም ሁለት በግ፣ አልፎ አልፎም አንዲት በግ ወይ ፍየል ትታረዳለች (ሚያዚያ 22፣2003፣ ስክርብ ገፅ 24)።

አቶ አርሲ ማርየ እና አቶ እምባየ ደስታ አሁን አሁን የዕርድ ስርዓት እየተካሄደ አይደለም ይላሉ። የዚህም ምክንያት አንዱ በንሮ ውድነት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ለዕርድ የሚሆን እንስሳ የሚያቀርቡ የሚች ወገኖች ስለሆኑ፣ ከካሳ ተጨማሪ ሌላ እዳ እየሆነባቸው ነው ከሚለው የተነሳ ነው። ሌሎች መረጃ አቀባዮች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ የዕርዱ ሁኔታ እየቀጠለ መሆኑንና በብዙ አካባቢዎች እየተተገበረ እንደሆነ ይናገራሉ።

ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ(1) አውራ መረጃ አቀባዬ ስለዕርድ ስነ-ስርዓት ሁኔታ እንዲህ በማለት ነግረውኛል።

"በተለይ የግድያ ዕርቅ ከሆነ ድግስ ይካሄዳል። እንደየ ሀብት መጠናቸው ያርዱና ለተሰበሰበው ህዝብ ያበሉታል። ብዙ ህዝብ እኮ ነው የሚሰባሰበው፣ የገዳይ ወገኖችና የአካባቢው ህዝብ በመተባበር ሃይለኛ ግብዣ ተዘጋጅቶ ብሉ ጠጡ ይባባል፤ የእነሱ መታረቅ ደስታቸው ስለሆነ፣ ተደስቱ እየተባባለ ይደገሳል" (ሚያዚያ 11፣2003፣ ስክርብ ገፅ 46)።

ስለዚህ መዋቅሩ በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። በዕርድ ስነ-ስርዓት ላይ የመቀነስ አዝማሚያ ቢታይም ስርዓቱ ግን አልተዳከመም ማለት ይቻላል።

## 3. የራያ አላማጣ ብሔረሰብ ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸው ሂደቶች (Procedures)

### 3.1 ግጭት እንደተከሰተ መጀመርያ የሚኬደው ቦታ

አንድ ግጭት ሲከሰት የሚሰማውና በተቻለው መጠን ነገሩን ለማረጋጋት የሚሞክር ሲጋጩ አይቶ ቶሎ የደረሰ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩን ለማጣራት ቅድሚያ ጠቡን የተመለከቱ ሰዎች ቤት ይኬዳል፡፡ ከዛ በኋላ ያለው ነገር ግን እንደየ ግጭቱ ዓይነት ይለያያል፡፡ አቶ ፍርዱ እምባየ ግጭት እንደተከሰተ መጀመሪያ ማን ያየዋል ለሚለው እንዲህ ብሎውኛል፡፡

> እሱንማ እ... እንደየ ግጭቱ ዓይነት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ቀላል ጠብ ከሆነ አቦገረብ ሳያዩት ይችላሉ፡፡ እ... እናቶች ወይም አባቶት ሊያስታርቋቸው ይችላሉ፡፡ እነዚህ ያልፈቱት አንደሆነ ደግሞ ጎረቤት ያየዋል፡፡ እንደህ እያለ ነው አቦገረብ ድረስ የሚሄደው፡፡ እ... አንድ አንድ ጊዜማኮ አቦገረብ የማይፈቱት ግጭትም አለ፡፡ አቦገረብ የማይፈቱት ከሆነ ግን ሳይወድ በፖሊስ ተጣርቶ ፍርድ ይሰጠዋል (ሚያዚያ 19፣2003፣ ስክርብ ገፅ 38)፡፡

ግጭቱ የአካል ጉዳት እና ሌሎች ችግሮች ካላደረሰ ቀድመው የተገኙት ገላጋዮች ሊያስታርቋቸው ይችላሉ፡፡ ካልሆነ ግን የተጣሉትን ሰዎች የቅርብ ጓደኞች ወይ በቅርብ የተገኙት አባቶች ወይ እናቶች ያስታርቋቸዋል፡፡ እነዚህ ካልቻሉ ደግሞ ከጎረቤት ደህና የሚባሉት ሰዎች ተመርጠው እንዲያግባቧቸው ይደጋል፡፡ በዚህም ሁኔታ ያልተቻለ አንደሆነ ግን አቦገረብ ያዩታል፡፡ አቦገረብ ጥፋተኛው ማን እንደሆነ በተለያዩ ዘዴዎች ነገሩን ይመረምራሉ፡፡

ግጭት እንደተፈጠረ ለሚመለከታቸው የአገር ሽማግሌዎች የሚናገሩ ወይ የዕርቁ ሂደት ለማፋጠን የሚያስተባብሩ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑት ቅን ሰዎች ናቸው፡፡ ነገሩ እንዳይባባስና የተጋጩትን ሰዎች የቅርብ ዘመድ የሆኑትን ነገሩን ሰምተው ይበልጥ እንዳያባብሱት ያስታርቃሉ ተብለው ለታመነባቸው ሰዎች ቶሎ በሚስጢር ይነገራቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ አቦገረብ ድረስ የቀረበ እንደሆነ ግን ጥፋተኛውን ለማወቅ ይመረመራል፡፡

አቦገረብም ለድባርተ ቶሎ በማሳወቅ የሚቹ ዘመዶች እንዲለመኑ ያደርጋሉ፡፡ ይህንን አስመልክተው ወ/ሮ በለጠች መሐሪ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

"ይሄ ነገር እንደተፈጠረ ከሟቹ ዘመድ ቤት ሄደን፣ ወይም ሚስቱ እና ልጆቹ ወዳሉበት ሄደን እግዚኦ እንላለን። ገዳዩን ያታለለው ሰይጣን እናንተን እንዳያታልላችሁ እያልን እንለምናለን። ምህላችንን እናቀልጠዋለን" (ሚያዚያ 28፣2003፣ ስክርብ ገፅ 32)።

ቀላል ግጭት ከሆነ፣ ጥፋተኛው ማን እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አይፈጅባቸውም። እዚያው ጠይቀው እዚያው ይፈቱታል። ከባድ የአካል ጉዳት እና እስከ ግድያ የደረሰ ጠብ ከሆነ ግን በግጭቱ ጊዜ መጀመሪያ የደረሱ ሰዎች ተጠርተው አቦገረብ ወደ አሉበት በመሄድ ጥፋቱን ይመረምሩታል።

በተለይም በአሁኑ ጊዜ አካል ላጎደለ ይሄን ያህል የገንዘብ ቅጣት፣ ሰው ለገደለ ይሄን ያህል የገንዘብ ቅጣት፣ በማለት በፅሑፍ ስላሰፈሩት ብዙ የሚያስቸግር አይደለም። ቅጣቱ ምን ያህል እንደሆነ አቦገረብ ከወሰኑ በኋላ ግን ወደ ዘመናዊው ህግ በመሄድ ያስታውቃሉ። አቦገረብ በጥፋተኛው ላይ ቅጣት ከወሰኑ በኋላ ለዘመናዊው ህግ እንደሚያስታርቁ አቶ ብርሃኑ አበራ እንደሚከተለው ብለውኛል።

> ለምሳሌ የግድያ ዕርቅ ሲደረግ አቦገረብ ፍርድ ቤት ድረስ መጥተው በአገር ሽማግሌ ወይም በአቦገረብ ህግ አስታርቀናቸዋል ብለው ካመለከቱ ተቀብሎ ያጸድቅላቸዋል። ስለዚህ የአገር ሽማግሌዎች ከተስማሙ መንግስት አይቃወምም። የአገር ሽማግሌዎች በወሰኑት ውሳኔ ወይም ቅጣት መሰረት ዕርቁ ይፈፀማል። ወይ ደግሞ የአገር ሽማግሌዎች የማይስማሙ ሲሆን፣ በሉ ህግ ይዳኛችሁ፤ በበኩላችን የምንችለው ይሄን ነው በማለት እ... ግጭቶችን ይፈታሉ ማለት ነው (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 10)።

### 3.2 ግጭቱን የመመርመር ሁኔታ

በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ግጭቱን መመርመር የሚጀመረው ጠቡ ከተከሰተ ከመጀሪያው ቀን ጀምሮ ነው። ግጭቱን የሚመረምሩበት ቦታ በብዛት በሰፈር ውስጥ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ገላጋዮችን በመጥራት ነው። በመጀመሪያ ሽማግሌዎቹ ወይም አቦገረብ የተጣሉትን ሰዎች ጠርተው የጠባቸውን መንስኤ ለየብቻ ይጠይቋቸዋል። የሁለቱም ጠበኞች ሐሳብ ከተቀበሉ በኋላ ነገሩን ይበልጥ ለማረጋገጥ ጠቡ ሲከሰት የነበሩት ወይም ያዩ ሰዎች በመጥራት ያነጋግራሉ።

አንድ አንድ ጊዜ ግን ጥፋተኛው ራሱን የሚያጋልጥበት ወይም ጥፋተኛነቱን አስቀድሞ የሚናገርበት ሁኔታ አለ። ጥፋተኛው ካመነ ብዙ ውጣ ውረዶች አይኖሩም። ጥፋተኛው የሚባለው ቅጣት ተቀጥቶ ነገሩን ቶሎ በባህላዊ የእርቅ ስርዓት እንዲቋጭ ይደረጋል።

## 3.3 ሽማግሌዎቹ ወደ ውሳኔ የሚያመሩበት መንገድ

አቦገረብ የጠበኞችን ጥፋተኛነት፣ ግጭቱ ሲከሰት ከነበሩበት ሰዎች እና ጠበኞቹ እራሳቸው ከሰጡት ሐሳብ በመሳት ወይም በተለያዩ መረጃዎች ተመርኩዘው በአቦገረብ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ወይም በራሳቸው ስምምነት ጥፋተኛውን ይቀጣሉ።


ጥፋተኛው ወይም ገዳዩ ካሳ መክፈል የማይችል ከሆነ በአቦገረብ ወይም በገዳዩ የቅርብ ዘመዶች አማካኝነት ከ"ሀገር"[13] ገንዘብ እንዲዋጣ ይደረጋል። ገዳዩ የተወሰነለትን የካሳ መጠን ከያዘ በኋላ የዕርቅ ስርዓት ይካሄዳል።

## 3.4 የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት

### አቦገረብ ውሳኔያቸውን ለባለጉዳዮቹ የሚያሰሙበት መንገድ

ጥፋተኛው ማን እንደሆነ የሚመረመረው ለዕርቅ በተመረጠው ቤት፣በትንሽ ተራራ ላይ፣ወይም ደግሞ ዛፍ ስር ሲሆን ይችላል። መርማሪዎቹም በብዛት አቦገረብ ሲሆኑ፣ የተወሰኑት ደግሞ ካገር ሽማግሌዎች (የዕድሜ ባለ ጸጎች) እና ከድባርተ ይገኙባቸዋል። የውሳኔው ጉዳይ በአቦገረብ የሚነገር ሲሆን ይህም በዕርቅ ጊዜ ነው።

[13] "ሀገር" በአካባቢው አጠራር ሁለት ትርጉም አለት። "ሀገር" በአንድ በኩል ግጭቱ በተከሰተበት አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ ሲሆን፣ ሀገር በሌላ በኩል ደግሞ በግጦሽ መሬት ምክንያት የተጣሉትን አቦገረብ ከማየታቸው በፊት ለማስታረቅ የሚቀመጡት ተወካዮች ናቸው በማለት በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ተገልጋይ የሆኑት እና በራያ አላማጣ የሚኖሩ አቶ መንገሻ ብርሃኑ ገልጸዋል።



ስእል 5 ጥፋተኛ ከአቦገረብ ውሳኔ ሲቀበል

## የዕርቅ ስርዓት የሚካሄድበት ቦታ

እንደ አቶ እምባየ ደስታ አባባል ለዕርቅ የሚሆን ቦታ ይመረጣል። ሆኖም የድሮ እና የአሁን ለዕርቅ የሚሆን ቦታ የአመራረጥ መንገድ የተለያየ መሆኑን እንዲህ ይላሉ

"ድሮ አዎ ትላልቅ ዋንዛዎች እና ወይራዎች ነበሩ። ስለዚህ ከፀሐይም ከዝናብም ለመዳን ተጠልለን ነበር የምናስታርቀው፤ ዘንድሮ [በአሁኑ ሰዓት] የለም፣ አልታደላችሁም፤ በየሜዳው፣ በየተራራው፣ አሁን አሁንማ ገለል ያለ ጠጅ ቤት ወይም ጠላ ቤት መርጠን እያስታረቅን ነው" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 25)።

ዘንድሮ በራያ አላማጣ አካባቢ ትላልቅ ዋንዛዎች እና ወይራዎች ባለመኖራቸው የተነሳ በየሜዳው፣ በየተራራው ወይም ገለል ባለ ጠጅ ቤት የዕርቅ ስርዓት እየተካሄደ ይገኛል።

በግድያ ዕርቅም ሆነ በሌላም የግጭት ዓይነቶች ዕርቅ ሲደረግ ከአቦገረብ ጎን ለጎን በምህላና በጸሎት ድባርተ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ድባርተ ለምህላ ወይም ለጸሎት ሲወጡ የአካባቢው ሁሉም ሴቶች ማለት ይቻላል ይሰበሰባሉ፡፡ ስለዚህ የሟች ዘመድ ሴቶችም ለድባርተ ስለሚወጡ፣ ለጸሎቱ ተማርከው ለዕርቁ እንዲቀርቡ ያደርጋሉ፡፡

ከዋናው የዕርቅ ቀን በፊት ድባርተ ፈጣሪያቸውን ለመለመን የሚወጡ ሲሆን፣ በዋርካ ስር ወይም በተራራ ላይ ሆነው ይፀልያሉ፡፡ ወ/ሮ በለጠች መሐሪ ለድባርተ የሚሆን ስፍራ ምን አይነት እንደሆነ ሲገልፁ÷

## በዕርቅ ስርዓት ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች

በዕርቅ ስርዓት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚገኙ መሆናቸውን፣ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ (1)የ63 ዕድሜ አዛውንት እንዲህ በማለት ነግረውኛል፡፡

"በዕርቅ ጊዜ አንተ ልጅ ነህ፣ እርስዎ ትልቅ ነዎት ተብሎ የሚቀር የለም፡፡ ህፃናት ቢሆኑ እንኳ ከዚህ ዓይነት ድርጊት እየተማሩ ማደግ አለባቸው፤ ህዝቡ ቢበዛ ደግሞ የዕርቁ ስርዓት የደመቀ ይሆናል" (ሚያዚያ 11፣ 2003፣ ሰክርብ ገፅ 46)፡፡

ስለዚህ በዕርቅ ስርዓት ጊዜ ሁሉም ሰው መካፈል ይችላል፡፡ መገዳደል ወይም እርስ በርስ መጋጨት መጥፎ መሆኑ ታውቆ ባህላዊ ዕርቅ ማድረግ ደግሞ ጠቃሚና በአካባቢው ማህበረሰብ ሰላምና ፍቅርን እንዲነግስ የሚያደርግ መሆኑን ታምኖበት ሁሉም እንዲያየው ይደረጋል፡፡

## በዕርቅ ስርዓት ጊዜ የሚታረደው ዕርድ

በዕርቅ ስርዓት ጊዜ የተወሰኑት መረጃ አቀባዮች ዕርድ የመኖሩ ጉዳይ ቢያጠራጥራቸውም፣ በብዛት ግን እንደሚታረድ ይጠቁማሉ፡፡ የሚታረደው የእንስሳ ዓይነት ግን እንደ ገዳይ ወገኖች ሀብተገነት ሊለያይ ይችላል፡፡ ደህና ኢኮኖሚ ያላቸው በሬ (በሬዎች) ማረድ የሚችሉ ሲሆኑ፣ የሌላቸው ደግሞ በግ ወይም ፍየል ማረድ እንደሚችሉ እምባየ ደስታ፦

"ዘንድሮ እንደ ድሮ አይደለም፡፡ ድሮ የከብት ዋጋ እንዳሁኑ አይደለም፡፡ ድሮ ሁሉም ነገር ርካሽ ነበር፡፡ እና እስከ አምስት በሬ ይታረድ ነበር፡፡ ዘንድሮ ግን እንደሚታወቀው ነው፡፡ አይደለም በሬ ፍየልና በግም ከመጠን በላይ ተወዷል፡፡ እና እንደየ ሁኔታው ሁለት ፍየል ወይ ሁለት በግ፣ አልፎ አልፎም አንዲት በግ

ወይም ፍየል ትታረዳለች" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 24) ብለው ይናገራሉ፡፡

ጠበኞች ድጋሚ እንዳይጣሉና ከታረቁበት ቀን ጀምሮ በመካከላቸው ወንድማማችነት እንዲነግስ ከተደረገ በኋላ የእርድ ሁኔታ በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል፡፡ አንደኛው እርድ በዕርቅ ስርዓት፣ ማለትም የገዳይና የሟች ወገኖች ለሚያደርጉት የዕርቅ ክዋኔ ተብሎ የሚታረድ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጠበኞቹ ከተታረቁ በኋላ የሟች እና የገዳይ ወገኖች በጋራ እየተደሰቱ ለሚበሉት ተብሎ የሚደረግ ግብዣ ነው፡፡

የገዳይ እና የሟች ወገኖች ለሚያደርጉት የዕርቅ ክዋኔ ተብሎ የሚታረድ እርድ አቶ እምባየ ደስታ ትርጉም እንዳለው ሲናገሩ

> "... እንዴታ! በግ ከታረደች፣ የሞተው ሰውየ የዋህ ነበር፤ ቅንና የተባረከ ነበር፡፡ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ፍየል ከሆነች የታረደችው ደግሞ፣ ገዳዩ ሰይጣን አሳስቶት ሰው ገድሏልና በፍየሉ የተመሰለው ሰይጣን ይታረድ የሚል ትርጉም አለው፡፡ እ.. እንዲህ ነው ነገሩ፡፡ ይህ ዓይነት ምሳሌ ከየት የመጣ ነው ብትለኝ ከድሮ ከአባቶቻችንና ከመፅሐፍ ቅዱስ ነው" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 24) ይላሉ፡፡

በዕርቅ ጊዜ ማንኛውም የእንስሳት ዓይነት ሲታረድ አራጁ ከገዳይ ወገኖች ነው፡፡ የገዳይ ወገኖች የሚያርዱበት ምክንያት አቶ እምባየ ደስታ

"ከገዳይ ወገኖች የቅርብ ዘመድ የሆነ ነው የሚያርደው፤ ምክንያቱም በሰይጣንም ሆነ በየዋህነት ደም ያፈሰስን እኛው ነን ማለት ነው፡፡ የሟች ወገኖች በፍፁም አይነኩም፡፡ ከዛ በኋላ በሟች እና በገዳይ ወገኖች በታረደው በግ ወይም ፍየል ደም እየተረጨ ይቅር ይባባላሉ" (ሚያዚያ 22፣2003፣ ስክረብ ገፅ 24) በማለት ያስረዳሉ፡፡

አቶ እምባየ ደስታ የዕርዱ ዓይነት ምን ዓይነት ማህበረሰባዊ እምነት እንደሚወክል፣ የገዳይ ወገኖች አራጅ የመሆናቸው ሚስጢር፣ እንዲሁም ደም ከፈሰሰ በኋላ ምን እንደሚደረግ በሚገባ አብራርተዋል፡፡ አክለውም ደሙ ወደ ሟች እና ገዳይ ወገኖች ለምን እንደሚረጭ ሲያብራሩ "ያጣላን እርኩስ መንፈስ ደሙ እንደዚህ ይረጭ ነዋ" (ገዞ. ከማሁ) ይላሉ፡፡

## የዕርቁ ስርዓት የሚያጠናክሩ ጸሎት፣ ምርቃት፣ እርግማን ወዘተ፣

በዕርቅ ስርዓት ጊዜ በሃይማኖት አባቶችም ሆነ በአገር ሽማግሌዎች (አቦገረብ) የሚደረጉ እርግማኖች፣ ምርቃት እና ጸሎት አሉ፡፡ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ(1) አዛውንት ቀሳውስት እንደሚመርቁ እንደሚከተለው ነግረውኛል፡፡

"ይህ የሚፈሰው ደም የዕርቃችሁ ምልክት ነው፡፡ እርኩስ መንፈስ አሸንፉት፡፡ ተዋደዱ እንጂ እርስ በርሳችሁ አትጣሉ፣ ምናምን እያሉ ይመርቃሉ" (ሚያዚያ 11፣2003፣ ስክርብ ገፅ 46)፡፡

ይህ ዓይነት ምርቃት የሟች እና የገዳይ ወገኖች ከታረቁ በኋላ በቀሳውስት የሚሰነዘር መፅሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ልማዳዊ የማስማማት ስርዓት ነው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው፣ የሽማግሌዎች እና የሃይማኖት አባቶች ጉልበት ስመው ከታረቁ በኋላ እንደየ ሁኔታው በገዳይ ወገኖች ቤት ወይም በታረቁበት ስፍራ በመሆን ድግስ ተደግሶ ይጨፈራል፡፡ አሁንም ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ አዛውንት÷

"በተለይ የግድያ ዕርቅ ከሆነ ድግስ ይካሄዳል፡፡ እንደየ ሀብተገነታቸው ያርዱና ለተሰበሰበው ህዝብ ያበሉታል፡፡ ብዙ ህዝብ እኮ ነው የሚሰበሰበው፤ የገዳይ ወገኖች እና የአካባቢው ህዝብ በመተባበር ሃይለኛ ግብዣ ተዘጋጅቶ ብሉ ጠጡ ይባላል፤ የእነሱ መታረቅ ደስታችሁ ስለሆነ ተደሰቱ እየተባለ ይደገሳል" (ዝኒ ከማሁ፣ ስክርብ ገፅ 46)፡፡

ስለዚህ በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች እንዲሁም በአካባቢው ማህበረሰብ አመለካከት የሟች እና የገዳይ ወገኖች ሲታረቁ ታላቅ ደስታ ይሆናል፡፡ የደስታ መገለጫም በጋራ መብላት እና መጠጣት ስለሆነ ከገዳይ ወገኖች እና የአካባቢው ህዝብ ለግብዣቸው የሚሆን ገንዘብ ወይም እህል ተሰብስቦ ይደገሳል፡፡ የሟች ወገኖች ለድግስ የሚሆን ገንዘብ ወይም እህል፣ ወይም ደግሞ ቁሳቁስ የማያዋጡበት ምክንያት ግን በበደላቸው ላይ ሌላ ተጨማሪ ጫና ማድረግ ጥሩ አይደለም፤ ከሚለው የአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ነው፡፡

## 3.5 አቦገረብ እና ድባርተ ወይም የአገር ሽማግሌዎች የወሰኑትን ተሚጋቾች እንዲቀበሉና በተግባር እንዲተረጉሙ የሚያደርጉበት መንገድ

### 3.5.1 በታቦት እንዲምሉ ማድረግ

በራያ አላማጣ አካባቢ እና የህዝቡ ማስተዋወቂያ ላይ እንደተገለጸው አብዛኛውን የአካባቢው ህዝብ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነው። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የራሳቸው "ቃልቾች"[14] ስላሏቸው በራሳቸው ባህላዊ ህግ ይተዳደራሉ፣ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችም እንዲሁ በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ይጠቀማሉ። ለክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች "ታቦት"[15] ትልቅ ቦታ አለው።

ባህላዊ ተቋማቱም፣ ጠበኞቹን ወይም ተሚጋቾቹን በታቦት እንዲምሉ ያደርጓቸዋል። ስለዚህ ጉዳይ አቶ ፍርዱ እምባየ የሚያውቋቸው ሰዎች በሚታረቁበት ወቅት ከታዘቡት እንደሚከተለው ነግረውኛል።

"...ከዛ በኋላ የተጣሉትን ሰዎች ታርቀው፣ በሽማግሌዎች ፊት ዳግመኛ የተጣሉ እንደሆነ የሚካኤል ታቦት ይቅር አይበላቸው፣ ያሳደጋቸው ህዝብም ክብር አይሰጣቸው ተብለው ታረቁ" (ሚያዚያ 19፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 39)።

---

14 [illegible] ። የራያ ክርስትያን ማህበረሰብ ግጭትን ለማብረድ አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች እንደሚጠቀም ሁሉ የራያ ሙስሊም ማህበረሰብም ቃልቾች ጠብን የሚያበርዱ አባቶች አድርጎ ይጠቀምባቸዋል።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በውጪ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ የተመረቀው ልሳነ ብዙ የሆነው አብርሃም ሃይለስላሴ ቃልቻ"ቃሉ " ከሚለው የኦሮምኛ ቃል የወጣ ሲሆን አማኞች ወይም የአምላክ ተከታዮች ናቸው በማለት ይገልፃል። በራያ ማህበረሰብ ቃልቾች አስታራቂ የአገር ሽማግሌዎች የሆኑበት ምክንያትም ካላቸው ክብር ወይም ከታማኝነታው አንፃር በመነሳት የመሰላል ።

15 በመፅሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 25 ቁጥር 10 ላይ ተጽፎ የሚገኘውን ማለትም "ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን።" የተባለለትን መስሎ የሚሰራ በክርስትና( ኦርቶዶክስና ካቶሊክ) አሁንም ድረስ ለቁርባንና መስዋእት የሚውል ቅዱስ የእንጨት ቅርፅ ነው።

### 3.5.2 ስነ-ቃል የአገር ሽማግሌዎች ወይም አቦገረብ እንዲከበሩ በማድረግ ያለው ፋይዳ፤

ስነ-ቃሎች ግጭቶች እንዲፈቱም ሆነ ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች ተግባራዊ እንዲሆኑና ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረግ አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የራያ አላማጣ ወረዳ ህዝብም ይህ የስነ-ቃላት የማሳመን ኃይል ሲገለገልበት ይታያል፡፡ ጠበኞች ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች (አቦገረብ እና ድባርተ) ጥሰው እንዳይሄዱና ለአገር ሽማግሌዎች ትልቅ ክብር እንዲሰጧቸው የራያ አላማጣ ህዝብ የሚከተለው ምሳሌአዊ ስነ-ቃል ይጠቀማል፡፡

- ገፅ ሽማግለ ድፈርሕ ወዲ ጭዋ [የሽማግሌዎች ፊት አይቶ የሚፈራ የጨዋ ልጅ ነው]፡፡
- ድንዕቕኸ ንዑቕ ሃም ዕንጭዋ [ሽማግሌዎችን የሚንቅ ግን እንደ አይጥ የተናቀ ነው] ይባላል፡፡

ከዚህ ጋር አያይዘው ወ/ሮ በለጠች መሐሪ የሚከተለውን ብለውኛል "ለታላቆችህ ካከበርክ በእግዚአብሔር የተመሰገንክ ትሆናለህ፡፡ ሽማግሌዎች ሊከበሩ ይገባል እንጂ መናቅ አይገባም" (ሚያዚያ 28፣2003፣ ስርክብ ገፅ 35)፡፡

### 3.5.3 በጋብቻ ወይም በክርስትና እንዲተሳሰሩ በማድረግ

ተሚጋቾች በአቦገረብ እና ድባርተ የተወሰነው ውሳኔ በመሻር ድጋሚ እንዳይጣሉና አንዱ በአንዱ ላይ እንዳይበቃቀሉ የዕርቁ ስርዓት እንደተፈፀመ የአካባቢው ህዝብ ከአቦገረብና ድባርተ በመተባበር በጋብቻ ወይም በክርስትና አባትነት (እናትነት) እንዲተሳሰሩ ያደርጋል፡፡

አሁንም አቶ ፍርዱ እምባዬ ተጣልተው የታረቁትን ሰዎች ታሪክ በመጥቀስ፣ የአገር ሽማገሌዎቹ ያዘዟቸውን ደግመው እንዳይሳሳቱ እና ቃል እንዲገቡ ሲጠይቋቸው ጠበኞቹ ምን እንደሚሉ እንዲህ በማለት ነግረውኛል፡፡ "... እነሱም ዳግመኛ አንጣላም፤ በጋብቻና በክርስትና አባትነት/እናትነት ዝምድናችንን እናጠናክረዋለን፤ እስካሁን ያደከምናችሁና ያስቀየምናችሁ አባቶቻችን ይቅር በሉን በማለት በግንባራቸው አፈር ላይ ተደፍተው ለመኑ" (ሚያዚያ 19፣2003፣ ስክርብ ገፅ 39)፡፡

ጠበኞቹ በጋብቻ ተሳሰሩ ማለት በተዘዋዋሪ መንገድ እህትና ወንድም ሆኑ ማለት ነው፡፡ በክርስትና እናትነት/አባትነት ከተሳሰሩ ደግሞ ዳግመኛ ላይጣሉ ወይም ላይበቃቀሉ ሃይማኖት እንደ ማሰሪያ ያገለግላል ማለት ነው፡፡

### 3.5.4 በአቦገረብ ወይም በአካባቢው ህዝብ እንዲናቁ በማድረግ

አቦገረብ እላይ ታች በማለት ለማስታረቅ የለፋትን ልፋት፣ ድባርተ ጠቡን ለማብረድ አፈር እየጫሩ በምህላና በጸሎት የደከሙትን ድካም ንቀው ጠበኞቹ አንታርቅም ካሉ፣ ወይም በዕርቅ ጊዜ ከጠፉ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶቹ እና በአካባቢው ህዝብ በችግራቸው ጊዜ አቤቱታ ቢያቀርቡ ተቀባይነት የላቸውም፡፡

ፍርዱ እምባየ ይህን ሐሳብ እንዲህ በማለት ነግሮኛል፡፡

> እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብህ ምንድነው፣ የበዳይ ወገኖች ወይም የተበዳይ ወገኖች አንታረቅም ካሉ፣ ለወደፊቱ በአቦገረብ መዳኘት አይችሉም፤ አቦገረብ ክብራቸው እንደተነካ፣ እንደተናቁና ከእነሱም አልፎ የአካባቢውን ማህበረሰብ እንደናቁ ይቆጠራል፡፡ አንዳች ችግር ቢደርስባቸው እንኳ የራሳቸው ወገኖች ካልሆኑ በስተክር ማንም አይደርስላቸውም (ሚያዚያ 07፣2003፣ ስክርብ ገፅ 15)፡፡

ጠበኞች አብረው ካደጉበት ማህበረሰብ ላለመነጠል ሲሉ፣ ለመኖር የሚያስችሉ ማህበራዊ ግንኙቶች ላለማጣት ሲሉ፣ ወይም ደግሞ ከአካባቢው ሽማግሌዎች እርግማን ለመዳን ሲሉ፣ የታዘዙትን ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ በአገር ሽማግሌዎችና በአካባቢው ማህበረሰብ እንዲገለሉ ማድረግ ሌላው የዕርቅ ዘዴ ነው፡፡

## 4. በራያ አላማጣ ማህበረሰብ የግጭት መፍቻ ስርዓት ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶች እና የተሰጡ ዓይነተኛ ውሳኔዎች

### 4.1. ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ላይ የሚከሰቱ ግጭቶች መሬትን፣ ድንበርን፣ የግጦሽ መሬትን የውሀን፣ የከብት ዝርፊያን፣ ብድርንና የመሳሰሉትን ምክንያት አድርገው የሚነሱ ጠቦችን ይመለከታል፡፡

በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ግለሰቦች መካከል፣ ቡድኖች  እና በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዳይስማሙ ወይም እንዲጋጩ ከሚያደርጉት ዋነኛ መንስኤ ምክንያቶች፣ ሴት (ውሽማ) ወይም በአካባቢው አጠራር "ሓያም"፣ ስካር፣ መሬት  (በሚታረስ መሬት፣ ድንበር፣ የግጦሽ መሬት)፣ ከብቶችን መምታት፣ ለከብቶች በተከለከለ መሬት ("ሕዛእቲ") ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 4.2. ከሴት (ውሽማ) ጋር የተያያዘ ግጭት

በራያ አላማጣ አካባቢ፣ በአጠቃላይ በራያ ማህበረሰብ ማለት ይቻላል፣ ትዳር የሌላት ሴት ወይም በአካባቢው መጠርያ "ሓያም" ትባላለች፡፡ ሓያም ትዳር ስለሌላት ወንዶች በውሽምነት ለመያዝ ይፎካከሩባታል፡፡ አንዱ በጉልበት ሌሎቹን ያሸነፈ እንደሆነ ወይም በመልኩ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ባህላዊ ዘፈን የሆነውን "ጉማየ" የሚችል ከሆነ በሴቷ ትልቅ ግምት ይሰጠዋል፤ ወይም እሺ ማለቷን ታረጋግጥለታለች፡፡ በሴቷ ያልተመረጡ ወንዶችም ለምን ተሸነፍን ከሚለው ቅናት ተነስተው ወንዱን ለመምታት ወይም ለመግደል ይጣጣራሉ፡፡ በዚህ ሰበብ የተነሳም እስከ ከባድ የግጭት ዓይነት ግድያ ይደርሳሉ፡፡ በሴት ለሚነሳው ግጭት አቶ ብርሃኑ አበራ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> እ… በራያ አላማጣና አካባቢዋ የሚነሱ ጠቦች ዋና መንስኤዎቻቸው አንዱ በሴት ነው፡፡ ሴት ስልህ በአካባቢው መጠሪያ "ሓያም" ማለት ነው፡፡ "ሓያም" አሁን.. የአንድ ወንድ ላትሆን ትችላለች፡፡ በተለይም በዝናዋ እና በቁንጅናዋ የታወቀች ከሆነች ወንዱ የራሱ ለማድረግ ወይም አሸናፊነቱን ለማሳወቅ ከብዙ ሰዎች ይጣላል፡፡ ሴቷም ወንዶች ከተጣሉባት ራሷን ከፍከፍ የምታደርግበት ሁኔታ አለ (ሚያዚያ 06፣2003፣ ስክርብ ገፅ 4)፡፡

### 4.3. በመጠጥ (በስካር) ምክንያት የሚከሰት ግጭት

ሰዎች ከመጠን በላይ ይጠጡና ሰክረው እርስ በርሳቸው ይጋጫሉ። በስካር ምክንያት የሚነሱ ግጭቶች በብዛት ወዲያውኑ በመጠጡ ጊዜ የሚነሱ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የቆየው ጠባቸውን በማስታወስ የሚያነሷቸው ናቸው። ለዘመናት ወይም ለዓመታት ያረገዙትን ቂም በመጠጥ ተገፋፍተው ይጋጫሉ። አቶ ብርሃኑ አበራ በመጠጥ ምክንያት የሚከሰተውን ግጭት እንዲህ በማለት ገልፀውታል።

> … ሌላው የግጭት መንስኤ በስካር ነው። ሰክረው ከቁስለት እስከ ግድያ የሚደርሱ ሰዎች አሉ፤ እንግዲህ የእኛ ሰው ታውቀዋለህ፣ በልቼ ጠጥቼ ልሙት ነው፣ ለነገ ብሎ ነገር አይሰራም፤ ከመጠን በላይ ይጠጡና ወንድም ከወንድሙ፣ ጓደኛ ከጓደኛው፣ ትንሽ ቂም በቀል ከነበራቸው ሰዎች ጋር ለመጣላት ተመቻችላቸው ማለት ነው። መጠጡ ራሱ ይገፋፋቸዋል። እና በዚህ በዚህ ሃይለኛ ጠብ ይነሳል። እስከ በቢላ መውጋት ወይም መገዳደል የሚያደርስ መጠጥ ነው (ዝኒ ከማሁ)።

ሌላው አቶ ተላ ቓሺ የመጠጥ ወይም የስካር አስከፊነት "መጠጥ ቤት ስታስበው ከብዙ ሰዎች ጋር ትጣላለህ። በቀላል ንግግር ጀምረህ ወደ ሌላ ነገር ልትደርስ ትችላለህ። ስለዚህ መጠጥ ቤት ችግር ነው (ግንቦት 02፣2003፣ ስክርብ ገፅ 58) በማለት ይገልፃሉ።

ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል እንዲሉ፣ መጠጥ ሰዎች በነፃነት እንዲናገሩ ወይም የሆዳቸውን ሚስጢር እንዲያወጡ ያደርጋቸዋል። የራሳቸው ምስጢር ከማውጣት አልፈው የሌላውን ያወጡና እርስ በርስ መሰዳደብ ይጀምራሉ፤ በእንዲህ መልኩ የተጀመረ ንትርክ እስከ አካል መጉደል እና ግድያ ያደርሳቸዋል።

### 4.4. ከመሬት (የሚታረስ መሬት፣ ግጦሽ መሬት፣ ድንበር) የተያያዙ ግጭቶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ መታየት ካለበት አንዱ የድንበር ግጭት ነው። ከድንበር ግጭት ጋር ተያይዞ የግጦሽ መሬትም አለ። የራያ አላማጣ ወረዳ አጎራባች ከሆኑት አንዱ ከዓፋር ክልል ጋር ግጭቶች የሚከሰቱ መሆናቸውን አቶ ብርሃኑ አበራ ነግረውኛል።

> ከአማራ ክልል ጋር እንኳ እስካሁን ግጭት አላጋጠመንም። ከአፋር ክልል ግን ግጭቶች ይታያሉ። እ... እነዚህ ግጭቶች በመንግስት አካላትም፣ በአቦገረብም እንዲፈቱ ይደረጋል። አቦገረብ የእኛዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ከአፋርም ስላሉ ተባብረው ነው የሚፈቱት። የሁለቱም ክልሎች ከፍተኛ አመራሮች በመወያየትም ግጭቱን ይፈቱታል። ግጭቱን የሚያነሱት ግን በብዛት በአፋር ድንበር ያሉትን ነው። አንዳንዴ ስታስበው ከፍተኛ ችግር አለባቸው። በብዛት ለግጦሽ መሬት ሲሉ የሚያነሱት ግጭት ነው። ግን በሁለቱም በኩል በይበልጥ የአገር ሽማግሌዎች ስላሉ ጠቡ ወዲያውኑ እንዲፈታ ያደርጋሉ (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 12-13)።

አቶ ብርሃኑ አበራ እንዳሉት በራያ አላማጣ እና ዓፋር ክልል መሀከል የድንበር ግጭት ሲከሰት በሁለት መንገድ ይፈታል፡ አንደኛው በዓፋርና ራያ አላማጣ ባሉት አቦገረብ አማካኝነት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በሁለቱም ክልሎች ባሉት የበላይ አመራሮች ነው።

ከእርሻ ጋር የተያያዘ ግጭትም አለ። እያንዳንዱ ሰው ለመተዳደሪያው የሚሆን በህጋዊ መንገድ የተሰጠው የሚታረስ መሬት አለው። እንዲህ ሆኖ ሳለ፣ በንቀት ወይም አላግባብ የሌላ ሰው ድርሻ የራስን ለማድረግ በሚል ፈሊጥ የእርሻ መሬት ድንበር ያፈርሳል። በዚህም የተነሳ በሰዎች መሀከል ጠብ ይከሰታል። አቶ ብርሃኑ አበራ "... እኮ! አሁን... ሀብትና ንብረት ሲባል መሬት ነው። መሬትክን ሌላ ሰው ከወሰደው ወይም ድንበሩን ከገፋብህ፣ ለምን መሬቴን ገፋህብኝ በሚለው መንገድ ግጭት ይነሳል" (ሚያዚያ 06፣2003፣ ስክርብ ገፅ 5) በማለት ተናግረዋል።

### 4.5. ለከብቶች በተከለከለ መሬት ("ሕዛእቲ") የሚነሳ ግጭት

እያንዳንዱ ገበሬ በቡድን በመመዳደብ የራሱ የሆነ ለከብቶቹ የሚሆን የተከለከለ የሳር መሬት አለው። ነገር ግን አንዱ በሌላው ላይ ከብቶቹን የማሰማራት አጋጣሚ ይከሰታል። ግማሹን የተበላበት ሰው ወይም ቡድን ለምን እንዲህ ይሆናል በማለት ጠብ ያነሳል።

የዚህ ዓይነቱ ግጭት ከአቦገረብ በፊት "ሀገር" ያዩታል። "ሀገር" ለተከለከለው መሬት በአግባቡ በማከፋፈል የሚያስተባብሩ እና ሰዎች በጉዳዩ እንዳይጣሉ የሚያደርጉ ናቸው።

### 4.6. የቤተሰብ ጠብ

በዚህ የጠብ ዓይነት ከጋብቻ፣ ከልጆች፣ ከውርስ፣ ወዘተ... ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶች ይገኙበታል። በራያ አላማጣ አካባቢ መረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ ከጋብቻ እና ከውርስ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ግጭቶች አሉ።

ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ነገሮች ከሚከሰቱ ግጭቶች አንዱ አንድ ወንድ አንዲት የሴት ልጅን ለትዳር ጠይቆ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካለት ሲቀር እና ለሌላ ወንድ ስትታጭ የሚከሰት ግጭት ነው። አቶ አርሴ ማርየ በቅርብ ጊዜ በራያ አላማጣ ወረዳ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የተከሰተ ግጭት ታሪክ እንደሚከተለው ተርከውልኛል።

> ... እነዚህ ሰዎች የተጣሉት በጋብቻ ነው። ልጅህን ስጠኝ አልሰጥም እየተባባሉ በሽንጎ ፍርድ እየተከራከሩ ይውላሉ። ወደየቤታቸው ሲመለሱ ሲሉ፣ በጉልበት ጠልፎ ሊወስዳት ሲል እሪታዋን ታሰማለች። ሰውየውም አባቷን በቢላ ይገድላቸዋል። ከዛ በኋላ የሟቹ ቤተሰብ በሁለተኛው ቀን የገዳዩን እናት ይገድሏታል። የመጀመሪያ ገዳዩም አልተያዘም ነበርና በነጋታው እህታቸውና አጎታቸውን ገደለባቸው፣ በአጠቃላይ በሁለቱም ወገኖች አራት አራት ሞቱ። ስለዚህ ከአላማጣ ሃምሳ አቦገረብ፣ ከጨርጨር ሃምሳ አቦገረብ፣ ከሌሎች አካባቢዎች ደግሞ የተወሰኑትን አቦገረቦች ተውጣጥተው እግዚኦ ሊሉ ተሰበሰቡ። ከዋና ዋና አቦገረብ ተመካክረን፣ ድባርተም ከኋላ ሆነው አፈር እየጫሩ እግዚኦ እንዲሉ አደረግን። ከዛ በኋላ አቦገረብ ባወጡት ህግ መሰረት የሚቀጣው ተቀጥቶ፣ የሚክስ ክሶ፣ መንግስትም በህግ ቀጣቸው። በእኛ በኩል ግን ለወደፊቱ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዳይከሰት በታቦት፣ በመስቀል ለምነን አስታረቅናቸው (ሚያዚያ 07፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 18፣17)።

በራያ አላማጣ ወረዳ ከባልና ሚስት የጋብቻ ፍች ተያይዞ የሚነሳ ጠብም አለ። ይህ ግጭት ወንዱ በሴቷ ላይ የበላይነት በማሳየት በጋራ ያፈሩትን ሀብት አልከፍልም በሚልበት ወቅት የሚከሰት ነው።

አባት ወይም እናት፣ ወይም ደግሞ አባት እና እናት በሞቱባቸው ልጆች መሀከልም ያባቴ ሃብት ለእኔ ይገባኛል በሚል ራስ ወዳድነት ግጭቶች ይነሳሉ።

አቶ ብርሃኑ አበራ በባልና ሚስት ፍች ስለሚነሱት ግጭቶች እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

> አዎ፣ ከፍች ጋር ተያይዞ የሚነሳ ችግር ራሱ የጎላ ነው፣ ስለዚህ ባልና ሚስት ሳይፈልጉ፣ ማለቴ ሚስትየው እየፈለገች ወይም

> ባልየው እየፈለገ ከተፋቱ ከፍተኛ የሆነ ጠብ ይነሳል። በተለይም ባልየው እየፈለገ ሴቷ አልታረቅም ያለች እንደሆነ "ንቃኝ ነው" በሚል ኃይለኛ ጠብ ይከሰታል። ወይም ደግሞ ሌላ ወንድ ለምዳ ነው እንዲህ አልታረቅም የምትለው ብሎ አካኪ ዘራፍ ይልና በሴትየዋ ቤተሰብና በባልየው ቤተሰብ መካከል ግጭት ይከሰታል። ይሄ አሁን የሴቶች መብት እየጣሰ ማለት ነው። ሴቶቹ ካልፈለጉ አልፈለጉም ነው። ለምን ይገደዳሉ! ባልና ሚስት ተጣልተው በጋራ ያፈሩትን ንብረት በሚካፈሉበት ጊዜም እኩል መካፈል እያለባቸው ባልየው አይገባትም በማለት ጠብ ያነሳል፤ ይማታልም፤ ይህ ዓይነት ባህል ጥሩ አይደለም (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 5)።

አንድ አንድ ጊዜ የባልና ሚስት ፍች እራሳቸው ባመጡት ጣጣ ላይሆን ይችላል። ባልና ሚስት ጥሩ ፍቅር እያላቸው፣ የባልየው ዘመዶች ወይም የሚስትየው ዘመዶች ደስ ካላላቸው እንዲፋቱ ይወተውቷቸዋል። በዚህ ጊዜ የባልየው ዘመዶች ከሚስትየው ዘመዶች መካከል ጠብ ሊከሰት ይችላል። ወይም ደግሞ ባልየው ከሚስትየው ዘመዶችና ጋር፣ በሚስትየው ከባልየው ዘመዶች ጋርም ይጋጫሉ።

### 4.7. ወንጀል

በወንጀል ውስጥ የሚካተቱ ግጭቶች ድብድብ እና ግድያን የሚያጠቃልሉ ናቸው። በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ድብድብና ግድያ የተለመዱ ናቸው። እነዚህ በወንጀል ስር የሚመደቡ ከባድ ግጭቶች ናቸው። በአካባቢው ማህበረሰብ ከባድ ግጭቶች ወይም ወንጀሎች የሚባሉት ግድያ፣ የአካል መጉደል፣ የድንበር ግጭት እና የመሳሰሉት ናቸው። ይህን አስመልክተው አቶ ተሳ ቓሺ እንዲህ በማለት ገልጸውልኛል። "አሁን አሁን ቀርቷል እንጂ ከአፋሮች ጋር የድንበር ግጭት ነበር፤ ዘንድሮ ግን እግዚአቤሔር ይመስገን የለም። ግድያ ደግሞ ትልቅ ጠብ ነው። እና እነዚህ በጣም አስቀያሚ ግጭቶች ናቸው" (ግንቦት 02፣ 2003፣ ስክርብ 58)።

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ በተለይም የግድያ፣ የድንበር ግጭት እና ሌሎች ከባድ ግጭቶች ሲከሰቱ ፣ ድባርተ ከአቦገረብ በመተባበር ጠቡን ይፈቱታል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ድባርተ አቦገረብን የሚያግዟቸው በጸሎት ብቻ አይደለም። ድባርተ አቦገረብ ለዕርቅ ሲሉ ከቤታቸው በሚወጡበት ጊዜ በምግብ ዝግጅትም ሆነ የተለያዩ

ቁሳቁሶችን በማቀበል ይረዷቸዋል። ይህን አስመልክተው አቶ እምባየ ደስታ እንዲህ ይላሉ።

"በተለይም ከአፋር ስንጋጭኮ በምግብ ዝግጅት፣ አቦገረብ ለዕርቅ ከቤታቸው ሲወጡ፣ አንድ አንድ ስራ በመተባበር በጣም ያግዛሉ (ሚያዚያ 22፣2003፣ ስክርብ ገፅ 30) ።

በከባድ ወንጀልነት ከሚመደቡት ጉዳዮች አንዱ ግድያ ነው። በራያ አላማጣ ማህበረሰብ የግድያ ወንጀል በሶስት ይከፈላል። አንደኛው የግድያ ወንጀል "ቀይ ደም" የሚባል ሲሆን፣ ገዳይ ሳያስበው ወይም በአጋጣሚ ሰው ሲገድል ነው። ሁለተኛው የግድያ ዓይነት "ጥቁር ደም" የሚባል ሲሆን፣ ገዳዩ ተዘጋጅቶበት፣ በቆየ ቂም በቀል ላይ ተመስርቶ፣ ሆን ብሎ የሚያደርገው ከባድ ጥፋት ነው። ሶስተኛው የግድያ አይነት ደግሞ "ሙሉ ጥቁር" ደም ሲሆን፣ ገዳዩ የሟች ብልት፣ አንገት ወይም ሌላ አካሉን ቆርጦ ሲጥል ነው። ከዚህ ጋር አያይዘው አቶ አርሴ ማርየ በራያ አላማጣ ወረዳ የተከሰተው የመኪና የሞት አደጋ እንደሚከተለው ተርከውልኛል።

> ለምሳሌ አንድ ሰው በቅርብ ጊዜ እዚህ ከተማ ውስጥ ሞቷል። [የሞተው በNGO መኪና ነው]። ወዲያው ሾፌርዋ ሴት ነበረችና ሐኪም ቤት ወሰደችው። ግን ሰውየው ሊድን አልቻለም። ከዚያ በኋላ አቦገረብም በቅርብ ስለነበርን ገዳይዋንና የሟቹን ሚስት ከነዘመዶቹ ለመዳኘት አሰብን። አውቃ እንዳልሆነ የገደለችው፣ በትራፊክ ሕግም የሰውየው ችግር እንደነበር ከተመካከርን በኋላ ገዳይዋን መክፈል የምትፈልገውን የካሳ መጠን ጠየቅናት። እሷም የተባረከች ነበረችና መናገር እስኪያቅታት ድረስ እያለቀሰች ለልጆቹ ማሳደጊያ፣ እንዲሁም ለሟቹ ለተዝካር የሚሆን እክሳለሁ ብላ ወሰነች። ስለዚህ አቦገረብም ብዙ አላለፉንም፣ እሷም ሸማነ [ጥቁር የሐዘን ልብስ] ሳትለብስ፣ ድባርተ ሳይደክሙ፣ ነገሩ ሳይካበድ ዕርቀ ሰላም ወረደ ማለት ነው። (ሚያዚያ 07፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 19)።

### 4.8. ተራ ወንጀሎች

በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ተራ ወንጀሎች የሚባሉት ለክፉ የማይሰጡ እና ስር ሰደድ የሆነ ቂም በቀል የማይፈጥሩ ናቸው። ቀላል ግጭቶች ወይም ተራ ወንጀሎች በብዛት እንደተከሰቱ ወዲያው የሚበርዱ ናቸው። ለምሳሌ መሰዳደብ ተራ ወንጀል ነው። ተራ ወንጀል ወይም ቀላል ግጭት የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ አቶ ብርሃኑ አበራ እንደሚከተለው ገልጸውልኛል።

> ቀላል የሚባሉት ግጭቶችማ አንዱ ስድብ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች መሰዳደብ አለ። ከዚህም ተያይዞ ለክፉ የማይዳርጉ መነሻቸው ስድብ ሆኖ ቀላል መማታት አለ። ተማተው ክፉኛ ሳይቆስሉ ሲቀሩ ጊዜ በቀላሉ ይታረቃሉ። እ... ቀላል መማታት ስልህ ደም ሳይወጣ ወይም የአካል ጉድለት ሳያጋጥም ማለት ነው። እነዚህ ቀላል ናቸው። አቦገረብ ራሱ ላያያቸው ይችላል። በቀላሉ በጎረቤት ሊታረቁ ይችላሉ (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 6)።

ጠበኞች አካላቸው ካልጎደለ፣ ወይም ደም መፋሰስ ካላጋጠማቸው ቀላል ግጭት ነው። መሰዳደብ ተራ ወንጀል የተባለበት ምክንያት ለዚህ ነው። ስለዚህ ተራ ወንጀል ማንም ሰው ሊዳኘው ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ተራ ወንጀሎች ለከባድ ግጭቶች መንስኤ ናቸው። በቀላል ነገር ይጀመርና ወዲያውኑ ወይም ከጊዜ በኋላ ወደ ወንጀል ይሸጋገራል። እነዚህ ቀላል ጠቦች ላልታሰበ ቂም በቀል ወይም የከፋ ግጭት የሚዳርጉ መሆናቸውን መንገሻ ካሳ "በስድብ ወይም ጣቶችን እየቀሰርክ ከሚደረጉ ጥቆማዎች ሊሆን ይችላል። እና ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ በዓይን ግልምጫና ምራቅን በመትፋት የሚነሱ ጠቦች አሉ። እነዚህ ናቸው ወዳልታሰቡ ግጭቶች ወይም ከባድ ግጭቶች ወደምንላቸው የሚያሸጋግሩ" (ግንቦት 02፣2003፣ ስክርብ ገፅ 50) በማለት ገልጾልኛል።

በመስክ ጥናቴ ላይ ከታዘብኩትና አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ ስርቆት ነውር ነው። ስርቆት እንደ ተራ ወንጀል ሳይሆን እንደ ከባድ ወንጀል በዕርቅ ምህረት የማይደረግለት ነው። የአካባቢው ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች የማይከታተሉትና ለመዳኘት የማይሞክሩት ወንጀል ስርቆትን ብቻ ነው። ስርቆት ያልለፉበትንና ጉልበት ያላፈሰሱበትን ነገር የራስ የማድረግ ጉጉት ነው በማለት ያወግዙታል። እየሰረቀ የተገኘ እንደሆነ ቢገደል እንኳ ገዳዩን መንግስት ይከታተለዋል እንጂ በአቦገረብ ወይም በድባርተ በኩል ትኩረት አይሰጠውም።

> "ሆን ብሎ ሰው የገደለምኮ አለ፣ ሆን ብሎ የገደለ ግን በአቦገረብ ይዳኛል?" ብዬ ስጠይቃቸው፣ አንድ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ መረጃ አቀባዩ ምክንያቱን እንዲህ በማለት ነግረውኛል። "ሁለቱም ይለያያሉ፤ አንተ ከባዶ ተነስተህ ሰው አትገድልም። ቂም በቀል ሲኖርብህ፣ ወይም ጥቃት ሲደርስብህ ነው። ስርቆት ግን አሳፋሪ ስራ ነው። መስራት እየቻልክ እንዳንተ ጉልበት ያላቸው ያፈሩትን ንብረት መመኘት ነው፤ ስለዚህ በጣም ይለያያሉ" (ሚያዚያ 11፣ 2003 ስክርብ ገፅ 44) ።

### 4.9. የቡድን ጠብ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የሚነሱ ሐሳቦች በጎሳና ጎሳ፣ በብሔረሰብና ብሔረሰብ፣ በሃይማኖትና በሃይማኖት መካከል የሚነሱ ግጭቶች ናቸው። በዘመናችን ከቋንቋ፣ ከማንነት/ከምንነት (Identity) እና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች እንዳሉ ይታወቃል። በራያ አላማጣ ማህበረሰብ በእነዚህ ምክንያቶች ግጭቶች እንዳልተነሱ ቢናገሩም አልፎ አልፎ ከቡድን ጠብ አንዱ የሆነው በጎሳና ጎሳ ጠብ እንደሚከሰት ይናገራሉ። አቶ ብርሃኑ አበራ በአንድ ወቅት በሁለት የተለያዩ መንደሮች ወይም ጎሳዎች ግጭት ተከስቶ መኖሩን እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡-

> ለምሳሌ እኔ የማውቀው ምናለ መሰለህ ... እ... የዛሬ ስንት አመት ነው? ስድስት ወይም ሰባት አመት ይሆነዋል። አላማጣ ገጠር አካባቢ በሰፊር (መንደር) ተጣልተው ነበር። በኋላ በአቦገረብ ከታረቁ በኋላ በጣም የሚደንቅ ፍቅር በሁለቱም መሀከል ተፈጥሯል። በአሁኑ ጊዜ የታረቁበትን ቀን በአመት አንዴ ያከብራሉ። ከመንግስት አካላትም የተወሰኑትን እየጠሩ በሬ አርደው ይደግሳሉ። ሰርግ ሲኖራቸው፣ ክርስትና ሲኖራቸው፣ ወይም የሆነ ችግር ሲገጥማቸው ሁለቱም በጋራ እየሆኑ ብር እያዋጡ ተአምር የሆነ ፍቅር ፈጥረዋል (ሚያዚያ 06፣2003፣ ስክርብ 12)።

ብዙዎቹ የመረጃ አቀባዮቼ እንደሚስማሙበት በራያ አላማጣ ወረዳ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በሃይማኖቶች መካከል፣ እንዲሁም ከማንነት አንፃር የተያያዙ ግጭቶች አይታዩም። በእነዚህ ርእሰ ጉዳዮች የተነሳ ግጭት እንደሌለና ለምን እንደማይከሰት አቶ ብርሃኑ አበራ እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> በዚህ አካባቢ እስካሁን ድረስ በፖለቲካ ወይም በሃይማኖት መካከል ግጭት አላጋጠመንም። ምክንያቱም የአገሪቷ ህገ-መንግስት ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሰላማዊ መንገድ የማነሳሳት ስራ ሊሰራ ይችላል። ስለዚህ ደጋፊ ያልሆኑ ፓርቲዎችም ህገ-መንግስታዊ ስርዓት መሰረት አድርገው እንዲንቀሳቀሱ ነው የሚያዝዘው። ስለዚህ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚካሄደው በህግ እንጂ ከህግ ውጭ አይሆንም። በዋናነት ዘመናዊው የፍትህ አካል ለእነዚህ ነገሮች መሰረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ነው። መንግስት ባወጣው ህግ መሰረት ነፃ ሆኖ እንዲመርጥና እንዲመረጥ ተፈቅዶለታል። ስለዚህ በአካባቢያችን በእነዚህ ነገሮች የተነሳ ችግር የለም (ሚያዚያ 06፣2003፣ ስክርብ ገፅ 7)።

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ያሉ ሃይማኖቶች እስልምናና ክርስትና (በብዛት ኦርቶዶክስ) ናቸው። እነዚህ ሃይማኖት በሚከተሉት ማህበረሰቦች የየራሳቸው የሆኑ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች አሏቸው። መረጃ አቀባዮቼ እንደሚሉት በአካባቢው በሃይማኖት መካከል ግጭት አይከሰትም። ከድሮ ጀምሮ በሐዘንም ሆነ በደስታ ይግባባሉ። ክርስቲያኖቹ ቃልቾቹን፣ ወይም ደግሞ ሙስሊሞቹ አቦገረብን የሚንቁበት አጋጣሚ አልተፈጠረም ተፈጥሮም አያውቅም ይላሉ። ስለዚህ ጉዳይ መንገሻ ካሳ የሚከተለውን ሐሳብ አካፍለውኛል።

> የሚገርምህና የሚደንቅህ ነገር እኩል የሆነ ችሎታ ነው ያላቸው። አቦገረብ እና ቃልቻዎች ማለቴ ነው እ... ህዝቡን የትኛው ይበልጣል ብለህ ብትጠይቀው እንኳ ክርስቲያኑ አቦገረብ፣ እስላሙ ቃልቻዎች አይልህም። ሁለቱም እኩል ናቸው ነው የሚልህ። ይህ ከየት የተነሳ ነው፣ እ... የአቦገረብና ቃልቻዎች መከባበር ያመጣው ነው። በተለይ በድንበር ግጭትማኮ ተውጣጥተው በጋራ የሚሄዱበት አጋጣሚ አለ (ግንቦት 02፣2003፣ ስክርብ ገፅ 52)።

አቦገረብ በግጭት ወቅት ከማስታረቅ ውጪ ሌላ በሐዘንና በደስታ ጊዜ ህዝቡን በማስተባበር ረገድ ተጨማሪ አስተዋፅኦ አላቸው። አቦገረብ በመፅሐፍ ቅዱስ ህግ የሚተዳደሩ፣ አማኞች እና ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው ናቸው። በሙስሊሞች በኩል ያሉ ቃልቾችም በእምነታቸው የጸኑ፣ በአምላካቸው ስም የታመሙትን የሚያድኑ፣ እንዲሁም በአካባቢው ወንጀል በሚፈፀምበት ጊዜ ከአቦገረብ በመተባበር ግጭቱን የማብረድ ስራ የሚሰሩ ናቸው ተብሎ ይታመናል። ይህን አስመልክቶ መንገሻ ካሳ የሚከተለውን ብሏል።

> .... አንድ አንድ የታመሙ ሰዎችም በባህላቸው፣ በእምነታቸው ይፈውሳሉ። "ዓይነ ጥላ"[16] ያላቸው ሰዎች ያወጣሉ። ሁለት ባልና ሚስት የሚጣሉበት ምክንያት የራሳቸው "ቁራኛ"[17] ስላላቸው ነው ብለው ስለሚያምኑ የሚያፋቅር መድሃኒት ይሰጧቸዋል።ወይም "ዱአ"[18] አድርገው ይመርቋቸዋል። ይሄም በማህበረሰቡ እ... በሙስሊሙ

---

[16] "ዓይነ-ጥላ" ሰዎች በነፃነት እንዳይናገሩ፣ ከሌላው ማህበረሰብ ተግባብተውና ተስማምተው እንዳይኖሩ የሚያደርግ መንፈስ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከሰዎች ፊት በሚቆሙበት ጊዜ የሚያንቀጠቅጥ፣ ዓይን የሚያሳክክ በሽታ ነው ማለት በእምባ አላጌ ወረዳ በሚገኘው የቅዱስ ቅርቆስ ደብር አገልጋይ የሆኑት መርጌታ ካሳ ኪሮስ ገልጸውልኛል።

[17] "ቁራኛ" የማያንቀሳቅስ፣ ጠምዶ የሚይዝ በሽታ ነው(ዝኒ ከማሁ) ።

> ማህበረሰብ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። ባልና ሚስት እንዲጣሉ የሚያደርግ "ጸላኤ ሰናይ"[19] ነው ይላሉ።

ሁራ መረጃ አቀባዮቼ በብዛት የሚስማሙበት ነጥብ በሃይማኖት መካከል ጠብ የሌለ ሆኑን ነው። ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ ነገሩ ባልጎላ መልኩ አዳዲስ ሃይማኖት መምጣታቸው የሚነሱ ቀዝቃዛ ግርግሮች እንዳሉ ይናገራሉ። በዚህ ላይ ያላቸው ሳብ አቶ ብርሃኑ አበራ እንዲህ ይላሉ።

> "ዝም ብሎ ጉልህ ባልሆነ መልኩ ብቅ ብቅ የሚል ነገር አለ። ለምሳሌ በኦርቶዶክስና ጴንጤዎች[20] በተወሰነ መልኩ ያለመስማማት ሁኔታ አለ። ለወንጀል የሚዳርግ ወይም ለወረዳችን ፍትህና ፀጥታ የሚበጠብጥ ግን አይደለም። በድብቅ እንዲህ ዓይነት ችግር አለ ሲባል እንጂ እንዲህ ሆነዋል ተብሎ ለህግ የቀረበ ግለሰብ ወይም የሃይማኖት አባቶች የሉም" (ሚያዚያ 06፣2003፣ ስክርብ ገፅ 7)።

---

[18] "ዱአ" ጸሎት ነው። በእስልምና ሃይመኖት ፈጣሪያቸውን የሚለምኑበት መንገድ ነው። (መንገሻ ካሳ፣ ግንቦት 02፣2003)።

[19] "ጸላኤ ሰናይ" በጎ ስራዎች እንዳይሰሩ የሚያደናቅፍ እርኩስ መንፈስ ነው ማለት በእምባ አላጌ ወረዳ በሚገኘው የቅዱስ ቅርቆስ ደብር አገልጋይ የሆኑት መርጌታ ካሳ ኪሮስ ገልጸውልኛል።

[20] ጴንጤ የተባለው ፕሮቴስታንት ለማለት ነው።(ምንጭ ከራሴ)

## 5. በመደበኛ ፍርድ ቤት፣ በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች መሀከል ያለ ግንኙነት

አቦገረብ እና ድባርተ እንደ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በብዛት ከዘመናዊው ወይም መደበኛ ፍርድ ቤት በጋራ የሚሰሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱም በሰላማዊ መንገድ ስራቸውን እንደሚያከናውኑ የተረዳሁት መረጃ አቀባዮቼ ከሰጡኝ ቃለ-መጠይቅ እንጂ፣ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ከመደበኛ የፍርድ ቤት አካላት ያገኘሁት መረጃ የለም፡፡

### 5.1 አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓቶች በአሁኑ ጊዜ

አቦገረብ እና ድባርተ እንደ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓቶች በመዋቅራቸው እና በአንድ አንድ ሂደቶቻቸው የመለዋወጥ ወይም የመቅረት ሁኔታ ቢታይባቸውም፣ የሚሰጡት አገልግሎት ግን በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ እየተስፋፋ መሆኑን አውራ መረጃ አቀባዮቼ ይናገራሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ዋናው የፍትህ ስርዓት በመሆን እያገለገለ እንደሚገኝም ይናገራሉ፡፡ አቦገረብ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ከድሮ ጀምሮ እንደነበረም ይናገራሉ፡፡

እንዲህ ላደረገ ይሄን ያህል ወይም ይህን መሰል ቅጣት ይገባዋል ተብሎ በአገር ሽማግሌዎች የሚል ህግ መደንገግ የተጀመረው ከ1919 ዓ/ም እንደሆነ አቶ አርሴ ማርየ እንደሚከተለው ይናገራሉ፡፡

> እ… አስታውሳለሁ፡፡ አባቴ እንደነገሩኝ በ1919 ዓ/ም አካባቢ ነው፡፡ እስከ 1922 ዓ/ም ቀጥሏል፡፡ ከዛ በኂላ ግን ህዝቡ እየዋለ እያደረ ሲያየው መግደል እንደቀላል ነገር ይታይ ስለነበር፣ እ… በፍየሎች እንዲቀየር ይደረጋል፡፡ ወይም ደግሞ በፍየሎች የማይችል ከሆነ፣ ስድስት መቶ ብር እንዲያቀርብ ይታዘዛል፡፡ ይህ ካሳ ለሟች ወገን ነው የሚሆነው፤ ለሚያስታርቁ አቦገረብም ከሃያ እስከ ሃያ አምስት ብር እንዲከፍሉ ተወሰነ፣ የዚያን ጊዜ በህግ የጸደቀ ሳይሆን ዝም ብሎ በጎን ሲወሰን የነበረ ነው፡፡ ስድስት መቶ ብር የነበረው ወደ አራት መቶ ወይም ሶስት መቶ የሚወርድበት አጋጣሚም አለ፡፡ ለመስቀል፣ ለሽማግሌ፣ ለድባርተ ሲባል ብዙ ብር ይቀነሳል፡፡ (ሚያዚያ 07፣2003፣ ስክርብ ገፅ 14)፡፡

### 5.1.1 ለመስዋዕት የሚሆን እንስሳ ዕርድ

ነዕርቅ ጊዜ የሚችና የገዳይ ወገኖች በደሙ ተረጭተው ድጋሚ ላለመጣላት ቃል እንዲገቡ ዕርድ ይደረጋል። አራጁ ከገዳይ ዘመዶች ሲሆን፣ ጥፋተኞች እኛው ነን፤ ደም የፈሰስነው እኛው ነን፤ ስለዚህ ጥፋተኝነታችን አምነናልና ይቅር በሉን የሚል ትርጉም አለው። አቶ እምባየ ደስታ እንዲህ በማለት ይገልፁታል።

"ከገዳይ ወገኖች የቅርብ ዘመድ የሆነ ነው የሚያርደው፣ ምክንያቱም በሰይጣንም ሆነ በየዋህነት ደም ያፈሰስን እኛው ነን ማለት ነው" (ሚያዚያ 22፣2003 ስክርብ ገፅ 24) ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዕርቅ ጊዜ ለሚታረድ በሬ ወይም መስዋእት መፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል።

"የሚቃጠል መስዋዕት እንዲያቀርቡ፣ ለእግዚአብሔርም ስለ ደህንነት መስዋዕት በሬዎችን እንዲሰዉ የእስራኤልን ልጆች ጎበዛዝት ሰደደ"(ዘጸ 24፣5)።

መስዋእት ወይም በሬዎች ማረድ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው። በኦሪት ጊዜ መስዋእት የሰላምና የደህንነት ተምሳሌት ከመሆኑም በተጨማሪ፣ እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ድርጊት ነበረ። "የሚቃጠል መስዋዕት" ሲል፣ የሚጠፋ፣ ህይወቱ የሚያልፍ ወይም የሚታረድ እንስሳ ማለት ነው። በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶችም ይህ ነገር ሲደረግ ይታያል። ከዕርዱ በኋላ በታረደው እንስሳ ደም ጠበኞቹ እንዲረጩ ይደረጋል። ከዚህ በኋላ ነው ተሚጋቾች ወይም ጠበኞች መታረቅ የሚችሉት። መረጃ አቀባዮቹ እንደሚሉት ከታረደው እንስሳ ደም መርጨት፣ ያጣላቸውን እርኩስ መንፈስ ደሙ እንደዚህ ይረጭ ለማለት ነው። "ያጣላን እርኩስ መንፈስ ደሙ እንደዚህ ይረጭ ነዋ" (ሚያዚያ 22፣2003 ስክርብ ገፅ 24) በማለት አቶ እምባየ ደስታ ይናገራሉ።



ስእል 6 በእርቅ ወቅት የሚታረደው እርድ

በዕርቁ ስርዓት ላይ ዕርዱ ከተካሄደ በኋላ በአቦገረብና ሌሎች የአገር ሽማግሌዎች የተወሰነውን የደም ካሳ ገንዘብ፣ የገዳይ ወገኖች እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ ወይም ደግሞ ከአቦገረብ አንዱ ተወካይ በመሆን ለሚመለከታቸው የሟች ወገኖች ያስረክባሉ፡፡ የሟች ወገኖች ገንዘብ ወይም የደም ካሳ አነሰን ሊሉ ይችላሉ፡፡ አቦገረብም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው ቀጠሮ ይጠይቃሉ፡፡ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች የደም ካሳ ገንዘብ ጠቃሚ መሆኑን የኢትዮጵያ ጥናት ምርምር አንደኛ ሀገራዊ ኮንፈረንስ ላይ ኢብራሂም እድሪስ እንዲህ ይላል፡፡

> "In the traditional Ethiopia, blood-money played an important social function in that it helped to heal the injuries sustained by the relatives of the deceased. The payment of blood-money helped to attain apporochement between the parties involved" (IES 1990: 31).

የደም ካሳ ገንዘብ ጠበኞቹ ታርቀው ወንድማማችነት እንዲፈጥሩና በወዳጅነት እንዲግባቡ ያደርጋቸዋል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ የደም ካሳ ከፍተኛ ተቀባይነት ስላለው ጠበኞችን በማረጋጋት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

## 5.2. በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ዘንድ አቦገረብ ከመደበኛው ፍርድ ቤት የሚመረጡበት ምክንያት

አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው። አንድ ሰው ጥፋት ፈፅሞ ወደ ጫካ ወይም ወደ ዘመናዊው ህግ ከመሄድ ይልቅ አቦገረብ ወዳሉበት ፈጥኖ ይሄዳል። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም አቦገረብ ጥፋተኛው ጥቃት እንዳይደርስበት የመከላከል ህዝባዊ ሃላፊነት ስላላቸው ነው። የዕርቁ ስርዓት ፈጣንና ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥ መሆኑም ከመደበኛው ፍርድ ቤት የሚመረጥበት ሌላው ምክንያት ነው።

## 5.3. በራያ አላማጣ ማህበረሰብ መደበኛ ፍርድ ቤት ከባህላዊው ይበልጥ ጠቃሚና ፍትሐዊ የመሆን ሁኔታ፤

አውራ መረጃ አቀባዮቹ ከሆኑት ዘጠኝ ሰዎች፣ ስምንቱን ባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት ጠቃሚና ፍትሐዊ መሆኑን የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ይናገራሉ። አውራ መረጃ አቀባዮቹ ከሆኑት አንዱ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ (2)ግን አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ጠቃሚ እንዳልሆኑ፤ ሰላምና መረጋጋት ከመፍጠር ይልቅ ብጥብጥና ድብድብ የሚያነግሱ መሆናቸውን ይናገራሉ። ይህንን የሚሉበትን ምክንያትም እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> አቦገረብ ጥሩ አይደሉም። ወንጀለኛ ታውቆ ቅጣቱ እንዳያገኝ፣ እስከ መጨረሻ ታስሮ ቅጣቱ እንዳይቀበል እያደረጉ ነው። እያታየ ያለው ጉድኮ ጉድነው። ቅዳሜና እሁድ ካየህ ከሚያስታርቁበት በላይ ጊዜአቸውን የሚያጠፉት እየበሉ እየጠጡ ነው። የፈረደባቸው የሚች ወገኖች አሉ፣ ደግሰው ያበላሉ። ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ብትሄድ ጉድ ትላለህ። ጥፋተኛው የመንግስት አካላት እንዳይመረምሩት፣ ነገሩ ተጠፋፍቶ ወይም ተድበስብሶ እንዲቀር ሲያደርጉት ታያለህ (ግንቦት 02፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 54) ።

እኚህ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ መረጃ አቀባይ አያይዘውም፣ አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ለራሳቸው ተጠቃሚ እንደሆኑ፣ የሚች ወገኖች ከሚከሱት ካሳ በተጨማሪ ለምግብና መጠጥ እንዲያወጡ እንደሚያደርጉ ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ አቦገረብ ወይም ድባርተ ያስታርቁኛል ከማለት የተነሳ እርስ በራሱ እንደሚጋጭ ይገልፃሉ። ዘመናዊው ወይም መደበኛው ህግ ከሆነ ግን በርከት ያለ የገንዘብ ቅጣት

ቀጥቶ ጥፋተኛው ለዓመታት እንዲታሰር ስለሚያደርግ፣ ሰዎች ላለመጣላት ይጥራሉ የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡ እንደ ተጠያቂው አባባል ሕግ እያወቀ የሚያጠፋ ከሆነ የሞት ፍርድ ቢፈረድበትም አይቆጭም ይላሉ፡፡

"ሕግ ካልሰማማ ለምን አያልቅም? የሚገርምኮነው፣ በአሁኑ ጊዜ ህግ ምን እንደሚል የማያውቅ ማን ነው? ህፃኑ፣ ወጣቱ፣ ሽማግሌዎቹ ያውቃሉ፡፡ እያወቀ ሳጠፋ ሞት ፍርድም ይገባዋል፡፡ እኔ ይህንን ነው የምለው (ግንቦት 02፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 54) ፡፡

እኚህ መረጃ አቀባይ ያቀረቡትን ሐሳብ አቶ ተላ ቓሺ ይቃወሙታል፡፡

"ሰው ለምን ያጠፋል? ለምን ይጣላል? አይባልም፤ አይደለም የሰው ልጅ ድንጋይ ከድንጋይ ጋር እንኳን ይጋጫል፤ ሰዎች በተጣሉበት ጊዜ መንግስት መከታተል ወይም ማስታረቅ ደግሞ አይቻልም"(ግንቦት 02፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 54)፡፡

አቶ ተላ ቃሺ በሰዎች መካከል መጣላት እንዳለ ሆኖ፣ የአገር ሽማግሌዎች ወይም አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ መፍቻ ስርዓቶችም ማስታረቅና ማስማማት እንዳለባቸው እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> አለመጣላቱ ጥሩ ነው፡፡ መንግስትም አቦገረብም የሚፈልጉት ይሄን ነው፡፡ የሰው ልጅ እንዲወነጀል የሚፈልግ የለም፡፡ አገር ሰላም እንዲሆን ዋናው ዓላማቸው ነው፡፡ አቦገረብ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት እኮ ደመወዝ ኑሯቸው አይደለም፡፡ አጠገባቸው ሆነን እንታዘባለን፡፡ ነገር ግን የራሳቸው ህዝብ እየተጣላ እንዴት ያያሉ? እ...? (ግንቦት 02፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 55)፡፡

አቶ ተላ ቓሺ የራያ ሰው ቢጣላ እንኳ ከነ ቂም በቀሉ ውሎ እንደማያድር፣ ዛሬ ተጣልቶ ነገ አብሮ እየበላ እየጠጣ እንደሚውል፣ ሰይጣን እስካለ ድረስ ሰው ለምን ይጣላል እንደማይባል ይናገራሉ፡፡

## 5.4. በራያ አላማጣ ወረዳ አቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ከመደበኛ ፍርድ ቤት ጋር ያላቸው ዝምድና

መረጃ አቀባዮቼ እንደ ነገሩኝ፣ በራያ አላማጣ ያሉት አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጋር ተባብረው ይሰራሉ፡፡ በአካባቢው ማንኛውም ግጭት ሲከሰት፣ ቅድሚያ አቦገረብ እንዲያዩት ዘመናዊው ፍርድ ቤት ይፈቅዳል፡፡ አቦገረብ እና ድባርተ በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ዕርቁን ካጠናቀቁ በኋላ በፅሑፍና በአካል በመቅረብ ለዘመናዊው ፍርድ ቤት ያሳውቃሉ፡፡ አቦገረብ እና ድባርተ ከዘመናዊው

ሕግ በጋራ በመሆን የሚሰሩበት ሁኔታ ለሁሉም የግጭት ዓይነት ላይሆን ይችላል። ግጭቶቹ ቀላል ከሆኑ፣ በአቦገረብ ወይም ከዛ በታች ያሉትን ሽማግሌዎችና ጎረቤቶች ሊያስታርቋቸው ይችላሉ። ይህን አስመልክተው አቶ ብርሃኑ አበራ እንዲህ በማለት ይናገራሉ።

> ...አዎ! እዎ! በደንብ ነው እንጂ፣ አሁን አየህ አንደኛው በዘመናዊው ህግ መሰረት በማድረግ የሚሰራ ስራ ነው። ያኛውም በሽምግልና በአቦገረብ የሚወሰን ውሳኔ ነው። እነዚህ "አቦዓዲ" ወይም አቦገረብ የሚባሉት ሽማግሌዎቹ የወሰኑት ውሳኔ፣ ህዝቡ አምኖበት ከልቡ ተቀብሎት የሚደረግ ነው። ግን እንዴት ነው፣ እ... ዘመናዊው ህግ ባህላዊው ሽምግልና ያበረታታዋል። ማንኛውም ጠብ ሲከሰት መጀመሪያ የአገር ሽማግሌዎች እንዲያዩት ይመከራል (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 3)።

በተለይም የግድያና የድብደባ ወንጀሎች ሲፈፀሙ፣ ጥፋተኛው ወይም ገዳዩ በሁለቱም በኩል ይመራመራል።አቦገረብና ድባርተ የገዳዩ ጥፋተኝነት መርምረው ካበቁ በኋላ ያስታርቋቸዋል። የሟችና የገዳይ ወገኖች ከታረቁ በኋላ፣ ገዳዩ የሰበሰበው የገንዘብ መጠንና ሌሎች ያደረጋቸው እገዛዎች ይዘው ወደ ዘመናዊው ፍርድ ቤት ይሄዳሉ። ዘመናዊው ፍርድ ቤትም በአቦገረብ የተደረገውን ስምምነት ወይም የሟችና የገዳይ ወገኖች የፈፀሙትን ስምምነት ከሰማ በኋላ የራሱን ውሳኔ ይሰጣል።

በዘመናዊው ሕግ ያሉት ሰዎች ከአቦገረብ እና ድባርተ ጋር በመገናኘት የመመካከር ስራ እንደሚሰሩ ወይዘሮ በለጠች እንደሚከተለው ነግረውኛል።

"ከመንግስት አካላት መጥተው ወይም እኛ ወደ እነሱ እንድንሄድ ጠርተውን እንገናኝና፣ መበርታት እንዳለብን፣ ህዝቡን እየረዳነው እንደሆነ፣ መንግስትም የሚደግፈው ባህላዊ ዕርቅ መሆኑን ይነግሩናል" (ሚያዚያ 28፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 34) ።

እንደ መረጃ አከባዮቹ አባባል መንግስት ወይም መደበኛ ፍርድ ቤት ከአቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በመተባበር የሚሰሩበት ምክንያት፣ በአካባቢው ሰላምና ፍትህ እንዲነግስ ነው። ባህላዊ ዕርቅ ከሌለ ዘላቂ የሆነ ሰላም አይኖርም፤ ወይም ደግሞ ጠበኞች በመደበኛው ፍርድ ቤት ተቀጥተውና ታስረው ከወጡ በኋላ፣ ስላልታረቁ ድጋሚ መጋጨታቸው አይቀርም ከሚል እምነት ነው።

የራያ አላማጣ ማህበረሰብ የአቦገሬብ እና ድባርተ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ለበርካታ ዘመናት ሲገለገል ቆይቷል፤ አሁንም እየተገለገለባቸው ይገኛል። መደበኛው ህግም ይህንን ሁኔታ ተቀብሎታል። ስለዚህ አብረው በሚሰሩበት ጊዜ፣ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት የመደበኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሽርበት ወቅት ወይም አጋጣሚ እንደሌለ ይናገራሉ። በአንፃሩ ፍርድ ቤት የባህላዊውን የፍትህ ስርዓት ውሳኔ የሻረበት ወቅት እንደሌለም ይናገራሉ።

በአሁኑ ጊዜ ለራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ዋናው የፍትህ ስርዓት በመሆን እያገለገለ የሚገኘው ከዘመናዊው ሕግ ይልቅ አቦገሬብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶችን ነው፡

ሴቶች በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ያላቸው ተሳትፎ እና ውሳኔ የመስጠት መብት የተጠናከረ አይደለም።በተለይም በግድያ እና በድንበር ግጭትን በመሳሰሉ ከባድ የግጭች ዓይነቶች አንድ ወይም ሁለት አዋቂ የተባሉትን ሴቶች በዕርቁ ሂደት ይሳተፋሉ እንጂ፣ "ሴቶች ወሬ ያበዛሉ፣ምስጥር አይደብቁም" ከሚል ምክንያት የተነሳ ጎን ለጎን ሆነው ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ከማራመድ አልፈው ፍርድ ሊሰጡ አይችሉም።

## 6. ትንተና እና ቁዘማ (Analysis and reflection)

ይህ ክፍል በአቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ያሉት ሂደቶች፣ መዋቅሮች፣ የአፈፃፀም ስርዓቶች (Rituals) ከተጨማሪ ትርጓሜ (Interpretation) ጋር እና ልዩ ልዩ ትእምርታዊ (Symbolic) ጉዳዮችን የሚተነተንበት ክፍል ነው።

### 6.1. አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ያላቸው ማህበራዊ እሴቶች፣ እምነቶችና መርሖች

በራያ አላማጣ ወረዳ ያሉት አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶችና እንቅስቃሴዎች፣ ከእምነት፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትእምርቶች የተያያዙ ናቸው። እነዚህ እምነቶችና ትእምርቶች ጠበኞችን ለማስታረቅ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ዘዴዎች የያዙ ናቸው። በሚያስታርቁበት ጊዜ የሚያነሷቸው ሐሳቦች እና ለጸሎት የሚመርጧቸው ቦታዎች የያዟቸው ትእምርቶች እና ሌሎች የክዋኔ ስርዓቶች የሚያካትቱ ናቸው።

#### 6.1.1. ድባርተ የሚጸልዩበት ወይም የሚለምኑበት ቦታ

ድባርተ ፈጣሪያቸውን ሲለምኑ፣ተሰባስበው ስለተፈጠረው ግጭት ሲወያዩ በአጠቃላይ ችግር በተከሰተበት ጊዜ፣ ነገሩን ለማቃለል ሲያስቡ ወደ ተራራ፣ ዛፍ ስር ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። ወይዘሮ በለጠች መሐሪ፣ ድባርተ ወደ ተራራ ለምን እንደሚወጡ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

"ቦታ እ... ለመሰብሰብ እንዲመችን፤ ከግራም ከቀኝም ለሚመጡት ሴቶች የሚታይ ቦታ እንዲሆንላቸው ነው። እ.... ሌላም ጣጣ ሊኖረው ይችላል" (ሚያዚያ 28፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 33) ።

እንደ ወይዘሮ በለጠች አገላለፅ፡- ምህላ ወይም ጸሎት የሚያደርጉበት ቦታ ተራራ የመሆኑ ሚስጢር፣ ለመሰብሰብ እንዲመቻቸው ነው። ነገር ግን እሳቸው ባያውቁትም ሌላ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ጠቁመዋል። አቶ እምባየ ደስታ ተራራ የሆነበትን ምክንያት እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> ተራራ የሰፈሩ ህዝብ ይሰማዋል። ስለዚህ ሁሉም ሰው እየሰማ ይወጣል ማለት ነው። እግዚአብሐርምኮ ይሄን ነው

> የሚያገዘው፡፡ እየሱስ ክርስቶስ ለጸሎት ተራራ ላይ ይወጣ ነበር፡፡ አባታችን አምላካችንም እኮ ደቀመዛሙርቱ የሆኑትን ሐዋርያት ተኝተው እያሉ ይፀልይ ነበር፡፡ በተጨማሪም ማታ ከሆነ፣ እ... ብዙ አለው፡፡ ማታ ልጆች ይተኛሉ፣ ከብቶች አበረታቸው ላይ ይገባሉ፤ ምን ልልህ ፈልጌ ነው፣ እ... በጸሎት ጊዜ ጫጫታ አያስፈልግም፡፡ ምን ይህ ብቻ ካህናት ሰዓታት ሲቆሙኮ በቀን አይደለም፡፡ ተመስጦ ያስፈልገዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምክንያት ነው ሴቶች እግዚኦ መሐረነ እያሉ ማታ ማታ የሚጸልዩት (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 27)፡፡

አቶ እምባየ ደስታ ከተናገሩት መረዳት የሚቻለው የራያ አላማጣ ማህበረሰብ የሚገለገልባቸው ድባርተና አቦገረብ የዕርቅ ስርዓቶች፣ ከክርስትና ሃይማኖት የተያያዙ ናቸው፡፡ ሴቶች ለጸሎት ወይም ለምህላ ለምን ተራራ ላይ እንደሚወጡ፣ ሁለት ምክንያቶች ተናግረዋል፡፡ አንደኛው ትርጉም ተራራ ከፍተኛ ቦታ ስለሆነ፣ የአካባቢው ሴቶች ጸሎት ወይ ምህላ ሰምተው እንዲወጡ ነው፡፡ እየሱስ ክርስቶስ ተራራ ላይ ወጥቶ የመፀለዩ ምክንያት ከዚህ ጋር ይያያዛል፡፡

ይህ ዓይነት የጸሎት ስርዓት እየሱስ ክርስቶስ ለጸሎት ተራራ ላይ ይወጣ ከነበረው በቀጥታ ይዛመዳል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን "ህዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፡፡ በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበር" (ማቴ፣ ምዕ 14፣23)፡፡

እየሱስ ክርስቶስ በምድረ እስራኤል በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙ ህዝብ እና የአይሁድ አለቆች እንዳሳደዱት ሁሉ፤ ብዙ ህዝብም ይከተለውና ትምህርቱን ሰምቶ ያደንቀው ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ሲያስተምር ውሎ፣ ሐዋርያት በተኙበት ጊዜ ለብቻው በጨለማ ይጸልይ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አቶ እምባየ ደስታ እንዳሉት ድባርተ በብዛት በጨለማ ወይም እራት ከተበላ በኂላ ይወጣሉ፡፡

> "በዚህ ጊዜ ከኂላችን የገዳይ ወገኖች ሸማነ (ጥቁር ልብስ) ለብሰው ፊታቸው አፈር እየለበሱ ይለምናሉ" (ሚያዚያ 22፣2003 ስክርብ ገፅ 24)፡፡

## 6.2. በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ላይ የሚታዩ ብርታቶች እና ድክመቶች፤

ብዙ ጊዜ መረጃ አቀባዮቼ እንደሚሉት አቦገረብ በርከት ያሉ ጠንካራ ጎኖች አሉት፡፡ ከእነዚህ መካከል፣ ሳይሰላቹ በፍፁም ትዕግስት ጠበኞቹን ማስታረቅ፣ ደመወዝ

ሳይከፈላቸው ለህዝብ ደህንነት ሲሉ ብቻ ማገልገል፣ የተጋጩትን ሰዎች ስር የሰደደ በቀል እንዳይኖራቸው በጋብቻና በክርስትና/አባትነት/እናትነት ማስተሳሰር ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ ጋር አያይዘው አቶ አርሴ ማርየ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል።

"አቦገረብ የሌለው ህዝብማ እ... ምሰሶ የሌለው ቤት ነው። ተንኮል ያለው ሰው አለ፣ የዋህ የሆነ አለ፤ እነዚህ የተለያዩ ባህሪ ያላቸው ሰዎች አንድ ላይ አይኖሩም ነበር። አቦገረብ ግን የሁሉንም ባህሪ ችለው፣ ሳይቀየሟቸው በተጣሉበት ጊዜ ያስታርቃሉ" (ሚያዚያ 07፣2003 ስክርብ ገፅ 20)።

ጥንካሬአቸው እንዳለ ሆኖ አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ እንደሚሉት ደግሞ፣ አቦገረብና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በአካባቢው ጠብ እንዲነግስ ያደርጋሉ። የተጋጩት ሰዎች በመደበኛው ህግ ሳይቀጡ በአቦገረብ የሚታረቁ ከሆነ፣ ከመጋጨት አይቆጠቡም በማለት ቅሬታቸውን ይገልፃሉ። ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ መረጃ አቀባዩ እንዳሉት፣ "አቦገረብ ጥሩ አይደሉም። ወንጀለኛ ታውቆ ቅጣቱ እንዳያገኝ፣ እስከ መጨረሻ ታስሮ ቅጣቱ እንዳይቀበል እያደረጉ ነው" (ግንቦት 02፣2003 ስክርብ ገፅ 54)።

በራያ አላማጣ ወረዳ ግጭቶችን መፍታት በሚያስችሉ አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ላይ ብዙ የሴቶች ማግለል ባይታይም በተወሰነ መልኩ ግን አለ። በማንኛውም የግጭት ዓይነት (በተለይም ከባድ ግጭቶች) ድባርተ ከአቦገረብ ጎን ለጎን በመሆን የዕርቁ ስርዓት እንዲፋጠን ወይም ግጭቱ እንዲበርድ ያደርጋሉ። ይህም በምህላና በጸሎት ነው።

በኢትዮጵያ ያሉት ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በብዛት የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ እንደሆነ ታረቀኝ አደቦ "Many Ethiopian traditional mechnisms bias against women and being an all-male institution" (2002, 17). በማለት ይገልፃል። አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ባህላዊ ስርዓቶች በሴቶች እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ አላቸው። ከዚህም አልፎ ሁሉም ተሳትፎዎች የወንዶች እንዲሆኑ የሚያደርጉ ናቸው።

አቦገረብ እና ድባርተ የዕርቅ ስርዓቶች በአሁኑ ጊዜ በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ። ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ለወደፊት በቀጣይነት እንደሚያገለግሉም በአሁኑ ጊዜ እየተደረገ ባለ የባህላዊ ሽምግልና ስርዓት መተዳደሪያ ደንብ እንዲጸድቅ ማድረግ ዋና

ፍንጭ ነው። ለወደፊት ሂደቶቹ ወይም መዋቅሮቹ አከዋወናቸው ሳይቀየር የመቀጠል ሁኔታ አስጊ ነው። ምክንያቱም አንድ አንድ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት፣ ድሮ በሬ የነበረውን ዕርድ በአሁኑ ጊዜ ወደ በግና ፍየል መቀየሩ፣ አልፎ አልፎም ከነ አካቴው ዕርድ ሳይደረግ የዕርቅ ስርዓቱ የማስፈፀም አዝማሚያቸው ይታያሉ። በባህላዊ የዕርቅ ስርዓት መዳኘት ወይም የአቦገረብ እና ድባርተ የመቀጠላቸው ሁኔታ ግን የሚያጠራጥር አይደለም። ከአሁኑ በፊት ከነበረው በበለጠ ተጠናክሮ፣ ባህላዊ ሕግ ጸድቆ፣ መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቶለት እያገለገለ መሆኑን አቶ ብርሃኑ አበራ እንዲህ ብለውኛል።

> በእከሌ ሰበብ ይሄን ያህል ዓመት ታስሯል፤ ይሄን ያህል ገንዘብ ተቀጥቷል መባሉ አይቀርም። በአገር ሽማግሌዎች ከታረቁ ግን እንዲህ ዓይነት ችግር አይከሰትም። መንግስትም በተለይም በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ሽምግልና እያበረታታ የሚገኝበት ሁኔታ ነው ያለው። አቦገረብ በአሁኑ ጊዜ ጥሩ ደረጃ ላይ ነው ያሉት። ለእያንዳንዷ ነገር የቅጣት ልክ አበጅተውላታል (ሚያዚያ 06፣2003 ስክርብ ገፅ 8) ።

## 6.3. ጠበኞች አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቶች ተቀብለው ጉዳያቸውን ወደዚያ እንዲወስዱ የሚያደርጓቸው መሰረታዊ ምክንያቶች

አቦገረብ እና ድባርተ ከአካባቢው ማህበረሰብ ወይም ከመንግስት የሚያገኙት አንዳች ጥቅም የለም። ነገር ግን ከአባቶቻቸው በወረሱት መልካም ምግባርና እምነት፣ ማህበረሰቡ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ ይለፋሉ። ዓላማቸው ይህ በመሆኑም፣ የማይቆጡ፣ ቅንና አስተዋይ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ እንዲህ ይገልጸዋል።

> “ሽማግሌዎች ልከኞች፣ ጭምቶች፣ ራሳቸውን የሚገዙ፣ በእምነት፣ በፍቅር፣ በመፅናትም ጤናሞች እንዲሆኑ ምከሯቸው” (ቲቶ፣ 2፣2) ።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የሽምግልና ስርዓት መጠበቅ እንዳለበት በሐዋርያት ስራ እንዲህ ተገልጾአል። “በከተማዎችም ሲዞሩ፣ በእየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የመሰረቱትን ስርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጧቸው” (ሐዋ፣ 16፣24) ።

የአገር ሽማግሌዎች በተገልጋዩ ማህበረሰብ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። ከእድሜ አንጻርም በብዛት የዕድሜ ባለጸጎች ስለሆኑ፣ በፍርድ ጊዜ አያዳሉም። በመጽሐፍ

ቅዱስም ቅንነትና ሐቀኝነት ይኖራቸው ዘንድ አደራ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ ወደ አቦገረብ የሚሄድበት ምክንያትም ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ ገዳይ አቦገረብ ቤት ቢገባ እንኳ በሟች ወገኖች አይደፈርም፡፡ ማህበረሰቡ በአቦገረብና ድባርተ ካለው ከፍተኛ አክብሮት፣ እነሱ ይዳኙን በማለት በእምነት አደራ ይሰጣቸዋል፡፡

አቦገረብ ጠበኞች ከመታረቃቸው በፊት መሸሸጊያም ናቸው፡፡ የአካባቢው ሕዝብ በሚጋጭበት ጊዜ ችግሩን አቦገረብ ይፈቱልኛል ከማለት የተነሳ ቀድሞ እነሱ ወደ አሉበት ይሄዳል፡፡ ስለዚህ ህዝቡ ጉዳዩን ይዞ የሚሄድበት ምክንያት አንዱ ይህ ነው፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ(1) አባት እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡፡

"ለጊዜው መደበቅ ካለበት እንዲደበቅ ይመክሩታል፡፡ አይዞህ እኛ ጋር መቆየት አለብህ ካሉትም እነሱ ጋር ይቆያል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አቦገረብ ጥሎ አይጥልም፡፡ የምትድንበት መንገድ ያፈላልጋሉ፡፡ እንደዚህ እያሉ ነው የዕርቁ ስነ-ስርዓት የሚያካሂዱት" (ሚያዚያ 11፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 44)፡፡

## 6.4. አቦገረብና ድባርተ ማህበራዊውን ሰላም የማስጠበቅና የማረጋጋት ፋይዳ

አቦገረብ ሕይወትን በተለያዩ አቅጣጫዎች ይተረጉሟታል፡፡ ሕይወት ደስታ ነች፣ ሕይወት ሐዘንም ነች፣ በራያ አላማጣ ወረዳ ሰው በሚሞትበት ጊዜ፣ በገዳይ ወገኖችና ሟች ወገኖች ሐዘንና ዋይዋይታ ይበረክታል፡፡ መሪር ሐዘንና ከፍተኛ ቁጭት ይስተዋላል፡፡ ከዚህም የተነሳ ሐዘኑ የደረሳቸው ሰዎች እራሳቸውን ይጎዳሉ፡፡ የአለምን ከንቱነት፣ የሰው ልጅን ጠፊነት ይገነዘባሉ፡፡ የሚለብሱት ልብስ ድሪቶ፣ የሚበሉትና የሚጠጡትም ከወትሮው በተለየ መልኩ በጥራቱ የወረደ ነው፤ ይህ ደግሞ ከባህል አንፃር ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል፡፡ የሟች ወገኖች ሐዘናቸውን በለቅሶ ካላወጡት፣ በውስጣቸው የታመቀ ሕመም ያረግዛሉ፤ የመንፈስ መረጋጋትም አይታይባቸውም፡፡ በሌላም በኩል አምርሮ ማልቀስ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላትን ያተርፋል፡፡ እግዚአብሔር ፈጠረ፣ እግዚአብሔርም ወሰደ፤ ለሚለው እውነታ መቃወምን ያህል ነው፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ ትእዛዝ፣ ከአቦገረብ ባህላዊ ስርዓት ጋር ተዋህዷል፡፡ በአንደኛ ቆሮንቶስ መልእክት ላይ እግዚአብሔር ላደረገው ነገር ወይም የሞተው ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ማዘን እንደማያስፈልግ እንደዚህ ይላል፡፡ "በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ሐዘንን በታገሰ ምስጋናን ይገባዋልና" (2፣19)፡፡

የአቦገረብ መተዳደሪያ ደንብ የተለያዩ ማሕበራዊ ደንቦች ከክርስትና ሃይማኖት የተያያዙ ናቸው። በማሕበረሰቡ ላይ ለሚያደርጉት ውሳኔና አስተምህሮም ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር የተያያዘ ነው። አቦገረብና ድባርተ ሐዘን እንደማያስፈልግ የሚች ወገኖችን ሲያፅናኑ ይህንኑ እንደ መሳሪያ ይጠቀሙበታል።

የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ሰው ሲሞት ወይም በአካባቢው አንዳች ከባድ ችግር ሲከሰት፣ ሸማኒ መልበስ፣ አፈር እየጫሩ ሰውነታቸው ላይ መነስነስ፣ ፊታቸውን መንጨት፣ በአጠቃላይ እራስን ዝቅ ማድረግ በመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከኦሪት ጀምሮ ይፈፀም የነበረ ድርጊት ነው። "ያዕቆብም ልብሱን ቀደደ፣ ወገቡንም ማቅ ታጥቆ ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ" (ዘፍ፣ 37፣34) ።

በሐዘን ጊዜ ራስን ማቆሸሽ ወይም እራስን መናቅ ከአብርሃም ዘር የተወረሰ ነው። ያዕቆብ ልጁን በሞተበት ጊዜ አምርሮ አለቀሰ፣ ወገቡንም በማቅ ታጥቆ ወዲያ ወዲህ በመንጎራደድ የዓለምን ከንቱነት ሰበከ። በዚህ ጊዜ ነበር ያዕቀብ የሚያደርገው ነገር ትክክል እንዳልሆነ እግዚአብሔር ያስጠንቅቀው ዘንድ በህልሙ የታየው፤ አፈር የመልበስ፣ በግንባር ተደፍቶ ማልቀስ፣ ከኢያሱ ታሪክ የተያያዘ ነው። በመፅሐፈ ኢያሱ ወልደ-ነዌ እንዲህ ይላል። "ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፣ እሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ፊት እስከ ማታ ድረስ በግንባራቸው ተደፉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ" (ምዕ 7፣6)። ከሙሴ መሞት በኋላ የእግዚአብሔርን ልጆች ይጠብቅ ዘንድ የተተካው ኢያሱ ወልደ-ነዌ ነው። ኢያሱ ሕዝቡን ከምድረ ግብፅ ወደ ከነዓን ስፍራቸውን እንዲቀይሩ አስቀድሞ ሰላዮችን ይልካል። ሰላዮቹ ከነአን ከመድረሳቸው በፊት ጋይን[21] እንዳሉ በጠላት ተሸንፈው ሰላሳ ስድስት ሰዎች ይሞቱባቸዋል። ኢያሱም ይህን በሰማ ጊዜ አምርሮ አለቀሰ፣ ትቢያም እላዩ ላይ ነሰነሰ።

ድባርተ እና የሚች ወገኖች፣ አልፎ አልፎም የገዳይ ወገኖች ሸማኒ ለብሰው አፈር እየጫሩ የሚለምኑበት ምክንያትም ችግር ስለተፈጠረ፣ ሞት ስለተከሰተ ነው። ስለዚህ አቦገረብና ድባርተ ጠበኞችን ከማስታረቅ በተጨማሪ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንደሚሰሩ እውን ነው።

---

21 [illegible]።

## 6.5. የራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ አቦገረብ ባህላዊ ስርዓት ከመደበኛው ፍርድ ቤት የሚመርጥበት ምክንያት

በባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ዙሪያ ያጠኑ ተመራማሪዎች በብዛት ማህበረሰቡ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ይልቅ ባህላዊውን የሚመርጥበት ምክንያት ሲገልፁ፦ ለባለጉዳዮች መኖሪያ ቅርብ በመሆኑ፣ የሚያስወጡት ወጪውም እጅግ በማነሱ፣ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዱ በጣም አነስተኛ በመሆኑ እና ሌሎች ምክንያቶች ይጠቁማሉ።

የራያ አላማጣ ማህበረሰብም አቦገረብና ድባርተ ባህላዊ ስርዓቶች የሚመርጥበት ምክንያት እነዚህ በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ተመስርቶ እንደሆነ ይናገራሉ፣ አቶ ብርሃኑ አበራ የራያ አላማጣ ማህበረሰብ አቦገረብ ባህላዊውን ስርዓት ለምን እንደሚመርጥ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

"ማህበረሰቡ ትልቅ እምነት የጣለባቸው በአገር ሽማግሌዎቹ ላይ ነው። ለምን ካልከኝ እ... ከገንዘብ አኳያ፣ ከምንም እኳያ ሲታይ፣ አቦገረብ የሚሰጡት ውሳኔ ቀላል ነው" (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 10) ።

አቦገረብ የሚወስኑት ውሳኔ እና መደበኛው ፍርድ ቤት የሚወስነው ውሳኔ ይለያያሉ። አቦገረብ ከህብረተሰቡ የኢኮኖሚ ደረጃ አንፃር፣ ለመግደል ያነሳሳው ነገር በመመርመር፣ ወይም ከሌሎች ነገሮች ጋር በማመዛዘን ገዳዩን ወይም ጥፋተኛውን የሚወስኑለት ውሳኔ ቀለል ያለ ነው። መደበኛው ፍርድ ቤት ግን እነዚህ ነገሮች ከግምት ውስጥ የሚያስገባ አይመስለኝም፤ቢያስገባም ሚዛናዊነቱ የጎላ አይደለም።

ሌላው ከዘመናዊው ፍርድ ቤት ይልቅ ባህላዊውን የአቦገረብ ስርዓት የሚመርጡበት ምክንያት መበቀልን ነው። ጠበኞቹ በዘመናዊ ፍርድ ቤት ቅጣታቸውን ተቀብለው ከወጡ በኋላ በአቦገረብ ካልታረቁ፣ ብቀላው ይቀጥላል። አቶ ብርሃኑ አበራ እንዲህ በማለት ገልጸውልኛል።

"እየህ የአገር ሽማግሌዎች ሳይቀላቀሉበት በመደበኛው ፍርድ ቤት የሚከናወነው ውሳኔ ግን ብዙ ችግር ይታይበታል። ታስሮ የወጣ ግለሰብ ቅድም እንዳልኩህ እ... በዳኞችም፣ በፖሊስ አካላትም ቅሬታ ያሳድራል" (ሚያዚያ 06፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 8)።

አቦገሬብ ቋሚ የሆነ ዕርቅ መፍጠር ዓላማቸው ነው፡፡ አይደለም ጠበኞቹ፣ የጠበኞቹ ዘመዶችም ካልታረቁ ሙሉ እርቅ አይባልም፡፡ ጠበኞቹ በአቦገሬብ የታረቁ እንደሆነ ለወደፊቱ የሚያሰጋቸው ነገር አይኖርም፡፡ ባህላዊ የዕርቅ መንገዶች ለወደፊቱ ያላቸው ጠቀሜታ ታረቀኝ አዴቦ እንዲህ በማለት ይገልፃል፡፡

> "Here, with the term traditional mechnisims for conflict resolution we mean long-persistent social practices, rooted in local cultural settings, aiming at resolving conflicts, reducing tension, and rebuilding social relation ships" (2002፡11).

ባህላዊ የዕርቅ መንገዶች በሀገር ባህል ላይ ተመስርተው ቋሚ የሆነ መረጋጋት መፍጠር፣ ጠበኞች ከጭንቀትና ስጋት ነፃ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ፤ እንዲሁም በጠበኞቹ መካከል የተፈጠረው ግጭት ድጋሚ በፍቅር እንዲገነባ ዓላማቸው ነው፡፡

## 6.6. በአቦገሬብ እና ድባርተ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ሂደት ውስጥ የራያ አላማጣ ማህበረሰብ ያለው ሚና

በራያ አላማጣ ወረዳ ማሕበረሰብ የዕርቅ ሂደት ውስጥ ጥፋተኛውን ለመለየት አቦገሬብ ምርመራ ያደርጋሉ፡፡ ጥፋተኛው ታውቆ መታረቅ እንዳለባቸው እስኪወስኑ ድረስ አቦገሬብ እርስ በርሳቸው እየተቀባበሉ ስለ ጉዳዩ ይወያያሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ አንድ አስተዋይ የሚባሉት የአገር ሽማግሌዎች ካልሆኑት በስተቀር፣ ሌሎች የሕብረተሰቡ ክፍሎች ጣልቃ የመግባት ሚና የላቸውም፡፡ ጥፋተኛው ማን መሆኑ ታውቆ፣ የዕርቅ ቀን ከተቆረጠ በኋላ ግን ህፃኑ፣ ወጣቱ፣ ሽማግሌው፣ ሴቱና ወንዱ እንዲገኙ ይፈቀዳል፡፡ ሁሉም ሰው በዕርቁ ስርዓት እንዲሳተፍ የሚያደርጉበት ምክንያት፡- ሁሉም ሰው መጋጨት ምን ያህል ክፉ ነገር እንደሆነ አይቶ እንዲማር ነው፡፡ በተለይም ህፃናት ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ቢማሩ ጥሩ ነው የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡

ሁሉም ሰው በዕርቁ ስርዓት መገኘቱ የሟች ወገኖች የህዝቡን ብዛት በማየት፣ ህፃናቱና አረጋውያን ጭምር በመገኘታቸው እንዲራሩ በማድረግ ረገድም ሌላ ሚና አላቸው፡፡ በዕርቅ ስርዓት ሂደት ውስጥ ሌላ ትልቅ ሚና ያላቸው የሃይማኖት አባቶች ናቸው፡፡ የሃይማኖት አባቶች ሲባል የነፍስ አባቶችም ይገኙበታል፡፡ የሟች ወገኖች ከገዳይ ወገኖች እንዲታረቁ የነፍስ አባት እንዲለምኑ ይደረጋል፡፡ ትላልቅ የአገር ሽማግሌዎችም

በማህበረሰቡ የሚፈሩና የሚከበሩ ናቸው። ታላላቅ አባቶች የመከበራቸው ሚስጢር ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የተያያዘ ነው።

በአንደኛ ጢሞቴዎስ ላይ "በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፣ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል (5፣17)። የአገር ሽማግሌዎች በብዛት ለህዝብ ደህንነትና ፍቅር ሲሉ የሚሰሩ ናቸው። "ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አንጠብቅም" ብለው የሚሰሩ ናቸው። የድካማቸው ይከፈለን ሳይሉ፣ ህዝቡን በመልካም አስተዳደር የሚያገለግሉ ናቸው። በዛው ልክ ህዝቡም ይወዳቸዋል፤ ከእግዚአብሔር በታች እነሱ እንደሆኑ ያምናል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሽማግሌዎቹ ለማህበረሰቡ ጥሩ ነገር ሰርተው ማለፍ ዓላማቸው ስለሆነ ነው። "... ሰውን መፍራት እግዚአብሔርን መፍራት ነው። እኛም አናሳፍራቸውም። ኃላፊነት ተሰምቶን ለህይወታችን ጥሩ ነገር ሰርተን ማለፍ ነው የምንፈልገው" (ሚያዚያ 22፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 25) በማለት አቶ እምባየ ደስታ ነግረውኛል።

## 6.7. አቦገረብና ድባርተ ለተለያዩ ማሕበረሰብ ክፍሎች መብት የሚያስተናግዱበት ሁኔታ

አቦገረብና ድባርተ ባሕላዊ የዕርቅ ስርዓቶች የአረጋውያንን፣ የሴቶችን፣ የህፃናትንና የሌሎች ተመሣሣይ የማሕበረሰቡ ክፍሎች መብት ለማስተናገድ፣ የራሱ የሆነ ሕግ የለውም።

## 6.8. በመደበኛው የፍትሕ ስርዓት ውስጥ ቢካተቱ የሚጠቅሙ የአቦገረብ እና ድባርተ መልካም ባህሪያት

በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ያሉት አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች በርከት ያሉ መልካም ባህሪያት አሏቸው። እነዚህ መልካም ባህሪያት በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ቢካተቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል።

በአቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ ስርዓቶች ዕርቅ ሲባል፣ ጠበኞቹን ማስማማት ወይም ይቅር ማባባል ብቻ አይደለም። ሙሉ ዕርቅ ወይም ቋሚ ፍቅር እንዲፈጥሩ የጠበኞቹን ዘመዶችም መታረቅ ይገባቸዋል የሚል እምነትም የያዘ ነው። " በግድያ ጊዜ በገዳይና ሟች ወገኖች ያሉ ቤተሰቦች መታረቅ እንዳለባቸው እንመክራለን" (ሚያዚያ 11፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 45) በማለት ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ አባት ተናግረዋል።

በመደበኛ ፍርድ ቤት የተጋጨትን ሰዎች ብቻ እንጂ የሌሎች ሰዎች ወይም የጠበኞች ዘመዶች ጉዳይ የሚዳስስ አይመስልም። ከዚህም የተነሳ በተደጋጋሚ ግጭቶች ይከሰታሉ። ጠበኞቹና ዘመዶቻቸው ወይም ቤተሰቦቻቸው ከታረቁ ግን ዘላቂ መፍትሔ ይገኛል የሚል እምነት አለኝ።

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት መገንዘብ እንደቻልኩት ህዝቡ ከእምነት ጋር የተያያዘ ነው። አቦገረብና ድባርተ የሚያደርጓቸው የዕርቅ ስርዓቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ወይም ትእዛዛት ጋር የተያያዙ ናቸው። ህዝቡ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዛት ከፍተኛ እምነት ጣይም አክብሮት አለው። ስለዚህ ማህበረሰቡ እንደየ እምነቱ እየተጠቀመ፣ ከመደበኛ የፍትህ ስርዓት እያዋሀደ፣ በፍቅርና በሰላም እንዲኖር እነዚህ ሃይማኖታዊ ስነ-ምግባራት ቢካተቱ መልካም ነው። በዚህ ዙሪያ መንገሻ ካሳ እንዲህ ብሎኛል።

"መፅሐፍ ቅዱስ ላይ የምናገኘው እያንዳንዱ ቃል ፍቅርና ሰላም፣ ዕርቅና ይቅርታን ነው። አቦገረብ ወይም የወንዝ አባትም በብዛት ህጋቸው ወይም መተዳደሪያ ደንባቸው ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው" (ግንቦት 02፣ 2003፣ ስክርብ ገፅ 51)።

## 7. ማጠቃለያ (conclusion)

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ አቦገረብና ድባርተ የሚባሉት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች አሉ። አቦገረብ የወንዶች ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ሲሆን፣ ድባርተ ደግሞ የሴቶች ነው። የድባርተ ዋና ስራ በጸሎት እና በምህላ የተከሰተው ችግር እንዲቃለል ማድረግ ሲሆን፣ ከአቦገረብ ጎን ለጎን በመሰለፍ ነው። ድባርተ ግጭት ሲከሰት ከሚያደርጉት ጸሎትና ምህላ ውጪ፣ዝናብ ሲያቋርጥ ያልታሰበ በሽታ ወይም ወረርሽኝ ሲከሰት፣ በውጊያ ጊዜ እና በመሳሰሉት ችግሮች ሲከሰቱም ይታያሉ። አቦገረብም እንዲሁ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጠብ ማብረድ በተጨማሪ ማህበራዊ ሁኔታዎችን በማስተካከል ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

በጥናቱ እንደታየው ድባርተ አቦገረብን በምህላና በጸሎት ከመርዳት አልፎ፣ በጥፋተኛው ላይ በሚያደርጉት ውሳኔ በብዛት ጣልቃ ገብተው የመሰላቸውን መናገር አይችሉም። ይህም ወንዶቹ ሴቶቹን በራስ የመተማመን ብቃት የላቸውም፤ ይፈራሉ፣ ወሬ ያበዛሉ ብለው ስለሚፈርጇቸው ነው።

አቦገረብ ማንኛውም ግጭት የመፍታት ዓቅም አላቸው። ነገር ግን ቀላል በሆኑት ግጭቶች ላይሳተፉ ይችለሉ። ቀላል የሆኑትን ግጭቶች በጎረቤት እና ሌሎች ትላልቅ አባቶች ሊያስታርቋቸው ስለሚችሉ፣ አቦገረብ በግድያ፣ በድንበር ግጭት፣ የአካል መጉደል፣ አልፎ አልፎም በጎረቤት መፍታት ላልተቻለው የቤተሰብ ጠብ ያስታርቃሉ።

በራያ አላማጣ ማህበረሰብ ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎች ስካር፣ በሴት /ውሽማ/ እና በግጦሽ መሬት ናቸው። አንዲት ሴት ባል ከሌላት ብዙ ወንዶች ለውሽምነት ይፈልጓታል። በተለይም ቆንጆና ዝነኛ ከሆነች ወንዶች ይጣሉባታል።

አቦገረብ ወይም ድባርተ መስፈርታቸው ብዙ ቢሆንም፣ ዋና ዋናዎቹ ግን ባላባት (የአካባቢው) ተወላጅ መሆን፣ የነገር ልክ የሚያውቅ፣ ዕድሜ ባለጸጎች (በብዛት)፣ ጨዋ ባሕርይና ፈሪሀ እግዚአበሐር ያላቸው ተጠቃሽ ናቸው።

አቦገረብ ከመደበኛው ፍርድ ቤት በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ አለ። አቦገረብ የማስታረቅ ስራቸውን የሚጀምሩት ነገሮችን ቀስ ብለው ከመከሩና የገዳይና የሟች ወገኖች ካረጋጉ በኋላ ነው።

አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ጠበኞችን ከማስታረቅ በተጨማሪ የጠበኞቹን ቅርብ ዘመዶችም እንዲታረቁ በማድረግ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ያበጃሉ፡፡

አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ለወደፊቱ የመቀጠላቸው ሁኔታ የማያጠራጥር ቢሆንም፣እንደ ዕርድ የመሰሉት የተወሰኑት ስርዓቶቻቸው ግን የመቀነስ አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡

በራያ አላማጣ ወረዳ ማህበረሰብ ስርቆት እንደ ተራ ወንጀል ሳይሆን እንደ ከባድ ወንጀል እና ምሕረት የማይደረግለት፤ኃጢያት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ይመስላል የአካባቢው ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች የማይከታተሉትና ለመዳኘት የማይሞክሩት ነው፡፡ ስርቆት ያልለፉበትንና ጉልበት ያላፈሰሱበትን ነገር የራስ የማድረግ ጉጉት ነው በማለት ያወግዙታል፡፡ እየሰረቀ የተገኘ እንደሆነ ቢገደል እንኳ ገዳዩን መንግስት ይከታተለዋል እንጂ በአቦገረብ ወይም በድባርተ በኩል ትኩረት አይሰጠውም፡፡

8. ይሁንታ (Recommendations)

1. አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች በተለያዩ ዘዴዎች ጠበኞቹን ካስታረቁ በኋላ፣ ድጋሚ እንዳይጣሉና በፍቅርና በሰላም እንዲኖሩ፣ በጋብቻ እንዲሁም በክርስትና አባትነት/እናትነት እንዲተሳሰሩ ስለሚያደርጓቸው፣ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ያስገኛሉ። ስለዚህ ይህ ዓይነቱ የዕርቅ ዘዴ ለመደበኛ ፍርድ ቤት አርአያ ሊሆን ስለሚችል የወረዳው ይፍትህ አካላት ትኩረት ሊሰጡበት ይገባል።

2. አቦገረብና ድባርተ ማህበረሰቡን የሚያገለግሉበት ያለ አንዳች ክፍያ ነው። ሽማግሌዎቹ ማህበረሰቡን በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ፣ የራሳቸውን ስራ በመተው፣ በሕይወታቸው ጥሩ ነገር ሰርተው ማለፍ ዋና ዓላማቸው ነው። ስለዚህ እነዚህ ቅን አባቶች እና እናቶች ተሳትፎአቸውን እንዲቀጥሉ በሚመለከታቸው አካላት በገንዘብም ሆነ በሞራል ማበረታታት ያስፈልጋል።

3. ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶቹ ጠበኞቹን የሚያስታርቁበት መንገድ፣ ከማህበረሰቡ እምነት፣ ባህልና ልምድ በመነሳት ነው። ሽማግሌዎቹ ጠበኞችን በሚያስታርቁበት ጊዜ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ባላቸው እውቀት እየጠቀሱ እና አንታረቅም ያሉ እንደሆነ፣ እግዚአበሔርም ለጥፋታቸው ይቅር እንደማይላቸው በማሳመን ነው። ስለዚህ መንግስትም ሆነ ሌላው አካል የማሕበረሰቡ እምነት፣ ባህልና ልምድ እንዲጠበቅ በዙርያው መወያየት ያስፈልጋል።

4. ማሕበረሰቡ በብዛት በመደበኛው ፍርድ ቤት ሲያማርር እና ሲያዝን እንጂ ሲደሰት አይታይም። ይህም ዘመናዊው የህግ ስርዓት የማህበረሰቡ ፍላጎት ያላሟላና ያላገናዘበ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ፖሊሲ አውጭዎች ለወደፊቱ በሚወጣው ህግ፣ ቅድሚያ የማህበረሰቡን ፍላጎት እና አመለካከት ሊያጠኑ ይገባል። በተለይ የባህልና ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም የፍትሕ ሚኒስቴር በእነዚህ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓቶች ጥልቅ የሆነ ጥናት ሊያደርጉ ይገባል።

5. በአንድ ሀገር ወይም አካባቢ የልማትም ሆነ የተረጋጋ ሰላም ማምጣት የሚቻለው ህብረተሰቡ በራሱ ልምድ፣ ባህልና ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች መጠቀም ሲችል ነው። ስለዚህ የሚመለከታቸው አካላት ለእነዚህ ነገሮች ትኩረት ሊሰጧቸው ይገባል።

## ዋቢ መፃሕፍት (Biblilography)


በርሀ አሰፋ:: "ስያመ ራያ አላማጣ"፣ሃርሞ ራያ፣28 ታሕሳስ 2002 ዓ/ም፣3ይ ሕታም፣መቐለ፤ዳዮ ሕትመት

ተክለጻዲቅ መኩሪያ::የግራኝ አሕመድ ወረራ፣አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣1966::

ፈቃደ አዘዘ:: የስነ-ቃል መምሪያ፣ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፣ 1991::

Andargachew Tilahun. "Conflict and conflict resolution Institutions among the Dess'a Tigray, North Eastern Ethiopia." M.A thesis (Anthropology) Addis Ababa. Addis Ababa University. 2009.

Asefa Abebe: "Proceedings of the second National work shop of Eth pian chapter of OSSREA". Addis Ababa. 2005.

Campbell, Lyle. "Historical Linguistics. An Introduction". Edinburgh: Edinburgh University press. 1999.

Ibrahin Edris: "Proceedings of the first National conference of Ethiopian studies". Institute of Ethiopian studies, Addis Ababa University.1990.

M.L. Bender etal. "Language in Ethiopia." London: oxford University press. 1976.

Sisay Mengiste: "Zäwäld and Indigenous conflict Transformation institution in Raya Challenges and prospects." MA thesis Addis Ababa University. 2010.

Tarekegn M. "Change and continuity in the traditional institution on Mechanisms of local governance and conflict resolution among the Wajrat." An Ethno Historical study. M.A thesis (Social Anthrop logy). Addis Ababa University; 2005.

Tarekegn Adebo. 2002. Making peace in Ethiopia: Fire cases of Traditional Mechanisms for conflict Resolution. Peace and Development committee.

Yosef Gebre Hiwet and Tesfaye WeldeMaryam; "Enhancing Traditional Conflict Management Institutions of pastoral communities in Southern Etiopia"

(Dassenech,Nyangatom,Hmer,Erbore).Cultural and Art Society of Ethiopia;Nov.2008.

## የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | --- | ወ | 63 | የተገናኘንበት ቀን ሚያዚያ 07/11/2003ዓ.ም ሲሆን፣ከጠዋቱ አራት ሰዓት አላማጣ ጃሪ ካፌ ላይ ነው::<br>በግብርና ስራ የተሰማሩ ሲሆን፣በኣሁኑ ሰዓት በ"ጎልጎል ራያ"የዘመናዊ መስኖ ተጠቃሚ ናቸው:: በግምት የተናገሩት እድሜያቸው 63 ቢሆንም፣እንደ እኔ አመለካከት በአካል ሲታዩ በአርባዎቹ የዕድሜ ክልል የሚሆኑ ይመስላሉ::በተለይም በቀ ደም እና በጥቁር ደም የግጭት ዓይነቶች እና ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓታቸው ሰፋ ያለ ማብራርያ ሰጥተውኛል::በአቦገረብ የዕቅ ሥርዓት ጣልቃ በመግባት የሚያስታርቁ ናቸው:: |
| 2 | --- | ወ | 58 | የተገናኘንበት ቀን ግንቦት 02/09/2003ዓ.ም ሲሆን፣ዘጠኝ ሰአት ገደማ መረዋ በሚባለው ቦታ በአርሻ ላይ እያሉ ነው::<br>በተወሰነ መልኩ በከብት ዕርባታ የሚተዳደሩ ቢሆኑም ዋና መተዳደሪያቸው ግን በእርሻ ነው::የአቦገረብ አባል ባይሆኑም፣ባህላዊው የአቦገረብ የዕርቅ ሥርዓት የሚሰጠው አገልግሎት እና የሚከተለው ሥርዓት እንዴት እንደሆነ እውቀቱ አላቸው:: ሙሉ በሙሉ አቦገረብ ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓት ጠቀሜታ እንደሌለው እና የእርስ በርስ ግጭትን የሚያስፋፋ መሆኑን ይመሰክራሉ:: |
| 3 | ብርሃኑ ኣበራ | ወ | 38 | የተገናኘንበት ቀን 06/08/2003ዓ.ም ሲሆን፣ስምንት ሰዓት ተኩል መስሪያ ቦታቸው በሆነው በአላማጣ ከተማ የጸጥታና ፍትህ ፅህፈት ቤት ነው::<br>በእንዳ መኾኒ ወረዳ ለአራት አመታት በአፈ-ጉባኤነት ያገለገሉ ሲሆኑ፣በአሁኑ ጊዜ የአላማጣ ከተማ የጸጥታ አስተዳደር ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ:: በአቦገረብ ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓት ቀና የሆነ አመለካከት ያላቸው ሲሆን፣አቦገረብ ለዘመናዊው ሥርዓት አጋዥ እንደሆነ፣ወንጀልን በመከላከል በኩል ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው እና በማህበረሰቡ የመፈቃቀር፣የመተጋገዝ እና የመሳሰሉ ሁኔታዎች እንደሚፈጥር የሚያምኑ ናቸው:: |
| 4 | ኣርሴ ማርየ | ወ | 75 | የተገናኘንበት ቀን ሚያዚያ 07/08/2003ዓ.ም ሲሆን፣በአስር ሰዓት አላማጣ ከተማ ላይ በሚገኘው ራያ ሆቴል ነው::<br>በኃይለ ሥላሴ ዘመን ስልጣን የነበራቸው (ምን ዓይነት የሥራ ድርሻ እንደነበራቸው አልገለፁም::)ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ በግብርና ሥራ ተሰማርተው በ"ጎልጎልራያ" የመስኖ ልማት ተጠቃሚ በመሆን ወደ ባለሀብትነት የተሸጋገሩ ናቸው::ከአስራ አምስት አመት በላይ አቦገረብ በመሆን ያገለገሉ ሲሆኑ፣በአሁኑ ሰአት ደገሞ በአቦገረብ ባህላዊ የዕርቅ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ሥርዓት በመሪነት እያገለገሉ ይገኛሉ። |
| 5 | እምባየ ደስታ | ወ | 92 | የተገናኘንበት ቀን ሚያዚያ 22/08/2003ዓ.ም ሲሆን፣እሁድ አምስት ሰዓት ዓጸላ በተባለው ቦታ በቂርቆስ ቤተ ክርስትያን ነው።<br>በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በመሬት አስተዳደር ሥራ ኃላፊነት የነበራቸውና በጭቃ ሹምንት ለብዙ ዓመታት (ለስንት ዓመታት እንዳገለገሉ አያውቁትም) የሰሩ ናቸው።በአሁኑ ጊዜ መንኩሰው በቅርቆስ ቤተ ክርስትያን የሚኖሩ ሲሆኑ፣ ለብዙ ዓመታት አቦገረብ በመሆን አገልግለዋል።ድባርተ ባህላዊ ዕርቅ የሴቶች ብቻ መሆኑን፣ድባርተ ለዕርቅ የሚጠቀሟቸው ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ፣አቦገረብ እና ድባርተ ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓቶች ያላቸው ትስስር እና የመሳሰሉትን ነገሮች ጠንቅቀው ያውቃሉ። |
| 6 | ፍርዱ እምባዬ | ወ | 42 | የተገናኘንበት ቀን ሚያዚያ 19/08/2003 ዓ.ም ሲሆን፣ ጋርጃለ ላይ በሚገኘው መኖርያ ቤታቸው አርብ ጠዋት ሦሥት ሰአት ነው።<br>መተዳደርያቸው በእርሻ ሲሆን፣ መደበኛ አቦገረብ ባይሆኑም፣በአከባቢው ግጭት ሲከሰት ተሎ በመድረስ የአገር ሽማገሌ በመሆን ያገለግላሉ። |
| 7 | መንገሻ ካሳ | ወ | 27 | በተደጋጋሚ ቀናት የተገናኘንና እንደ ጓደኛ ወደ መስክ አብሮኝ የዞረ ቢሆንም፣ ለራሱ ቃለ መጠይቅ ያደረኩለት ግን ግንቦት 02/09/2003 ዓ.ም ነው።<br>በውጪ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሑፍ አንደኛ ደግሪ በ 2000ዓ/ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተመረቀ ሲሆን፣በአሁኑ ሰአት በአላማጣ ወረዳ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያስተማረ ይገኛል። በዕረፍት ጊዜው በአቦገረብ የዕርቅ ስርዓት እያገለገለ ይገኛል። |
| 8 | ተላ ቓሺ | ወ | 50 | የተገናኘንበት ቀን ግንቦት 02/09/2003 ዓ.ም ሲሆን፣ስድስት ከሩብ እመኖርያ ቤታቸው ላይ ነው።<br>በግብርና ሥራ የተሰማሩ ሲሆኑ፣በዘበኛነት ተቀጥረውም ይሰራሉ።አቦገረብ ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓት ከዘመናዊው ህግ ሥርዓት ይልቅ ለራያ አላማጣ ማህበረሰብ ቅርብ መሆኑን እና ህብረተሰቡ የሚቀበለው መሆኑን የሚመሰክሩ ናቸው። |
| 9 | በለጠች መሓሪ | ሴ | 41 | የተገናኘንበት ቀን ሚያዚያ 28/08/2003 ዓ.ም ሲሆን ፣አላማጣ አካባቢ በሚገኘው ጥሙጋ የሚባል ቦታ ሆኖ ስድስት ሰዓት ከሩብ ከቀብር ሲመለሱ ነው ።<br>ከሃያ አመታት በላይ ድባርተ በመሆን አገልግለዋል።በአሁኑ ሰአትም እያገለገሉ የሚገኙና አቦገረብ የድንበር ወይም የግድያ ግጭቶችን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | በሚያስታርቁበት ጊዜ፣በድባርተነት የብዙ ዓመታት ልምድ ስላላቸው ከአቦገሬብ ጋር በመሆን ያስታርቃሉ። |